

# በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት



## በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ፈቃድ አስተዳደር፣ ግብይትና ቁጥጥርን በተመለከተ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት



ጥር/2007 ዓ.ም.

<u>አዲስ አበባ</u>

## ማውጫ ገጽ


መግቢያ ........................................................................................................................1

የማዕድን ሚኒስቴር አመሰራረት ........................................................................................1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማዎች፡-.........................................................................................2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ(*Vision*).........................................................................................2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር ...................................................................................3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀትና የሰው ኃይል.........................................................................3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ...................................................................................4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ሂደት መግለጫ...............................................................................4

የኦዲቱ ዓላማ...............................................................................................................10

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ....................................................................................................10

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ..............................................................................10

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ...........................................................................................11

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት..................................................................................................11

ክፍል ሁለት...........................................................................................................................13

የኦዲት ግኝቶች .............................................................................................................13

ሀ. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የከበሩና በከፊል የከበሩ የማዕድን ሀብቶችን በማዕድን አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎችና አሰራሮች መሰረት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማስተዳደሩንና መቆጣጠሩን በተመለከተ፣ ................................................................13

በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጡት አዋጆች፣ ደንቦች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች መዘጋጀቱን በተመለከተ፣13

በዕቅድ ክንውን ሪፖርት ላይ ለሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶች እርምጃስለመወሰዱ እና የማኔጅመንት ውይይቱ በቃለ ጉባኤ ስለመያዙ፣ ...................................-------------------------------------------------------15

የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት ስለመቋቋሙ፣ ፈቃድ ሲሰጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይሁንታ ስለመጠየቁና ባለፈቃዶች በስራቸው ላይ የአከባቢ ጥበቃን ያገናዘቡ መሆኑን ሚ/ር መ/ቤቱ ስለማረጋገጡ17

ሚ/ር መ/ቤቱ በከበሩ ማዕድናት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው ግለሰቦች በህግ መሰረት መስራታቸውን የሚያረጋግጥበትና የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣.20

የማዕድን ማምረት የፈቃድ ዘመን በማዕድን ስራዎች አዋጅ መሰረት ስለመሆኑ፣ ባለፈቃዶቹ በአንድ ዓመት ውስጥ የምርት ስራቸውን ስለመጀመራቸውና የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች ስለማክበራቸው፣......23

ለ. ሚኒስተር መ/ቤቱ በከበሩ እና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ላይ ለሚሰማሩ ባለፈቃዶች በወሰዱት ፈቃድ እና በገቡት ውል መሰረት እየሰሩ መሆኑን ለመከታተል የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የፍቃድ አስተዳደርና የቁጥጥር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ ..........................24

ፈቃድ ሰጪ አካላት የማዕድን ስራ እንቅስቃሴ መከታተላቸውን፣.......................................................24

መቆጣጠራቸውን፣ ማስተዳደራቸውንና ማረጋገጣቸውን በተመለከተ፣.......................................24

ባለፈቃዶች ወርቅና ብር ለብሄራዊ ባንክ እንዲያቀርቡ ቁጥጥር መደረጉ እና ስለሚስተናገዱበት ሁኔታ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፤..........................................................................28

የእደጥበብ ባለፈቃዶች ጥሬ ወርቅና ብር ከባንክ ብቻ እንዲገዙ ስርዓት በመዘርጋት ስለመከታተሉ ፣33

ፈቃድ ሰጪ አካላት ምርት ላይ የተሰማሩ ባለፈቃዶች የሚፈለግባቸውን ልዩ ልዩ ገቢ በወቅቱ መሰብሰባቸው፣ መመርመራቸው እና እርምጃ መውሰዳቸውን በተመለከተ፣ ......................................34

ሮያሊቲ በወቅቱ ባልከፈሉ፣ ሮያሊቲ ያልተከፈለበት ማዕድን በገዙ ግለሰቦች ላይ እርምጃ መውሰድን በተመለከተ፣ .........................................................................................................40

ሐ.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ የከበሩ ማዕድናትግብይትን ለማካሄድ አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ስለማግኘት እና ፈቃዱን ማሳደስ የሚችለው በየአንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ መሆኑን በተመለከተ፤ ...........................................................................................42

ፈቃድ ሰጪ አካላት በማዕድን ህጎች መሰረት የማዕድን ፈቃድ ስለማደሳቸው እና ግዴታቸውን ባልተወጡ ባለፈቃዶች ላይ እርምጃ መውሰዳቸውን በተመለከተ፣......................................................44

ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የወጪ ንግድና የጌጣጌጥ ማዕድናት በኮንትሮ ባንድ ንግድ እንዳይወጡ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣.........................................................48

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመወያያ መድረክ ያለው ስለመሆኑ፤ .........................................................51

ሚ/ር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ፤ ....................................52

ሚ/ር መ/ቤቱ ባለፈቃዶችን ለመከታተል የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ዘዴ ያለው ስለመሆኑ፣...................................................................................................................54

ወደ ውጭ አገር ለመሸጡ የማዕድናት ተመን ስለማውጣቱ እና ለባህላዊ ማዕድናት አምራቾች የቴክኒክ ድጋፎች መስጠቱን በተመለከተ.............. -----------------------------------------------------------------57

ሚ/ር መ/ቤቱ ባለፈቃዶች ያመረቱትን (የሸጡትን) የማዕድን ዓይነትና መጠን ለፈቃድ ሰጪው አካል የሚያሳውቁበት ስርዓት ዘርግቶ ስለመከታተሉ እና የእደ-ጥበብ ባለፈቃዶች ሪፓርት ስለማድረጋቸው60

ክፍል ሦስት.............................................................................................................64

የመደምደሚያ ሃሳቦች...................................................................................................64

ክፍል አራት ...........................................................................................................64

የማሻሻያ ሃሳቦች........................................................................................................68

አባሪ 1------------------------------------------------------------------------------------------------i

# መግቢያ

## የማዕድን ሚኒስቴር አመሰራረት

1. የማዕድን ኢንዱስትሪ ለአንድ ሀገር ከፍተኛ ዕድገት ሊያስመዘግቡ ከሚችሉት የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል አንዱ ሲሆን የኢትዮጵያ የማዕድን ሀብትም በአግባቡ እንዲለማና ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ እንዲችል የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡
2. በኢትዮጵያ ያለው የተለያዩ የአለቶች ቅንብር በዛ ላሉ ማዕድናት መፈጠር አመቺ በመሆኑ የኢንዱስትሪ ማዕድናት፣የኮንስትራክሽን ማዕድናት፣ብረት ነክ ማዕድናት፣የከበሩ ማዕድናት፣ በከፊል የከበሩ ማዕድናት እና የመሳሰሉ የማዕድን ሀብቶች ይገኛሉ፡፡
3. የማዕድን ምርት በማናቸውም አይነት ዘዴ በሚከናወን ሥራ በገፀ-ምድር፣ በከርሰ-ምድር ወይም በውሃ አካላት ከሚገኝ የማዕድን ክምችት ወይም ተረፍ የማዕድን ክምችት ውስጥ ለማውጣት የሚደረግ ሥራ ነው፡፡ እነዚህም ማዕድናት በባህላዊ፣በአነስተኛ ደረጃ እና በከፍተኛ ደረጃ ዜዴዎች የሚመረቱ ናቸው፡፡
4. የማዕድን ሥራ ከ1935 ዓ.ም. ጀምሮ እንደ አንድ የሥራ ዘርፍ ለበርካታ ዓመታት በተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ሲተዳደር ከቆየ በኋላ በሚኒስቴር መ/ቤት ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1958 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ የማዕድን ሥራ በተለያየ አደረጃጀት ተዋቅሮ ሲካሄድ የነበረ ሲሆን በ1968 ዓ.ም በሥራና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር፣ ከ1969ዓ.ም ጀምሮ በማዕድን፣ የኃይል ማመንጫና የውሃ ልማት ሚኒስቴር፣ ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ በማዕድንና ኃይል ምንጭ ሚኒስቴር፣ ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ በማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሥር ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ ከመስከረም 1994 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የማዕድኑ ዘርፍ በማዕድን ሚኒስቴር እንዲሁም የኢነርጂዉ ዘርፍ በመሰረተ ልማት እና በግብርና እና ገጠር ልማት ሚኒስቴር እንዲደራጅ ተደርጎ ነበር፡፡ ከጥቅምት 01 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሥር ተዋቅሮ ቆይቷል፡፡ በ2003 ዓ.ም በተደረገው የአስፈፃሚ አካላት የአደረጃጀት ለውጥ የማዕድን ሚኒስቴር ራሱን ችሎ እንደገና እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡
5. የማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚውን ለማስተዳደር የመጀመሪያው የህግ አንቀጽ የወጣው በ1963 ዓ.ም. ሲሆን የማዕድን አዋጅ ቁጥር 282/1963ን ተከትሎ ደንብ ቁጥር 396/1963 ወጥቷል፡፡ ማዕድንን በዘላቂ መንገድ ለማልማትና ለንግድ አላማ በማዋል ሀገርቷ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲትችል በቅርቡ የከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ ቁጥር 651/2001 አንዱ ሲሆን ሁለተኛው የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

6. በአዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀጽ 1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የክልል ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤቶች ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ከሚሰጣቸው የኮንስትራክሽንና የኢንዱስትሪ ማዕድናት የቅኝት፣ የምርመራና ይዞ የመቆየት ሥራ ፈቃዶች የባህላዊ ማዕድናት የማምረት ሥራ ፈቃዶች እንዲሁም የኢንዱስትሪ ማዕድናት አነስተኛ ደረጃ እና የኮንስትራክሽን ማዕድናት አነስተኛና ከፍተኛ ደረጃ የማምረት ሥራ ፈቃዶችን የመስጠት ኃላፊነት የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ከተጠቀሱት ጉዳዮች በስተቀር የሌሎች ማዕድናት ማለትም ለውጭ ባለሀብቶች የቅኝት፣ የምርመራ፣ ይዞ የመቆየት፣ የአነስተኛና የከፍተኛ ደረጃ የማምረት ሥራ ፈቃዶች የመስጠትና የማስተዳደር እንዲሁም የከበሩ እና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ከማዕድናት ዓይነት አንዱ እንደመሆኑ ይሄን ማዕድን ለንግድ አላማ ለማዋልና ንግዱን ለማስፋፋት እንዲያስችል ለባለሀብቶች ፈቃድ የመስጠት፣ የመቆጣጠር እና የማስተዳደር ሥራው በማዕድን ሚኒስቴር እንዲሆን ተደርጓል፡፡በዚህ መሰረት እነዚህ ስራዎችን በዋነኛነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ፈቃድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እና በባህላዊ ማዕድናት ምርትና ግብይት ማስተባበሪያ የሚከናወኑ ናቸው፡፡

**የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ** (Objective)

7. **የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማዎች፡-**

መንግስት የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት ለመጠበቅ የተጣለበትን ኃላፊነት ተግባራዊ ማድረግ፤

የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ማስፋፋት፤

የኢትዮጵያውያንን የስራ ዕድል ማስፋፋትና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማሳደግ፤

በማዕድን ምርመራና ማምረት ሥራ የተሰማሩትን ባለሀብቶች የይዞታ ዋስትና ማረጋገጥ እና፤

የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ሥርዓትና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ መልማቱን ማረጋገጥ፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

**የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ**(*Vision)*

8. ከ2012-2015 የማዕድን ሀብታችንን የውጪ ምንዛሪ አስተዋፅኦን በ10 እጥፍ ማሳደግና ለኢንዱስትሪው ልማት የጀርባ አጥንት መሆን ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

9. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በማቋቋሚያ አዋጁ መሰረት የተለያዩ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡ እነዚህም፡-

- የማዕድን ልማቱ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
- የማዕድንና ኢነርጂ መረጃዎችን በአግባቡ እንዲሰበሰቡ፤እንዲጠበቁና ለተጠቃሚዎች እንዲቀርቡ ያደርጋል፤
- ለማዕድን ፍለጋና ልማቱ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የማዕድን ኢንቨስትመንትን ያበረታታል፤
- ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይት ህጋዊ መስመር እንዲይዝ ያደርጋል፤
- የማዕድን ልማቱን ለማፋጠን የሚረዱ የምርምርና የማስልጠኛ ተቋሞችን እንደአስፈላጊነቱ ያደራጃል፤
- ስለዘርፉ ልማትና አጠቃቀም ፖሊስና ሕግ ያዘጋጃል፤
- በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች ፈቃድ ይሰጣል፤ በገቡት ውል መሰረትም ስራቸውን ማካሄዳቸውንና የክፍያ ግዴታዎቻቸውን መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል፤

የሚሉት ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀትና የሰው ኃይል

10. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ጽ/ቤት ሆኖ የሚመራው በተቋሙ የበላይ አመራር አካል ነው፡፡ በአንድ ሚኒስትር፣ በአንድ ሚኒስትር ዴኤታ፣ በአንድ በሚኒስቴር ጽ/ቤት የጠጣር ማዕድናት አማካሪ፣ በአንድ የሚኒስትር ሚ/ዴኤታ አማካሪ፣ በአስራ አራት (14) ዳይሬክቶሬቶች፣ እና በሶስት(3) ጽ/ቤቶች ተዋቅሯል፡፡በሚኒስትር ዴኤታው ስር አራት(4) ዳይሬክሬቶች ያሉት ሲሆን የማዕድን ፍቃድና አስተዳደር ዳይሮክትሬትም ከነዚህ ውስጥ አንዱ ነው:: ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በጠቅላላው 451 የሰው ዓይል እንዲኖረው የተፈቀደ ሲሆን ሚኒስትሩን እና ሚኒስትር ዴኤታውን ጨምሮ በባለስልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ በስራ ላይ ያለው የሰው ሀይል 279 (61.9%) ሲሆኑ በሚኒሰቴር መ/ቤቱ በስራ ላይ ካሉት 279 ሰራተኞች ውስጥ 171 ወንድ እና 108 ሴት ሠራተኞች ያሉት ሲሆን በትምህርት ደረጃ ሲተነተን፡- 2 ፒኤች ዲ (ዶ/ር)፣ 26 በማስተርስ ዲግሪ፣ 102 የመጀመሪያ ዲግሪ፣ 40 ዲፕሎማ፣ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ እና ከ12ኛ ክፍል በታች የሆኑ 96 እንዲሁም 13 ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሰራተኞች ያሉት መሆኑን ከሰው ሀብት ልማትና ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ከተሰበሰበ መረጃ ለማውቅ ተችሏል፡፡

### የሚኒስቴር መ/ቤቱ   የፋይናንስ ምንጭ


11. የማዕድን ሚኒስቴር ስራውን የሚያከናውነው በመንግስት በሚመደብለት መደበኛና ካፒታል በጀት ሲሆን በ2004፣ በ2005 እና 2006 በጀት ዓመታት እንደየቅደምተከተሉ ከመንግስት የተመደበለት መደበኛ በጀት ብር18,170,400፣ ብር 23,584,320 እና ብር25,846,030 ናቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ በ2004 ዓ.ም ብር 17,008,582.5(94%)፣ በ2005 ዓ.ም ብር 21248218.13 (90%)፣ እንዲሁም በ2006 ዓ.ም ብር 21,860,163.16(85%) ስራ ላይ አውሏል፡፡
12. ከዚህ በተጨማሪም ለዚሁ ስራ የተፈቀደለት በ2004፣ በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመታት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ በቅደም ተከተሉ መሰረት ብር 81,927,000፣ 42,726,000 እና 64,720,000 ካፒታል በጀት ተፈቅዶለት 36,622,419.57(45%) ፣42,710,853.76 (99.9%) እና እስከ ሰኔ /2006 ዓ.ም 87,417,068.60 (135%)) ስራ ላይ ውሏል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ  የስራ ሂደት መግለጫ


### የማዕድን ፈቃድና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

13. የአገሪቱንና የአለም አቀፉን የማዕድን ምርት ፍላጎት በመከተል የኢንቨስትመንት አቅጣጫዎች የማረጋገጥ ልማታዊ ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ ፈቃድ የመስጠት፣ የመከታተልና እገዛ የማድረግ፣ የልማት መረጃዎች የማስተዋወቅ፣ ከማዕድን የሚገኘው ልዩ ልዩ ገቢ የማሰባሰብና የማሳወቅ ሥራዎችን በዋናነትያከናውናል፡፡


## 14.የማዕድን ፍለጋ/ምርመራ ሥራ ፈቃድ  የሥራ ፍሰት



## 15.የማዕድን ምርት ሥራ ፈቃድ የሥራ ፍሰት




## 16.የተመረጠው የማዕድን ፍለጋ/ምርመራና ምርት ፈቃድ ክትትል ቨርሽን የሥራ ፍሰት ካርታ (Process Map)




## የባህላዊ ማዕድናት ምርትና ግብይት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት

17. የተጀመረው ወርቅና ሌሎች ጌጣጌጥ ማዕድናት ለብሔራዊ ባንክና ለውጪ ገበያ የማቅረብ ስራ ቀጣይነት እንዲኖረው ከሚመለከታቸው ጋር በቅንጅት በመስራት አምራቾች እንዲደራጁ በማድረግና የቴክኒክና የማምረቻ መሳሪያዎች እንዲያገኙ በመደገፍ ፍትሀዊ የሆነ የገበያ ሥርዓትን የመዘርጋት ሥራዎችን በዋናነት ያከናውናል፡፡



## የፔትሮሊየም ፈቃድና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

18. የአገሪቱ የፔትሮሊየም እምቅ ሀብት በኩባንያ ያልተያዙትን በመለየት የኮንትራት ጉዳዮችንና የፔትሮሊየም ህጎችን ለኢንቨስተሮች ማስተዋወቅ፣ የኩባንያ ጥያቄዎችን በመገምገም ፈቃድ የመስጠት የመከታተልና እገዛ የማድረግ ከፔትሮሊየም ፍለጋ የሚገኘውን ልዩ ልዩ ገቢ የማሰባሰብና የማሳወቅ ሥራዎችን በዋናነት ያከናውናል፡፡



## የኦዲቱ ዓላማ

19. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የማዕድን ሚኒስቴር በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ማምረት እና ግብይት የሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው ባለፈቃዶች ፣ የማእድን ምርትን ለማስተዳደር እና ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጡ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እነዲሁም በወሰዱት ፍቃድ እና በገቡት ውል መሰረት ስለመስራታቸው መከታተሉን ፣ መቆጣጠሩን ፣ ድጋፍ መስጠቱን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን ፣ የማዕድን ምረትና ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በመገምገም በአግባቡ መወጣቱን እና አፈፃፀሙ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

20. ኦዲቱ የሚከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡"" ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2004 በጀት ዓመት እስከ 2006 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ፈቃድ አስተዳደር፣ ግብይትና ቁጥጥር አፈፃፀምና ውጤታማነት ዙሪያ የተሠሩትን ሥራዎች ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በማዕድን ሚኒስቴር ሲሆን፣በክልሎች ካሉት የማዕድን ቢሮዎች ውስጥ በኦሮሚያ፣በደቡብ እና በትግራይ ያሉትን የማዕድን ቢሮዎች/ኤጀንሲዎችን እና ሁለት የብሄራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ ጣቢያዎችን በናሙና መርጦ በማየት፣ የተለያዩ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን ለባለድርሻ አካላትና ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና የተለያዩ የኦዲት ማስረጃዎችን በመሰብሰብና በመከለስ ነው፡፡

21. በዚህም መሰረት በናሙና ለተመረጡ 15 በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ማምረትና ግብይትን በተመለከተ የስራ ፈቃድ የተሰጣቸው አምራቾች፣አዘዋዋሪዎች እንዲሁም ከእደጥበባት ባለፈቃዶች ጋር በአካል በመገኘት መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ ማስረጃዎችን በመከለስና ለኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

22. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ፈቃድ አስተዳደር፣ ምርት፣ግብይትና ቁጥጥር አፈፃፀምና ውጤታማነትን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች

23.ከላይ በተገለፀው የኦዲት አካባቢ ሶስት ዋና  የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን በመጀመሪያው የትኩረት አቅጣጫ ሥር ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የከበሩና በከፊል የከበሩ የማዕድን ሀብቶችን በማዕድን አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎችና አሰራሮች መሰረት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማስተዳደሩንና መቆጣጠሩን መገምገም፣
   - 1.1. ሚኒስተር መ/ቤቱ በከበሩ እና በከፊል በከበሩ መዕድናት ላይ ለሚሰማሩ ባለፈቃዶች በወሰዱት ፈቃድ እና በገቡት ውል መሰረት እየሰሩ  መሆኑን ለመከታተል የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የፍቃድ አስተዳደርና የቁጥጥር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡
   - 1.2 ሚንስቴር መ/ቤቱ በከበሩ እና በከፊል በከበሩ ማዕድናት  ልማት ላይ የተሰማሩ ባለፈቃዶች የሚፈለግባቸውን ልዩ ልዩ ገቢ በወቅቱ ገቢ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፡፡
2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡
3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሀብት አስተዳደር፣ ግብይት ክትትል እና ቁጥጥርን ቀልጣፋና ውጤታማ  ለማድረግ የሚያስችል ከክልሎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ፣ ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ እና ባለፈቃዶችን ለመደገፍ የሚያስችል ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

24.በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሶስት ዋና ዋና የኦዲት  የትኩረት  አቅጣጫዎች እና ሁለት ንዑስ የትኩረት  አቅጣጫዎችን  ለመመዘን የሚረዱ 33 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡  የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ ለማዕድን ስራዎች እና ለከበሩ ማዕድናት ግብይት የወጡ አዋጆች እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ የአፈፃፀም መመሪያዎች፣ መፃፃፎች /correspondence letters/  እና

መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ቀርቦ አስተያት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ተያይዘዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

**ሀ. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የከበሩና በከፊል የከበሩ የማዕድን ሀብቶችን በማዕድን አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎችና አሰራሮች መሰረት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማስተዳደሩንና መቆጣጠሩን በተመለከተ፣**

***በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወጡት አዋጆች፣ ደንቦች እና የአፈፃፀም መመሪያዎች መዘጋጀቱን በተመለከተ፣***

25. የሚኒስቴር መ/ቤቱን ስልጣንና ተግባር አስመልክቶ ለወጡት አዋጆች የማስፈፀሚያ ደንብ እንዲወጣላቸው ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ እና የቀድሞውም ስራ ላይ እንዲውል አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም ለከበሩና በከፊል ለከበሩ ማዕድናት ምርት እና ግብይትን ለማስፋፋት፣ ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር የወጡ አዋጆች እና ደንቦችን መሰረት አደርጎ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአዋጅ ቁጥር 651/2001 እና 678/2002 የማስፈፀሚያ ደንብ አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል በወቅቱ እንዲፀድቅ አላደረገም፡፡በአሁን ወቅት በስራ ላይ ያለው የማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 182/1986 ከአዋጅ ቁጥር 678/2002 በፊት የወጣና በተጠቀሰው አዋጅ የተደነገገው ዋና ዋና ጉዳዮች የሚያካትት በግልፅና በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ዝርዝር ማብራሪያዎች ባለመኖራቸው በአፈፃፀም ላይ ችግር እየተፈጠረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብና በትግራይ ክልሎች በታዩት 3 /ሶስት/ የክልል ማዕድን ቢሮዎች/ኤጀንሲዎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ላይ ለአዋጅ ቁጥር 651/2001 ደንብ ባለመውጣቱ በአዘዋዋሪዎች ላይ ስለሚጣለው ቅጣት በዝርዝር ስላልተመለከተ በስራላይ ክፍተት መፍጠሩን እና የማዕድን ስራዎችንና ፈቃድ ለማስተዳደርና ባለፈቃዶችን ለመቆጣጠር እንዳልተቻለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. በተጨማሪም ለአዋጅ ቁጥር 651/2001 ደንብ ባለመውጣቱ የፈቃድ ክፍያዎች መጠን፣ የአሰራር ደረጃዎች፣ የማጣሪያ ደረጃዎች፣ የስሚዘሪና ላፒደሪ ስራዎችን ደረጃ /standard/፣ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስፈርቶች /requirements/፣ የቴክኒክ ደረጃዎች፣ዳታዎች በመግለፅና በማያሻማ ሁኔታ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተጠያቂነትን የሚያጠናክር አሰራር

ተግባራዊ ለማድረግ እንዳላስቻላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ፈቃድ ከማስተዳደር አኳያ ፈቃድ ያገኙ አካላት ግዴታቸውን ሳይወጡ ሲቀሩ መቼና ምን ዓይነት ቅጣቶች (ፈቃድን እስከ መሰረዝ ድረስ) ሊወሰድባቸው እንደሚገባ የተቀመጠ ግልፅ አሰራር እንደሌለ ታውቋል፡፡

29. እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 651/2001 እና 678/2002 ላይ አንድ ጥፋት ያጠፉን ግለሰብ (ህገወጥ የማዕድናት አምራችና የወርቅ ጠቋሚ ማሽን አዘዋዋሪዎች) እና ዘግይተው ፈቃድ ለማሳደስ የሚመጡ ባለፈቃዶች ምን መቀጣት እንዳለባቸው፣ የወርቅ አቅላጭ ባለፈቃዶች መነሻ ካፒታል ምን ያህል መሆን እንዳለበት፣ ባለፈቃዶች ከአነስተኛ ወደ ከፍተኛ ወይም ከባህላዊ ወደ አነስተኛ እንዲሸጋገሩ ምን ዓይነት መስፈርት ማሟላት እንዳለባቸው፣ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት(የአዘዋዋሪ ፈቃድ) ለመስጠት፣ ለማደስ እና ለሌሎች የማዕድን ስራዎች የሚጠየቀው የክፍያ መጠን (Rate) ምን ያህል መሆን እንዳለበት በግልፅ የሚያመላክት አሰራር የለም፡፡ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 678/2002 ላይ የአከባቢ ጥበቃን በተመለከተ ባለፈቃዱ ፈንድ መመደብ እንዳለበት፣ ባለፈቃዱ የማህበረሰብ እድገት (community development) ላይ መሳተፍ እንዳለበት እንዲሁም አንድ ባለፈቃድ ወደ ውጭ የሚላኩ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ናሙናዎች መውሰድ እንዳለበት ቢገለፅም፤ የሚከፈለው የፈንድ መጠን እና ወደውጭ ስለሚላከው የማዕድናት ናሙናዎች መጠንን የኪሎ ግራም ግምት አስመልክቶ እነዚህን ጉዳዩች በማብራራት ለመግለፅ ያስችሉ የነበሩት ደንብና ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎች ባለመኖራቸው በአሰራር ላይ ከፍተኛ ችግር ማስከተሉ ታውቋል፡፡

30. በተጨማሪም የማዕድን ሚኒስቴር ለከበሩና በከፊል ለከበሩ ማዕድናት ምርት እና ግብይት አስተዳደር የወጡ አዋጆች እና ደንቦችን መሰረት አደርጎ ዝርዝር የአፈጻጸም መመርያ አለማዘጋጀቱ ታውቋል፡፡

31. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የህግ ጉዳይ የሥራ ኃላፊ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መግለጫ ለአዋጅ ቁጥር 651/2001 ደንብ እንዲፀድቅለት ሚ/ር መ/ቤቱ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ አለመከታተሉን ተብሎ የተገለፀውን በተመለከተ ይህንን አዋጅ አስመልክቶ የተዘጋጀው ረቂቅ ደንብ በዜሮ ድራፍት ደረጃ ላይ ያለ መሆኑን በተጨማሪም ለአዋጅ ቁጥር 678/2002 ደንብ አለመውጣቱ ወይም ደንብ ቁጥር 182/1986 አለመሻሻሉንም በተመለከተ አዋጁን መሰረት ያደረገ ደንብ ለማዘጋጀት የደንቡ ረቂቅ ከሁለት ዓመት በፊት የተዘጋጀ መሆኑንና በቅርቡም ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለመላክ እየሰሩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

32. በአዋጁ ግልፅ ያልሆኑትም ጉዳዮች የተዘጋጀው ረቂቅ ደንብ ተጠናቆ ዝርዝር መመሪያዎች ሲዘጋጁ የበለጠ ግልፅ እንደሚያደርገው አስረድተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በረቂቅ ደረጃ የማዕድን ስራዎችንና ግብይቱን አስመልክቶ ስለሚዘጋጁ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን አስመልክቶ በማዕድን ህጎቹና በጠቅላላ ህጎች ላይ በቂ ግንዛቤ ያለው ባለሙያና በልዩ ጥንቃቄና ችሎታ ሊዘጋጅ የሚገባ ቢሆንም በ2007ዓ.ም ስራ ሲታቀድ በነበረበት ወቅት የነበሩ ባለሙያዎች መ/ቤቱን በመልቀቃቸው ሌሎችም ደግሞ አዲስ ተቀጣሪዎች በመሆናቸው የደንቡን ረቂቅ የማዳበር ስራ መስራትም ሆነ ለአዋጆች መመሪያን የማዘጋጀት ስራ በዕቅዳቸውና ባስቀመጡት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለመተግበር የማይችሉባቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

33. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አዋጁ ግልፅ አይደለም ለሚለው በሕግ ባለሙያ ዓይን ሲታይ አዋጁ ከአዋጅ ደረጃ እራሱ ወረድ ያለና ዝርዝር ሁኔታዎችን ደንብ በሚመስል መልኩ ያካተተ ሆኖ እንደሚያዩት ነገር ግን ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮች ካሉም በባለሙያ ታይቶ መተርጎም እንደሚኖርባቸው እንዲሁም ለአዋጁ መመሪያዎች አልተዘጋጁም ለሚለው መመሪያዎች መዘጋጀት ያለባቸው ለአዋጁ የተዘጋጀው ረቂቅ ደንብ ዳብሮ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በኃላ መሆን ስላለበት የግድ የደንቡን መጠናቀቅ መጠበቅ እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

34. ይህም በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት በታዩት 3 የክልል ማዕድን ቢሮዎች እና በዞኖችና ወረዳዎች እንዲሁም በባለድርሻ አካላት ከላይ በተጠቀሱ ምክንያቶች በስራ ላይ የአፈፃፀም ችግር እንዳስከተለባቸውና ከባለፈቃዶች ጋር አለመግባባት የፈጠረባቸው መሆኑንና ህገወጥ የማዕድን አምራችና አዘዋዋሪ ግለሰቦች ላይ እርምጃ ለመውሰድም ሆነ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ እንዳላስቻላቸው የክልል ማዕድንና ኢነርጂ /ቢሮ/ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

35. ለአዋጆቹ የአፈፃፀም ደንብ እና መመሪያዎች ባለመዘጋጀታቸው በሚ/ር መ/ቤቱ እና በክልል ማዕድን ቢሮዎች እንዲሁም በባለድርሻ አካላት መካከል የአዋጁ አፈፃፀም ላይ ክፍተት የፈጠረ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

<u>በዕቅድ ክንውን ሪፖርት ላይ ለሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶች እርምጃ ስለመወሰዱ እና የማኔጅመንት ውይይቱ በቃለ ጉባኤ ስለመያዙ፣</u>

36. ሚ/ር መ/ቤቱ በየበጀት ዓመቱ በሚያዘጋጀው ዕቅድና የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች ለሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶች ወቅታዊ የስራ ክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ በማድረግ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ እንዲሁም መደበኛና ተከታታይ የስራ አመራር /የማኔጅመንት/

የውይይት መድረክ እንዲኖር በማድረግ በውይይቱ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በቃለ ጉባኤ በአግባቡ በመያዝ ጠንካራ የስራ አፈፃፀም ማሻሻያ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

37. ይሁን እንጂ ሚ/ር በመ/ቤቱ በየበጀት አመቱ በሚያዘጋጀው ዕቅድና የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ለሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶችን መሰረታዊ ምክንያታቸውን ለመለየት የሚያስችል ጠንካራ የስራ ክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ ስርዓት የሌለው መሆኑ፣

38. እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 30/07/2006 ዓ.ም የሚ/ር መ/ቤቱን አጠቃላይ የሥራ ሁኔታን አስመልክቶ ለሚካሄደው የማኔጅመንት ስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎች እንደማይያዙ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች በሰጡት መግለጫ ታውቋል፡፡

39. በ2004 ዓ.ምና በ2005 ዓ.ም 65 የማዕድን ምርት ፈቃዶችን በመስክ ለመከታተልና ለመደገፍ ታቅዶ በቁጥር 33 (50.7%) ብቻ ክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸው መሆኑ፣ ኢኮኖሚያዊ ማዕድናትን ወደ ውጪ ለመላክ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ድጋፍ መስጠት በቁጥር 36 ታቅዶ ለ8ቱ (22.2%) ብቻ ድጋፍ የተሰጠ መሆኑ እንዲሁም በ2004 እና በ2005 የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ለብሄራዊ ባንክ የቀረበው የወርቅ መጠን እንደቅደምተከተላቸው 27%ና 54 % እና በ2006 ዓ.ም ደግሞ የትግራይ 44.5%፣ የጋምቤላ 42%፣የቤንሻንጉል 32.87%ና የደቡብ 20.53% በመሆኑ የወርቅ ዕቅድ አፈፃፀማቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ከማዕድን ሚ/ር በተገኘው ዓመታዊ የዕቅድና ክንውን ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

40. ከዚህም በተጨማሪ በሚ/ር መ/ቤቱ በ2004 ዓ.ም ለታቀደው ዕቅድ ሁለት ዓይነት የአፈፃፀም ሪፖርቶች ያዘጋጀ በመሆኑ ምክንያት የአፈፃፀም ሪፖርቶችን በኦዲት ወቅት ለመገምገም አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ እንዲሁም የ2004ዓ.ም ዕቅድና አፈፃፀም ከ2005 ዓ.ም ዕቅድና አፈፃፀም ጋር ሲገመገም በይዘትም ሆነ በቁጥር አንድ አይነት መሆናቸው ታውቋል፡፡

ስለጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የዕቅድ ዝግጅትና ግምገማ ዳይሮክተሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ ባቀረበው መግለጫ ለታየው የዕቅድ አፈፃፀም ማነስ ዋነኛው ምክንያት በሚ/ር መ/ቤቱ በነበረው ከፍተኛ የሰራተኛ ፍሰት ምክንያት መሆኑን ገልፀው በክልሎችም የሚመረተው ወርቅን በተመለከተ አፈፃፀሙ አነስተኛ የሆነው በተጠቀሱት ክልሎች የዘርፉ ተጠሪ መ/ቤቶች መዋቅራዊ ይዘት ባለመጎልበቱ እና የቅንጅት ስራዎችን በጋራ ለመስራት የተደረገው ጥረት እንደተፈለገው ውጤት ባለማሳየቱ መሆኑን አስረድተው የ2004ና 2005ዓ.ም የዕቅድና አፈፃፀም መመሳሰልን በተመለከተ ከላይ የተገለፀውን አስተያየት በግብዓት በመውሰድ ለወደፊቱ በስራ ላይ እንደሚያውሉት የገለፁ መሆኑን፤

41. ለማኔጅመንት ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤ አለመኖሩን በተመለከተ በግምገማ ላይ የሚሳተፉ የማኔጅመንት አባላት በግምገማ ወቅት የሚነሱ ጉዳዮችን በራሳቸው ማስታወሻ በመያዝና የሚተላለፉ ውሳኔዎችንም ተፈፃሚ እንዲሆን ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በየስራ ክፍሉ ሳምንታዊ ስብሰባዎች እየተካሄዱ ስራዎች ተገምግመው ቃለጉባኤዎች በየስራ ክፍሎች ውስጥ የሚቀመጡ መሆኑንና ማኔጅመንት ስብሰባ ላይ ለውይይት እና ለስራዎቹ ቅድሚያ በመስጠት የግምገማ ቃለጉባኤዎች ያልተያዙ መሆኑንና በቀጣይ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ቃለ-ጉባኤዎችን በመያዝ መረጃው ተጠናክሮ እንዲቀመጥ የሚያደርጉ መሆኑን የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

42. በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሚ/ር መ/ቤቱ ሁለት ዓይነት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች አሉት ለተባለው መ/ቤቱ ሁለት ዓይነት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች እንደሌሉት ሆኖም ግን በመ/ቤቱ ለኤክስፐርት አስተባባሪ ኮሚቴው በዘርፍ ደረጃ የሚላክ በመኖሩ እንደ ሁለት የተወሰደ እንዳይሆን በማለት የገለፁ መሆኑ እንዲሁም መ/ቤቱ የተለያየ ቃለ ጉባኤ ያለው ቢሆንም መረጃዎችን የማደራጀትና የማሰባሰብ ችግር መኖሩ በመታወቁ ስብስባዎችና ሌሎች ለክዋኔ ኦዲቱ በተቀናጀ መልኩ ለመጀር በማኔጅመንት ከ2007ዓ.ም ጀምሮ የተወሰነ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

43. ይሁን እንጂ የዕቅድ አፈፃፀም ማነስ ዋነኛው ምክንያት በሚ/ር መ/ቤቱ በነበረው ከፍተኛ የሰራተኛ ፍሰት መሆኑ ቢገለፅም ይህንን ስራ ለማከናወን ከ2004-2006ዓ.ም የተፈቀደው በጀት ከፍተኛ ቢሆንም ስራው በዕቅዱ መሰረት አለመሰራቱን ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ 2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/07/2006 ዓ.ም የስራ አፈፃፀምን ለመገምገም የተደረጉ የማኔጅመንት ስብሰባዎች ለኦዲት ቡድኑ እንዲቀርቡ በተደጋጋሚ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

**<u>የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት ስለመቋቋሙ፣ ፈቃድ ሲሰጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይሁንታ ስለመጠየቁና ባለፈቃዶች በስራቸው ላይ የአከባቢ ጥበቃን ያገናዘቡ መሆኑን ሚ/ር መ/ቤቱ ስለማረጋገጡ</u>**

44. ሚኒስቴር መ/ቤቱን የሚያማክር የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት ሊቋቋም እና የማዕድን ማምረት ፈቃድ ሲሰጥ በቅድሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይሁንታ በመጠየቅ ሊሆን እንዲሁም የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ባለፈቃዶች የሚያካሂዱቸው የማዕድን ስራዎች የአከባቢ ጥበቃን ያገናዘቡና ለማኅበረሰቡ ለአካባቢ ልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

45. በአዋጅ ቁጥር 678/2002 ሚ/ር መ/ቤቱን የሚያማክር የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት መቋቋም እንዳለበት ቢደነገግም እስካሁን ሚኒስቴር መ/ቤቱን የሚያማክር የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት አለመቋቋሙ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን ይዞና ተናቦ ለመስራት አለማስቻሉን፣ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የተመረጡ የክልል ማዕድን ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

46. ከሚ/ር መ/ቤቱ ፈቃድ ካገኙ ከአምስት የከበሩ ማዕድናት አምራች ባለፈቃዶች ውስጥ ሚ/ር መ/ቤቱ ለ3ቱ (60%) ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ይሁንታ ማግኘታቸውን ስለማረጋገጡ በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት የተገኘ ማስረጃ የለም፡፡

47. ስለ ጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት ማቋቋምን በተመለከተ ለአዋጅ ቁጥር 678/2002 ደንብ እንዲዘጋጅ በቅርቡ ለፍትህ ሚኒስቴር የተላከ መሆኑንና ደንቡ ሲፀድቅ በደንቡ መሰረት እንደሚቋቋም እንዲሁም ከሚኒስትሮች ምክር ቤት የይሁንታ ፈቃድ ያላገኙ ሶስቱ ባለፈቃዶችን በተመለከተ ሶስቱ ባለፈቃዶች ከመንግስት ወደ ግል ባለፈቃድ የተዛወሩ እና ከክልል ፈቃድ የተሰጣቸው ድርጅቶች /አምራቾች/ በመሆናቸው ምክንያት ከሚኒስትሮች ምክር ቤት የይሁንታ ፈቃድ የተጠየቀበት ማስረጃ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

48. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ባለፈቃዶች የሚያካሂዱቸው የማዕድን ስራዎች የአከባቢ ጥበቃን ያገናዘቡና ለማኅበረሰቡ አካባቢ ለልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን በተሟላ መልኩ አያረጋግጥም፡፡

49. በኦዲቱ ወቅት በታዩት በኦሮሚያ፣በደቡብ እና በትግራይ ክልሎች በባህላዊ መንገድ ለረጅም ዓመታት ወርቅ ሲመረቱባቸው የነበሩ የተጐሣቆሉና መልሶ የማቅናቱ ሂደት ያልተከናወነባቸው ሰፊ ቦታዎች መኖራቸው (ለምሳሌ፡- በደቡብ ክልል ወደ 81 ጉድጓዶች)፣ የከበሩ ማዕድናት የሚያመርቱ አምራቾች ባለፈቃድ እና ህገወጥ ግለሰቦች ወርቅ ለማግኘት ብለው በአብዛኛው ጉድጓዶችን ቆፍረው እንደ ማይደፍኑ እና አከባቢውን እንደማያለሙ ከባለፈቃዶቹ፣ ከወረዳው ማዕድን ቢሮ እና ከክልል ማዕድን ቢሮዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ እና በኦዲቱ ወቅት ከክልሎች በተገኙ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

50. የለገደንቢ የወርቅ ማምረቻ (መቆፈሪያ) አከባቢ ሁለት የማምረቻ ስፍራ (open pit and underground gold mining) ያለው ሲሆን ስራው የተጀመረው በ1989 ዓ.ም በመሆኑ በዚህ አከባቢ (open pit gold mining) በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ጉድጓዶችን ደፍኖ ሳር የመትከል ስራ ቢጀመርም የኦዲት ቡድኑ የመስክ ምልከታ እስካደረገበት (29/02/2007 ዓ.ም) ወርቅ ተቆፍሮ የወጣበት ሌሎች ቦታዎች ላይ የማልማት ስራው ያልተጀመረ መሆኑ፣

51. ስለጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የአከባቢና የማህበረሰብ ልማት ዳይሮክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በከፍተኛ ደረጃ ማዕድናት የሚመረቱባቸው አከባቢዎችን ሚ/ር መ/ቤቱ ዕቅድ ይዞ የአከባቢ ጥበቃን ያገናዘቡና ለማኅበረሰቡ የአካባቢ ልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን፣ ማረጋገጥ መጀመራቸውን ገልፀው ሆኖም ግን በባህላዊ ደረጃ ያሉትን ለመስራት በ2007 ዓ.ም በዕቅድ አካተው ለመስራት ሃሳቡ እንዳለቸው ገልፀዋል፡፡

52. ስለጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በባህላዊ መንገድ ወርቅ የሚያወጡ ባለፈቃዶች ፈቃዳቸውን የሚያገኙት ከክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ሲሆን የአካባቢ ልማት አያያዝን በተመለከተ ቁጥጥር የሚያደርገው የክልሉ አካባቢና መሬት አስተዳደር በመሆኑ ይህም ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከተው ክልሎችን ቢሆንም ከዘርፍ አንጻር ሲታይ ግን ሚ/ር መ/ቤቱ የትብብርና ድጋፍ ሥራዎችን ከክልሎች ጋር እየሠራ መገኘቱን እና ለወደፊቱ ከብዙ ዓመታት በፊት ማዕድናት ሲመረትባቸው የቆዩ ቦታዎችን መልሶ ለማቅናት ከክልሎች ጋር የሚተገበር ፕሮጀክቶችን ለመቅረጽ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንና በዚህ በጀት ዓመትም በሁለት ክልልሎች ላይ አካባቢንና የሙያ ጤንነትና ደህንነት ላይ ሥልጠና እንደሚሰጡ የገለፁ መሆኑን፤ የለገደንቢ ወርቅ ማምረቻን በተመለከተ በተወሰኑ ወርቅ የተመረተባቸው ቦታዎች ላይ የማልማት ስራ የተሰራባቸው ሲሆን፣ አሁን ግን ማዕድኑም እያለቀ በመሆኑ የማዕድን ማውጣት ሥራው ከመጠናቀቁ በፊት Mine closure plan ኩባንያው አጥንቶ በሚያቀርበው መሠረትና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በተስማማበት ሁኔታ ቦታው ለሌላ ልማት የሚውልበት ሁኔታ እንደሚያመቻቹ ገልጸዋል፡፡

53. በተጨማሪም በአዋጅ 678/2002 ላይ በተገለፀው መሰረት ማንኛውም ኩባንያ በማዕድን ምርመራና ምርት ለማህበረሰቡ አካባቢ ለልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን በተሟላ መልኩ መሥራት ሲሆን አፈፃፀሙ ከክልሎች ጋር በጋራ ድጋፍና የማስተባበር ሥራ እንደሚሠራ እንዲሁም የባህላዊ አምራች ባለፈቃዶች የሚያካሂዱቸው የማዕድን ሥራዎች የአካባቢ ጥበቃን ያገናዘቡና ለማህበረሰቡ የአካበቢ ልማት ኩባንያዎቹ በተቀናጀ መልኩ መሥራት ባይችሉም በክልሉ ባለው ደንብ መሥራት ግዴታ እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

54. እንዲሁም በአምራች ማህበራት/ባለፈቃድ/ የሚደረሱ የአካባቢ ጉዳቶች በተመከተ፣ በአዋጅ 678/2002ና በደንብ ቁጥር 182/1986 ባለውና በክልሎች ፈቃድ ሲሰጣቸው በገቡት ውል መሠረት ከምርት በኋላ መልሶ ማከም ግዴታ እንዳለባቸው እና በማዕድን ሚኒስቴር ድጋፍ ማድረግ፣ ማስተባበርና አጠቃላይ በሀገር ደረጃ መሰራት ስላለባቸው ጉዳዮች አሠራሮች ማውጣት ሲሆን ከክልሎች ጋራ በአካባቢ ጉዳይ ላይ በጋራ የድጋፍና የማስተባበር ሥራ ላይ

ያተኮረ መሆኑን፤ ሆኖም የተፈጠሩ ችግሮችን ለመቅረፍ ክልሎችና ሚ/ር መ/ቤቱ በጋራ ለመስራት በዕቅድ መንቀሳቀስ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

55. ይህም በመሆኑ የማዕድን አምራቾቹ በእርሻ ቦታዎችና በተፈጥሮ ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠሩ መሆናቸውን እና እርምጃ እንዳይወሰድባቸው ወርቁን ቆፍረው ካጡት ትተውት ስለሚሄዱ ባለፈቃዶቹን በቦታቸው ላይ ማግኘትም እንደማይቻል በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩት የክልል ማዕድን ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

56. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ማዕድናት የሚመረቱባቸው ቦታዎች ላይ አስፈላጊው የመልሶ ማልማት ስራ በወቅቱ እየተከናወነባቸው ባለመሆኑ የአካባቢ ተፅዕኖ እንደሚያስከትል ለመረዳት ተችሏል፡፡

**<u>ሚ/ር መ/ቤቱ በከበሩ ማዕድናት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው ግለሰቦች በህግ መሰረት መስራታቸውን የሚያረጋግጥበትና የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣</u>**

57. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከበሩ ማዕድናት የአዘዋዋሪነት እና የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው ግለሰቦች /ድርጅቶች/ ወደ ውጭ የሚልኳቸውንና የሚያዘዋውሯቸውን ጥሬ የከበሩ ማዕድናት የተገኘበትን ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እንዲያሳውቁ የሚያደርግበት እና የማዕድን ማምረትና የምርመራ ባለፈቃዶች ለማዕድን ሥራ ከውጭ ሀገር ከቀረጽ ነፃ ያስገቧቸውን ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች በትክክል ለማዕድን ሥራው ማዋላቸውን የሚያረጋግጥበትና የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

58. ሚ/ር መ/ቤቱ በከበሩ ማዕድናት የአዘዋዋሪነት እና የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው ግለሰቦች /ሰዎች/ ወደ ውጭ የሚልኳቸውንና የሚያዘዋውሯቸውን ጥሬ የከበሩ ማዕድናት ጥራትና መጠን የሚያመለክት የላብራቶሪ ውጤት የተገኘበትን ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውንና የከበረውን ማዕድናት ኘሮሰስ ያደረገውን ስምና የፈቃድ ቁጥሩን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እንዲያሳውቁ ስርዓት በመዘርጋት እንደማይከታተል ታውቋል፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት የታዩት ኦሮሚያ፣ ደቡብና ትግራይ እንዲሁም ማስረጃቸው ከሚ/መ/ቤቱ የተገኘው በኦሮሚያና በጋምቤላ ክልሎች የሚገኙ የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪነት ባለፈቃዶች የሚያዘዋውራቸውንና ለባንክ ወርቅ ሲያስገቡ በማዕድን አዋጁ መሰረት የከበሩ ማዕድናትን ሕጋዊ ምንጭና አከባቢያቸውን ለፈቃድ ሰጪ አካላት እንደማያሳውቁ ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የከሬንሲ ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የወርቅ አዘዋዋሪዎች ከየት ክልል እንደመጡ ህጋዊ ምንጫቸውን መጠየቅን በተመለከተ በብሄራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ደንበኛው ከየት ክልል እንደመጣ የሚጠየቅ መሆኑን ቢገልፁም ለኦዲት ቡድኑ በወቅቱ የሚጠይቁበትን ማስረጃ ለማቅረብ አልቻሉም፡፡ እንዲሁም በሀዋሳ የብሄራዊ ባንክ ቅርንጫፍ ወርቅ አቅራቢዎች (አዘዋዋሪዎች) ለመሸጥ ወደ ባንኩ ሲመጡ ወርቁ የተገኘበትን ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውን እንደማያሳውቁ፣ ይህም የሆነው የብሄሪዊ ባንክ እንዲጠይቁ መመሪያ ባለመተላለፉ መሆኑን የሀዋሳ ብሄራዊ ባንክ የወርቅ መቀበያ ጣቢያ የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

61. ከዚህም ጋር በተያያዘ በአዋሳ ብሄራዊ ባንክ ወርቅ የሚያቀርቡ ከደቡብና ከኦሮሚያ ክልል ቢሆንም ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ እንደተገለፀው ባንኮች ወርቁ የመጣበትን ህጋዊ ምንጭ ከባለፈቃዶች ጠይቀው መረጃውን መያዛቸው ሲታይ ሃዋሳ ብሄራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ ጣቢያ 221 ባለፈቃዶች የሚሆኑ ወርቅ ሲያቀርቡ የነበሩ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በቋሚነት በግምት ከ 20 እስከ 30 ባለፈቃዶች በማቅረብ ላይ የሚገኙ ሲሆን ባንኩ ከያዘው ከአዘዋዋሪዎች ፈቃድ ኮፒ ውጭ ከየት ክልል ወርቅ እንደሚያቀርቡ የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩንና በየጊዜው ባንኩም ተከታትሎ በመረጃ እንደማይዝ ለመረዳት ተችሏል፡፡

62. በዚህ ዙሪያ የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ባለፍቃዶችን በተመለከተ የላፒደሪ እና የላኪነት ፍቃድ ያላቸው ባለፈቃዶች በተጨማሪም ደረሰኝ የሌላቸውም ድርጅቶች ስላሉ ማዕድናቱ የተገኙበትን ህጋዊ ምንጫቸውን ወይም አካባቢያቸውን እንደማይሳውቁ፣ ይሄ ችግር መኖሩን እንደሚቀበሉ እና የከበሩ ማዕድናት አዋጅ ቁጥር 651/2001 ላይ የተቀመጠ ቢሆንም ብሄራዊ ባንክም ለክልል ማዕድን ቢሮዎች መረጃ እንደማይሰጥ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይም የክልል ማዕድን ቢሮዎችም ቅሬታ እንዳላቸው ነገር ግን ለወደፊት በክልልም ሆነ በማዕድን ሚኒስቴር የደረሰኝ ስርዓት በመዘርጋት መከታተል እንዳለበት እንዲሁም ጥሬ የከበሩ ማዕድናት ጥራትና መጠን የሚያመለክት የላብራቶሪ ውጤት ባለፈቃዶች አለማሳወቅን በተመለከተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ረጃ ይሄንን ችግር ለመቅረፍ እያንዳንዱ ክፍል ላይ ሚኒ-ላብራቶሪ ለማቋቋም ሀሳብ እንደነበራቸውና ከአቅም አንጻር እንዳልቻሉ ገልፀዋል፡፡

63. በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 መሰረት የማዕድን ማምረትና የምርመራ ባለፈቃዶች ለማዕድን ሥራ ከውጭ ሀገር ከቀረጥ ነፃ ያስገቧቸውን ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች በትክክል ለማዕድን ሥራው ማዋላቸውን የሚያረጋግጥበትና የሚከታተልበት

ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ ቢገለፅም ሚ/ር መ/ቤቱ በተሟላ መልኩ እንደማይከታተል ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. በማዕድን ህግ መሰረት እደጥበባት ከቀረጥ ነፃ መሣሪያዎችን ማስገባት የማይችሉ ቢሆንም ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ ሚ/ር መ/ቤቱ ለ2 የዕደ ጥበብ ባለፈቃዶች ድጋፍ ሰጥቶ መሳሪያዎችን እንዲያስገቡ ማድረጉ፣

65. እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ በመስክ ምልከታ በትግራይ /ብ/ክ/መ/ በተለያዩ ቦታዎች የማዕድን ምርመራ ሥራዎች የሚሠሩትን ባለፈቃዶች ለማዕድን ሥራ ከውጭ ሀገር ከቀረጥ ነፃ ያስገቧቸውን መሣሪያዎች በየፕሮጀክቱ ማግኘት አለመቻሉ የታወቀ ቢሆንም እርምጃ ስለመወሰዱና ለባለፈቃዶቹ ግብረመልስ ስለመላኩ በሚ/ር መ/ቤቱ ምንም ማስረጃ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

66. ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በማዕድን ሴክተሩ ኢንቨስተሮችን ማበረታታት እና ከቀረጥ ነጻ ተሽከርካሪዎችን እና መሳሪያዎችን ከውጪ ማስገባት እንደሚችሉ አዋጁ ቢፈቅድም መሳሪያዎቹ እና ተሽከርካሪዎቹ ለማዕድኑ ስራ መዋላቸውን በአንዳንድ ቦታ ላይ በመስክ መታየት እንዳለበት እንደአሰራር የተቀመጠ ቢሆንም ክትትል የተደረገበት በሪፖርት ደረጃ መኖሩን አረጋግጠው ማሰረጃውን እንደሚያቀርቡ፡፡ እንዲሁም የእደጥበብ ባለፍቃዶችን በተመለከተ በተለይም የስሚዘሪ ባለፍቃዶች ከ2004-2006 ዓ.ም. ለማበረታታት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቅዶ እንደነበር፡ ነገር ግን ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ከከለከለ በኋላ ግን እንደቀረ ገልፀዋል፡፡

67. ስለ ሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ህጋዊ ምንጭ ማሳወቅ የሚለው በአዋጅ 651/2001 አንቀፅ 18(2)(መ) ላይ የተቀመጠ መሆኑን ሆኖም ግን አምራቾች ደረሰኝ የሌላቸውና ግብይቱ በተለምዶ መሆኑንና በሌሎች ምክንያቶች የተፈጠሩ ችግሮች እንደሚታዩ፤ ይህንንም ለማስተካከልና አሰራሩን ህጋዊ ለማድረግ ከምርት ጀምሮ እስከ ግብይት ያለውን አሰራር ለማስተካከል ስለሚገባቸው በመሆኑ ፈቃድ ሰጪ ክልሎች በምርት ቦታ ባለሙያ እንዲመድቡ፣ ህጋዊ ደረሰኝ እንዲቆርጡና ሌሎች ስራዎች በጋራ ለመጀመር ሚ/ር መ/ቤቱ ዕቅድ ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑን፣

68. እንዲሁም ጥቂት ድርጅቶች /እሴት የሚጨምሩ እደጥበባት/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በማውጣት እንዲያመርቱ በተቀመጠው መሠረት ሚ/ር መ/ቤቱ ድጋፍ የማድረግ ስራ የሚሠራ ሲሆን ከላይ በኦዲቱ የተገለፁትን ድርጅቶች ባለማወቃቸው ትክክለኝነቱን ማረጋገጥ እንዳልቻሉ ሆኖም ግን መረጃዎች ሲገኙ እንደሚያጣሩ የገለፁ መሆኑንና በተጨማሪም በፌዴራል መ/ቤት የተሰጣቸው ፈቃድ ከቀረጥ ነፃ ያስገቧቸው ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች

በአብዛኛው በመስክና በቢሮ የሚጠቀሙባቸው በመሆኑ ምክንያት ለሥራ የገቡ ተሽከርካሪዎች የመስክ ወቅት ባልሆነ ጊዜ በመስክ ያለማግኘት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

69. ይሁን እንጂ ባለፈቃዶች ማዕድናቱ የተገኙባቸውን ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ባለማሳወቃቸው በክልል ለሚገኙ የማዕድንና ኢነርጅ/ቢሮዎች/ ላይ የስራ አፈፃፀም ክፍተት የፈጠረባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የማዕድን ማምረት የፈቃድ ዘመን በማዕድን ስራዎች አዋጅ መሰረት ስለመሆኑ፣ ባለፈቃዶቹ በአንድ ዓመት የምርት ስራቸውን ስለመጀመራቸውና የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች ስለማክበራቸው፣</u>

70. የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት የፈቃድ ጊዜ 20 ዓመት፣ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት የፈቃድ ጊዜ 10 ዓመት እና የባህላዊ ማዕድን የማምረት የፈቃድ ጊዜ 3 ዓመት ሊሆን እንዲሁም የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ የምርት ስራውን ሊጀምርና የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች ሊያከብር ይገባል፡፡

71. በማዕድን ስራዎች አዋጅ ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት የፈቃድ ጊዜ ከ20 ዓመት በላይ፤ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት የፈቃድ ጊዜ ከ10 ዓመት በላይ፤ እንዲሁም የባህላዊ ማዕድን የማምረት የፈቃድ ጊዜ ከ3 ዓመት በላይ መብለጥ የለበትም ቢልም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች ከፈቃድ ዘመናቸው በላይ ፈቃዱን ይዞ የመቆየት እና ወደሌላ የፈቃድ ደረጃ ያለመሸጋገር ችግርም መኖሩን ከነዚህም ውስጥ በደቡብ ፈቃድ ከወሰዱት 16 ባለፈቃዶች ውስጥ 15ቱ፣ በኦሮሚያ ከ65 ባለፈቃዶች ውስጥ 56ቱና በትግራይ ክልል 78 ባለፈቃዶች በአዋጁ መሠረት በባህላዊ የማምረት የፈቃድ ዘመናቸውን ጨርሰው ፈቃድ ያልመለሱ እንዲሁም የፈቃድ ዘመናቸው ከተጠናቀቀ በኃላ ወደሌላ የፈቃድ ደረጃ ሳይሸጋገሩ ከ9ወራት እስከ 11ዓመታት በማስቆጠር በፈቃዱ እንደተጠቀሙ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. በኦሮሚያ፣ በደቡብ እና በትግራይ ክልል ማዕድን ቢሮዎች በአነስተኛ የማዕድን ማምረት ወይም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ተሰጥቷቸው የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች በማክበር ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ የምርት ስራ ያልጀመሩ መኖራቸው ታውቋል፡፡ እንዲሁም ቀድሞ ሚ/ር መ/ቤቱ ፈቃድ ሰጥቶ ያስተዳድራቸው የነበሩ የወርቅ ማቅለጥ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያላቸው ባለፈቃዶች በ2004

ዓ.ም.  ለደቡብ ክልል 6 ባለፈቃዶች እና በ2006 ዓ.ም ለትግራይ ክልል 10 ባለፈቃዶች ፈቃድ እንዲሰጡና እንዲያስተዳድሩ በሚ/ር መ/ቤቱ ውክልና ቢሰጥም ከውክልናው ጋር የአፈፃፀም መመሪያ እና ደንብ አብሮ አለመላኩ፣

73. በዚህ ዙሪያ የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባሪያዊ ሁኔታ ላይ እንደገለጹት የባህላዊ የማምረት ፈቃድ የሚሰጠው በክልል በመሆኑና የፈቃድ ዘመናቸውን ጨርሰው ያልመለሱ ባለፈቃዶች መኖራቸው ግንዛቤ ተወስዶ ክልሎች እንዲያስተካክሉ መግባባት ላይ መደረሱን እንዲሁም በማዕድን አዋጅ የአምራቾችን ፈቃድ ማደስና ማቋረጥ የክልሎች መብት መሆኑን ሆኖም ግን 11 ዓመታት በማስቆጠር በፈቃዱ የሚጠቀሙ ባለፈቃዶች ስለመኖራቸው መረጃው ቢኖርም ከአዋጁ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ለማጣራት ሚ/ር መ/ቤቱ እንደሚከታተልና በቀጣይም መረጃ ከተገኘበት ከክልሎች ጋር በጋራ ለማስተካከል ጥረት እንደሚያደርጉ እና በማዕድን ሥራዎች ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 816/2013 የደቨሎኘመንት ጊዜ 2 ዓመት የተቀመጠ ቢሆንም የሚድሮክ ሳካሮ ምርት ፈቃድና የኢዛና ምርት ፈቃዶች ባጋጠማቸው የቴክኒክ ችግሮች መጀመር እንዳልቻሉና ይህንንም ሚ/ር መ/ቤቱ ድጋፍ በማድረግ ቶሎ ወደ ምርት የሚገቡበት ሁኔታ እያመቻቸ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

74. ይሁን እንጂ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ዘመንና የማዕድን ማምረት ሥራው የሚጀመርበት ጊዜ በማዕድን ስራዎች አዋጅ 678/2002 መሰረት  እየተከናወነ አለመሆኑ እና ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ እንዲያድጉ ትኩረት አለመሰጠቱ እንዲሁም ግዴታቸውንም ባልተወጡት ባለፈቃዶች ላይም እርምጃ አለመወሰዱ የማዕድኑ ሴክተር እንዳይጠናከር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ለ. ሚኒስተር መ/ቤቱ በከበሩ እና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ላይ ለሚሰማሩ ባለፈቃዶች በወሰዱት ፈቃድ እና በገቡት ውል መሰረት እየሰሩ  መሆኑን ለመከታተል የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የፍቃድ አስተዳደርና የቁጥጥር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

***ፈቃድ ሰጪ አካላት የማዕድን ስራ እንቅስቃሴ መከታተላቸውን፣ መቆጣጠራቸውን፣ ማስተዳደራቸውንና ማረጋገጣቸውን በተመለከተ፣***

75. የማዕድን ሚ/ርም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች ወደ ማናቸውም ክልል በመግባት በፈቃድ ክልላቸው ላይ ወይም ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የማዕድን ስራ እንቅስቃሴ ሊከታተሉና ሊቆጣጠሩ እንዲሁም ሚ/ር የማዕድን ስራዎች መካሄዳቸውን በማዕድን ደንቦች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎች እና አግባብ ባላቸው ስምምነቶች (በማዕድን ውል) መሠረት ሊያስተዳድርና ሊያረጋግጥ  ይገባል፡፡

76. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ የማዕድን ስራዎች መካሄዳቸውን በማዕድን ደንቦች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎች እንዲሁም አግባብ ባላቸው ስምምነቶች (በማዕድን ውል) መሰረት ፈቃዱን አለማስተዳደሩ፣ አለመቆጣጠሩና አለማረጋገጡ ታውቋል፡፡

77. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በማዕድን ስራዎች እና በከበሩ ማዕድናት ግብይትና ቁጥጥር ማስፋፊያ አዋጆች መሰረት የማዕድን ፍቃድ ያላቸው ባለፍቃዶች በየአመቱ ፍቃዳቸውን ማሳደስ እንደሚገባቸው እና ከአንድ አመት በላይ ፍቃድ ሳያሳድሱ የቆዮ ባለፍቃዶችን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመከታተል ፍቃድ እስከ መሰረዝ የሚደርስ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባው ቢገለጽም በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ፍቃዳቸውን ሳያሳድሱ በዘርፉ ላይ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች/ድርጅቶች ያሉ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች ሳይታደሱ የቆዩ ፍቃዶችን በመለየት ፍቃዶቹን የመሰረዝ እርምጃ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዳልወሰደ ታውቋል፡፡

78. ከዚህም ጋር በተያያዘ በክልሎች የከበሩ ማዕድናትን ሳያስረክቡ የሚያከማቹ፣ በባህላዊ ደረጃ ከተፈቀደላቸው መሳሪያ ውጪ የሚያመርቱ፣ ፈቃድ ሳይኖራቸው ከ1 ኪ.ግራም በላይ የከበሩና በከፊል ከበሩ ማዕድናትን የሚያመርቱና የሚሸጡ እና የሚያዘዋውሩ፣ ፈቃድ ሳያሳድሱ እና ከፈቃድ ዘመናቸው በላይ በመጠቀም እንዲሁም የመንግስት ገቢ ሳይፈፅሙ በስራ ላይ ያሉ ባለፈቃዶች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

79. በአዋጅ 678/2002 አንቀጽ 36 መሰረት በሚካሄደው የማዕድን ስራዎች ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ ሳይገመገም እና ለቀድሞው ባለፈቃድ ባላሳወቁበት ሁኔታ የወርቅ ማዕድን የፈቃድ ክልል ውስጥ ተደራራቢ ፈቃድ ከሚ/ር መ/ቤቱ እና ከክልሎች የተሰጠ መሆኑ፣

80. እንዲሁም ለኢትኖ ማይኒንግ ኃ.የተ.የግ.ማ ከሚ/ር መ/ቤቱ ጋር በተፈረመ ስምምነት 80% ያህሉ ቦታ የሚገኘው በጋ/ህ/ክ/መ አኮቦ ዞን ዲማ ወረዳ ውስጥ እንዲሁም 20% ያህሉ ደግሞ በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ ቤንች ማጂ ዞን ቤሮ ወረዳ ለወርቅና ሌሎች ማዕድናት ጥናት ለማካሄድ የማዕድን ምርመራ ፈቃድ የተሰጠው ሲሆን ማዕድን ሚ/ር ለክልሎች የመሬት ኪራይ ወቅቱን እና ጊዜውን ጠብቀው እንዲያስከፍሉ መረጃም ሆነ ማስረጃ በወቅቱ ባለማስተላለፉ ኢትኖ ማይኒንግ የአራት ዓመት የመሬት ኪራይ ለክልሎቹ ያልተከፈለ መሆኑን፣

81. ስለ ጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከሚኒስቴር መ/ቤቱ እስከ ክልል ማዕድን ቢሮዎች ድረስ ያሉ ሰንሰለቶች እና ችግሮች ስላሉ እንዲሁም በማዕድን ሴክተሩ ላይ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው ባለመስራታቸው የከበሩ እና በከፊል የከበሩ

ማዕድናት ስራዎች በአዋጅ፣ በደንብ፣ በማዕድን ስምምነቶች እና መመሪያዎች መሰረት የማዕድን ፍቃዶችን የማስተዳደሩ፣ የመቆጣጠሩና የማረጋገጡ ስራ በተሟላ መልኩ እንደልተሰራ ገልጸዋል፡፡

82. ስለሁኔታው ሚ/ር መ/ቤቱ በነባራዊ ሁኔታ ላይ ሚ/ር መ/ቤቱ በአዋጅ 678/2002 እና 651/2011 የከበሩና በከፊል የከበሩ የማዕድን ሥራዎች የሚል ፈቃድ አለመስጠቱን፣ ሆኖም በአዋጁ 678/2002 መ/ቤቱ የሚሠጠው ለኩባንያዎች መሆኑን፣ ኩባንየዎችም ከዓመት በላይ ፈቃድ ሳያሳድሱ የቆዩት ጉዳዩ በህግ የተያዘ በመሆኑ በአሠራር ላይም ችግር ያለውና ክርክር ያለበት አሳማኝ የሆነ ምክንያት በመኖሩ ሲሆን የቀጣይ ዓመት የሥራ ኘሮግራም ሳይቀርብና ሳይገመገም የድሳትም ሆነ ሥራ እንደማይጸድቅ፣ ሆኖም ግን አንዳንድ ጊዜ ከፋይል አያያዝ አንፃር ለማግኘት ቢያስቸግርም ይህንንም ለማተካከል አሁን በአዲሱ ቢሮ ሁኔታዎች እየተመቻቹ ቢሆንም የከበሩና በከፊል የከበሩ የማዕድን ሥራዎችን የሚቆጣጠሩት ክልሎች ቢሆኑም ሚ/ር መ/ቤቱ ባለፉት ዓመታት ተከታትሎ ፈቃድ እስከ መሰረዝ የሚደርስ እርምጃ የመውሰድ ሥራ በመሥራት ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

83. በተጨማሪም ፈቃድ ሳይኖራቸውና ብዛት ያለው ማዕድናትን ማከማቸት የሚለው በአዋጅ 651/2001 ያለ እና የተከለከለ ቢሆንም በአዋጁ ያለው ማከማቸት ሲባል በብዛት ማምረት፣ ግብይት እና ገበያ እስኪያፈላልጉ መያዝ እንደማይከለከል እና በዘርፉ ማከማቸት የሚለው በብዛት ብቻ ሳይሆን መሆን ያለበት ለምን ተከማቸ የሚለው መታየት ያለበት መሆኑንና ፈቃድ ሳያሳድሱ እና ከፈቃድ ዘመናቸው በላይ በመጠቀም የሚለው የክልሎች በአዋጁና በደንብ መሰረት ካለመሥራት ጋር የተያያዙ ችግሮች መሆናቸውን፣ የኢትኖ ማይኒግ እና የአከቦ ማይኒግ ፈቃዶች መደራረብ ሁኔታ ጉዳዩ በፍርድ ሂደት ላይ በመሆኑ አስተያየት መስጠት እንደሚያስቸግር እና በክልሎች ቦታ በተፈጠረው የመረጃ መለያየት በክልሉና በሚ/ር መ/ቤቱ በተፈጠሩ ችግር መኖሩንና ለማስተካከል ሥራ መጀመራቸውን ይሁን እንጂ ከካርታ ሥራ ተጠይቆ ከመንግሥት እውቅና በላይና የወጣ ካርታ ባለመኖሩ በአንዳንድ ካርታዎች ላይ ችግሮች እንደተከሰቱና ይህንንም ለመፍታት ጥረቶች እንደተደረጉ የገለጹ ሲሆን፣ በተጨማሪም የመሬት ኪራይ የመሰብሰብ ሥልጣን የክልል በመሆኑ ፈቃድ ሲሰጥም ሆነ ሲታደስ በማዕድኑ ህግ መሠረት ለማሳወቅ የስምምነት ሰነድ አንድ ኮፒ ወይም የእድሳት ደብዳቤው ከጅኦግራፊካል ኮአርዲኔቱ ጋር ለክልል ማዕድን ቢሮዎች እንደሚላክ ገልፀዋል፡፡

84. ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች ወደ ማናቸውም ክልል በመግባት በፈቃድ ክልላቸው ላይ ወይም ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የማዕድን ስራ እንቅስቃሴ/ሂደት/ ወጥ

በሆነና በተሟላ መልኩ በሁሉም ክልሎች ላይ የማይከታተሉና የማይቆጣጠሩ መሆኑ እንዲሁም ለክትትል ለተከደባቸው አከባቢዎችም ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ ከክልል እስከ ወረዳ ያሉት የማዕድን ቢሮዎች/ፅ/ቤቶች መፍትሂም ሆነ የግብረ-መልስ ሪፖርት ለባለፈቃዶቹ እንደማይልኩላቸው ታውቋል፡፡

85. በኦዲቱ ወቅት ከተሄደባቸው 3 ክልሎች በናሙና ከታዩ 11 ማህበራት ውስጥ ለ8ቱ ከማዕድን ሚኒስቴርም ሆነ ከክልሉ ምንም ቁጥጥር እንደማይደረግላቸው ከወረዳው ማዕድን ቢሮ ግን በተወሰነ መልኩ ቁጥጥር እንደሚደረግላቸውና ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ ክልልሎች አለመቆጣጠራቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

86. በዚህ ዙሪያ በዞንና በወረዳ ደረጃ ያሉት የማዕድን ቢሮ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሚኒስቴር ሚ/ቤቱ እንደማይቆጣጠር፣ የቁጥጥር ስራው እንዳልተሰራና ቁጥጥር ባለመደረጉ ህገ ወጥ አሰራሮችን ለመግታት አለመቻሉን እና በስራ ላይ ያሉ ክፍተቶችን ለመድፈን እንዳላስቻላቸው ገልጸዋል፡፡

87. ይህንን በተመለከተ የክልል ማዕድን ቢሮ የስራ ኃላፊዎችም ተጠይቀው ሚ/ር መ/ቤቱ የክልል ማዕድን ቢሮዎች እንዲቆጣጠሩ ውክልና እንዳልሰጣቸው፣ በራሱ ፈቃድ የሰጠውንም ጭምር በተሟላ መልኩ ሄዶ ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደረግ በተጨማሪም ክልል ማዕድን ቢሮዎችም የእነዚህን ባለፈቃዶች መረጃ ስለሌላቸው ባለፈቃዶች በገቡት ውል መሰረት መስራታቸውን ለመቆጣጠርም ሆነ ለመከታተል እንዳላስቻላቸው ይህም በመሆኑ ባለፈቃዶች ግዴታቸውን በአግባቡ እንዳይወጡ ከማድረጉም ባሻገር ከፈቃዳቸው ውጪ እየሰሩ መገኘታቸውን፣ መክፈል የሚገባቸውን ክፍያዎች (የመሬት፣ የሮያሊቲ፣) በተገቢው ሁኔታ እንዳይፈፅሙ ማድረጉን ሆኖም ግን አልፎ አልፎ የባለፈቃዶችን ፈቃድ ለመዝጋት ሲፈልግ ክልሉ ያረጋግጥ የሚል መመሪያ በደብዳቤ ከሚ/ር መ/ቤቱ ቢተላለፍም ይህ ደግሞ የክልሉ የመሬት ኪራይ በአግባቡ ለመሰብሰብ አለማስቻሉንና ህገ-ወጦች እንዲስፋፉ ማድረጉን ገልፀዋል፡፡

88. ስለ ጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰው ሀይል እጥረት ምክንያት በተሟላ መልኩ እና መደበኛ በሆነ ሁኔታ ተሰርቷል ለማለት እንደማያስችል፡፡ በዚህ ዙሪያ ክትትል እና ቁጥጥርም እየተከናወነ አለመሆኑን፣ ለተላኩት ሪፖርቶችም ግብረመልስ መላክን በተመለከተ ሚ/ር መ/ቤቱ እንዳልሄደበት መልስ ሰጥተዋል፡፡

89. ስለ ሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ ላይ እንደገለፁት ለማህበራት /ለአዘዋዋሪዎች/ ፈቃድ የሚሰጣቸው ከክልል ሲሆን በክልል ያሉ ወረዳዎችም የቁጥጥር ስራውን እንደሚሰሩና ክትትል ሥራውንም በተመለከተ ሚ/ር መ/ቤቱ በተለያዩ ጊዜ ክትትል በማድረግ በአካልና በግብረ መልስ ሲሰጥ እንደቆየ ነገር ግን የበለጠ ማጠናከር የሚጠይቅ መሆኑን፣ ሆኖም ግን ሚ/ር መ/ቤቱ ከክልል ማዕድን ቢሮዎች ጋር በመነጋገር ከቢሮ ባለሙያ ቢሆንም ግብረ መልስ ሪፖርቱን ግን ከወረዳና ከክልል አመራር ጋር በጋራ የሚካሄድ መሆኑን፣ በተጨማሪም ሚ/ር መ/ቤቱ የክልል ማዕድን ቢሮዎች እንዲቆጣጠሩ ውክልና አልሰጣቸውም ለሚለው በማዕድን ሥራዎች አዋጅ ካለው እና የክልሎችን መብትና ተልዕኮ የሚቃረን ሲሆን በአዋጁ እንደተገለጸው ክልሎችና ሚ/ር መ/ቤቱ በተሰጣቸው መብት የመቆጣጠር ኃላፊነትና በጋራ የመሥራት ግዴታ ያላቸው በመሆኑ ሁለቱም የተሰጣቸውን ፈቃዶች የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለባቸው፣ የመሬት ኪራይ የመሰብሰብ ስልጣን በተመለከተ የክልሎች መሆኑን፣ ነገር ግን እነዚህ ችግሮች የተፈጠሩት ክልሎች አዋጁን ተግባራዊ ባለማድረጋቸውና ለዚሁ የሚያስፈልግ አደረጃጀት ባለመኖሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

90. ይሁን እንጂ ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 16 እና በአንቀፅ 52(መ) (ረ) እንዲሁም በአንቀፅ 54 ንዑስ አንቀፅ 1(ሀ)ና 3 መሰረት በፈቃድ ክልላቸው ላይ ወይም ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የማዕድን ስራ እንቅስቃሴ በተሟላ መልኩ ባለመከታተላቸውና ባለመቆጣጠራቸው ህገወጥ የማዕድን ምርትና ግብይት እንዲስፋፉ ማድረጉን ለመረዳት ተችሏል፡፡

**ባለፈቃዶች ወርቅና ብር ለብሄራዊ ባንክ እንዲያቀርቡ ቁጥጥር መደረጉ እና ስለሚስተናገዱበት ሁኔታ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፤**

91. ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በስምምነት የሚወሰነውን ወርቅና ብር መጠን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲያቀርቡ ፈቃድ ሰጪ አካላት መቆጣጠራቸውን ሊከታተል እንዲሁም ወርቅ አቅራቢዎች፤ በክልሎች ለሚገኙ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለወርቅ ግዥ ጣቢያዎች ወርቅ ሲያቀርቡ በወቅቱና ሥርዓትን በተላበሰ መንገድ እንደሚስተናገዱ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

92. ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በስምምነት የሚወሰነውን ወርቅና ብር ማዕድናት መጠን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲያቀርቡ ሁሉም ፈቃድ ሰጪ አካላት ስለመቆጣጠራቸው ወጥ በሆነ መልኩ ከ2004-2006 ዓ.ም በመደበኛነት ክትትል እንደማያደርግ እና ክትትል በተደረገባቸው ክልሎችም ወርቁ ሊቀንስ የቻለበትን ምክንያቶች በመለየት ለችግሮቹ አፋጣኝ መፍትሔ ሊያስወስድ የሚችል የግብረ መልስ ሪፖርት አለመላኩ ታውቋል፡፡

93. የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣ አዋጅ ቁጥር 651/2/ መሠረት የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በስምምነት የሚወሰነውን ወርቅና ብር ማዕድናት መጠን ለባንኩ ማቅረብ አለበት ቢልም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ በደቡብ፣ በኦሮሚያ እና በትግራይ ክልሎች ከ2004-2006ዓ.ም ለብሄራዊ ባንክ የሚቀርበው ወርቅ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን እንዲሁም ማስረጃቸው በሚ/ር መ/ቤቱ በተገኘው መሰረት በአምስቱም (በደቡብ፣ በኦሮሚያ እና በትግራይ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና በጋምቤላ) ክልሎች የወርቅ ዕቅድ አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ መሆኑ ታውቋል፡፡

94. ይህም የሆነው  በክልሎች ወጥ በሆነ መልኩ ሮያሊቲ ስለማይቆረጥ ማለትም ጋምቤላ ክልል ዲማ ወረዳ የሮያሊቲ ክፊያ ባለመቁረጡ እንዲሁም  በደቡብ ቤሮ ወረዳ  ደግሞ በመቆረጡ አምራቾች በህጋዊ መንገድ ለህጋዊ አዘዋዋሪዎች ወርቁን ስለማይሸጡ ወደ ባንክ የሚገባው ወርቅ በከፍተኛ ሁኔታ መጠኑ መቀነሱን እንዲሁም በሌሎች ክልሎች ደግሞ ለባንክ የድጋፍ ደብዳቤ ለማፃፍ የክልል ማዕድን ቢሮ ጋር ሲሄዱ ከአዘዋዋሪዎች ላይ የሮያሊቲ ክፊያ በመቁረጣቸው፣ የህገወጥ ወርቅ ግብይትና ዝውውር በመጨመሩ፣ ህገወጦች ብሔራዊ ባንክ ከሚገዛበት ዋጋ በላይ አስበልጠው በመግዛታቸው እና በህገ ወጥ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ወርቆችን ለመቆጣጠር የሚያስችል በሁሉም ክልል የተሻለ ኬላና ዘመናዊ የመፈተሻ መሣሪያ ባለመኖሩ መሆኑን፣ በተጨማሪም በአንዳንድ ክልል የሚገኙ የወርቅ አዘዋዋሪዎችም በመቀዝቀዙ፣ በክልል ወረዳዎች የሚገኙ ስትሪንግ ኮሚቴዎች ተከታታይና ቀጣይነት ባለው መልኩ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት አስፈለጊውን የደጋፍና የክትትል ሥራዎችን ባለመስራታቸው፣ ብሔራዊ ባንክ እና በክልሎች የሚገኙ ፈቃድ ሰጪ አካላት መካከል የመናበብ ችግር በመኖሩ  እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ ወርቁ ሊቀንስ የቻለበትን ምክንያቶችና ማነቆዎችን ለይቶ ለችግሮቹ አፋጣኝ መፍትሔ ባለመስጠቱ መሆኑን ከአዘዋዋሪ ባለፈቃዶችና ከፈቃድ ሰጪ ቢሮዎች እንዲሁም ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

95. በዚህ ዙሪያ የክልል ማዕድን ቢሮ የስራ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ ወቅት በሰጡት ምላሽ የክልል የማዕድን ቢሮዎች አዘዋዋሪዎች ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወርቅ መቀበያ ጣቢያ በዓመት ምን ያህል እንደሚያስገቡና የታቀደው ይግባ አይግባ የሚያውቁበት መረጃ እንደማያገኙ በሎሎች ክልሎች ደግሞ የወርቅ አምራቹ በፀጥታ ችግር ምክንያት በቂ የወርቅ ምርት ባለማግኘትና ያገኙትንም ወርቁንና ብሩን የሚዘረፉበት እና ለህገወጦች አሳልፈው የሚሸጡበት ሁኔታ በመኖሩ፣ ለዚህም የክልሎች ማዕድን ቢሮ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት አናሣ በመሆኑ በሚፈለገው ደረጃ ወደ ባንክ መግባት ያለበት የወርቅና የብር መጠን ወደ ባንክ አለመግባቱን ገልፀዋል፡፡

96. ይሄንን በተመለከተ የብሄራዊ ባንክ የከረንሲ ማኔጅሜንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በቃለ መጠይቅ ወቅት በሰጡት ምላሽ ማንኛውም የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት ወርቅና ብር ማዕድናት መጠን ለባንኩ ማቅረብን በተመለከተ ስምምነትነት ስለመኖሩ እርግጠኛ አለመሆናቸውን ነገር ግን ባንኩ ስትራቴጂ ስላለው ስትራቴጂውም አቅራቢዎችን ማበረታት እና ኮንትሮባንድን መከላከል መሆኑን በዕቅድ መሰረት ባይሰበሰብም በወርቅ ዋጋ መዋዠቅ ምክንያት ባንኩ ላይ ችግር መፍጠር እንደሚችል ነጋዴዎችም በመያዝ ለባንኩ እንደማያቀርቡ በዚህ ዙሪያም መጠናት እንዳለበት የገለፁ ሲሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለሽሬ ቅርንጫፍ የስራ ኃላፊዎችም በትግራይ ክልል በወረዳዎች የሚገኙ የወርቅ አዘዋዋሪዎች ወደ ባንክ በዓመት ምን ያህል እንደሚያስገቡ የማያውቁ መሆኑና በዓመት የታቀደው ወርቅ ስለመግባቱም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ እንዲሁም ይህንን ችግር በዓመታዊ ስብሰባ ላይ ቢያሳውቁም መፍትሔ እንዳልተገኘ ገልፀዋል፡፡

97. ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪም የማዕድን ሚኒስቴር ወርቅ አቅራቢዎች በክልሎች ለሚገኙ ለአራት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ ጣቢያዎች /አዋሣ፣ ጅማ፣ መቀሌና አሶሳ /ወርቅ ሲያቀርቡ በወቅቱና ሥርዓትን በተላበሰ መንገድ የሚስተናገዱ ስለመሆኑ የሚከታተልበት ሥርዓት የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

98. ይህም በመሆኑ አቅራቢዎች ወርቅ ሲያቀርቡ በወቅቱና ሥርዓትን በተላበሰ መንገድ እንደማይስተናገዱ፣ባንኩ የተለያየ ምክንያት በመፍጠር ክፍያ በወቅቱ እንደማይፈጸምላቸውና ከ አንድ ሳምንት በላይ እንደሚቆይባቸው በኦዲቱ ወቅት የታዩት 9 የወርቅ አዘዋዋሪዎችና አምራቾች የገለጹ ሲሆን እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት በሚ/ር መ/ቤቱ ቀርበው ከተከለሱ ሰነዶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

99. በዚህ ዙሪያ በናሙና የታዮት ሁለት የብሄራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ ጣቢያ የስራ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ የወርቅ አቅራቢዎች በአንድ ጊዜ መምጣት ከጂኦሎጂካል ሰርቬይ ሠራተኞች ጋር ያለመግባባት ችግር ከመፈጠሩም በላይ ወርቅ የሚመዘንበት እና ካራቱን የሚለካበት ማሽን ከአቅም በላይ ስለሚሰራና ብዙ ጊዜ በማገልገሉ ምክንያት የሚዛንም ሆነ የልኬት መዛባት እየፈጠረባቸው መሆኑን፣ እንዲሁም የወርቅ የማጣሪያ ውሃም እጥረት መኖሩ እና ከሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ ከጂኦሎጅካል ሰርቨይ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ቶሎ መፍትሄ እንደማያገኙ ይህም በመሆኑ አቅራቢዎች ያመጡትን ወርቅ ወዲያው ለመረከብ አለማስቻሉን ገልፀዋል፡፡

100. ስለሁኔታው የኢትዮጵያ የብሔራዊ ባንክ የከረንሲ ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው ክልል ላይ ያሉትን የግዥ ጣቢያዎች ለመቆጣጠር ቢከብድም ከነጋዴዎች ጥቆማ እንደሚደርሳቸው እና ሃሣባቸውንም ተቀብለው የሚያረጋግጡበት መንገድ እንዳላቸው ቢገልፁም የሚያረጋግጡበትን ማስረጃው በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው ማቅረብ ያልቻሉ መሆን፣ ሆኖም ግን ባንኩ ስትራቴጂ ስላለው ስትራቴጂውም አቅራቢዎችን በዕለቱ ካለው ገበያ ላይ 5% ጨምሮ በመክፈል ማበረታት መሆኑንና ባንኩ የተሻለ ስራ እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡

101. ስለ ጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ይሄ ያልተፈታ ችግር እንደሆነ ፈቃድ የመስጠቱና የማስተዳደሩ ሥራ ለክልሎች በመሰጠቱ ክፍተት መፈጠሩን ይሁን እንጂ የከበሩ ማዕድናት የአዘዋዋሪነት ፈቃድ የሚሰጠው በክልል ማዕድን ቢሮዎች ስለሆነ ባለፈቃዶች በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በስምምነት የሚወሰነውን ወርቅና ብር ማዕድናት መጠን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲያቀርቡ የመቆጣጠርም ሆነ የመከታተል የክልል ማዕድን ቢሮዎች ኃላፊነት እንደሆነና፤ ማዕድን ሚ/ርም የክልል ማዕድን ቢሮዎችን ስለመቆጣጠራቸው መከታተል እንደማይችል፡፡ ሆኖም ግን የክልል ማዕድን ቢሮዎች የሰው ኃይል እጥረት ስላለባቸው ወጥ በሆነ መልኩ እንደማይከታተሉ ገልጸዋል፡፡ ወርቅ አቅራቢዎች የሚስተናገዱበት ሁኔታን በተመለከተ የሶስትዮሽ ስምምነት ላይ የጂኦሎጅካል ሰርቨይ፣ ብሄራዊ ባንክ እና ማዕድን ሚ/ር አብረው እንደሚሰሩ መገለፁን፤ ሆኖም ግንየሶስትዮሽ ስምምነቱን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ክፍተት መኖሩን ከማዕድን ሚኒስቴርም አቅም በላይ እንደሆነ፣ እንዲሁም ማዕድን ሚ/ር ለአራት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ ጣቢያዎች /አዋሣ፣ ጅማ፣ መቀሌና አሶሳ/ ወርቅ አቅራቢዎች ወርቅ ሲያቀርቡ በወቅቱና ሥርዓትን በተላበሰ መንገድ ስለሚስተናገዱበት የሚያረጋግጥበት ሥርዓት አለመዘርጋቱን ገልጸዋል፡፡

102. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ ላይ በገለጹት መሠረት በክልሎች ማለትም በትግራይ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላና በኦሮሚያ ክልሎች የወርቅ ዕቅድ አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ ሊሆን የቻለበት ምክንያት በምርትና፣ በዓለም ገበያ የሚወሰን በመሆኑ ሲሆን፤ በአጠቃላይ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ቢኖሩም ችግሮቹን ለማቃለለ ቢሞከርም ከአቅም በላይ በመሆኑ በምርት መቀነስ ምክንያት ሚ/ር መ/ቤቱ ዳይሬክቶሬት በማቋቋምና ድጋፍ በመስጠት እንደሚገኝ፣ በተጨማሪም በክልሎች የታቀደው የወርቅ መጠን ባንክ ስለመግባቱ መረጃ አለማግኘትን በተመለከተ ችግሮች መኖራቸው በተለያየ መንገድ የተነሱ ቢሆንም፤ በተደረገው ስምምነትና አሠራር በማስተካከል ክልሎችና ገቢዎች መረጃዎችን ከብሔራዊ ባንክ እንዲወስዱ በመደረጉ በአሁኑ ወቅት በየጊዜው መረጃዎችን በማግኘት ላይ እንደሚገኙ፣ እንዲሁም ለክልሎች ለሮያሊቲ ክፍያ ደንብ ወይም መመሪያ ካላወጡ የፌዴራሉን መከተል እንደሚገባቸው፣ ሆኖም ግን ሚ/ር መ/ቤቱ ክልሎች የሮያሊቲ ተመን እንዲያወጡና በማዕድን ሥራዎች አዋጅ መሠረት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሚ/ር መ/ቤቱ የሚያስተባብር መሆኑን፣

103. እንዲሁም በብሔራዊ ባንክ ያለው የወርቅ ግዥ ጣቢያዎች አልፎ አልፎ የሚነሱ ችግሮች መኖራቸው የሚታወቅ ሲሆን አንዱ የሚነሳው አቅራቢዎች በአግባቡ የማይስተናገዱ መሆኑን ሚ/ር መ/ቤቱና ባንኩ በየጊዜው መስተካከል እንደሚሞክሩና አሁንም የወርቅ ግዥ ጣቢያዎች ላይ ማስተካከል የሚገባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው በጉዳዮቹ ላይ ግንዛቤ ተወስዶ የሚመለከታቸው አካላት በጋራ ለመሥራት ችግሮቹን ለማስተካከል ጥረት በማድረግ ሚ/ር መ/ቤቱ እንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝ፣ እንደሁም በሶስትዮሽ አሠራር ጥናት መቀየርና ለአቅራቢዎች ከምርት ቦታ በአቅራቢያው በቅርብ ኪሎ ሜትር ግዥ ጣቢያ አምራቾች በቀላሉ ግብይት የሚያገኙበት አሠራር በመዘርጋት፣ ኪሣራ ላይ እንዳይወድቁ ተስማሚ ቦታ የማመቻቸት ሥራ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት በመሠራት ላይ መሆኑን እና በጂኦሎጂካል ሰርቬይ የሚለኩ ወርቆችን በተመለከተ በጂኦሎጂካል ሰርቬይና ብሄራዊ ባንክ መካከል ያለመግባባት ችግር ከመፈጠሩም በላይ በወርቅ ካራት ላይ አልፎ አልፎ ተመሳሳይ ችግር መኖሩን ግን እንደአሠራር ባንኩ ከጂኦሎጂካል ሰርቬይ ጋር በጋራ መሥራት እንደሚገባው ገልጸዋል፡፡

104. ይህም በመሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን በተሟላ መልኩ ባለመወጣታቸው ወደ ብሄራዊ ባንክ የሚገባው ወርቅ ከዓመት ዓመት እየቀነሰ መምጣቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የእደጥበብ ባለፈቃዶች ጥሬ ወርቅና ብር ከባንክ ብቻ እንዲገዙ ስርዓት በመዘርጋት ስለመከታተሉ፣

105. ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩ ማዕድናት እደጥበብ ባለፈቃድ ለስራ የሚያስፈልገውን ጥሬ ወርቅና ብር ከብሄራዊ ባንክ ብቻ እንዲገዙ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስርዓት በመዘርጋት ሊከታተል ይገባል፡፡

106. የከበሩ ማዕድናት እደጥበብ ባለፈቃድ ለስራ የሚያስፈልገውን ጥሬ ወርቅና ብር ከብሄራዊ ባንክ ብቻ እንዲገዙ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስርዓት ቢዘረጋም አለመከታተሉ ታውቋል፡፡

107. የማዕድን ሚኒስቴር የከበሩ ማዕድናት ዕደ-ጥበብ ፈቃድ እና የከበረ ማዕድናት የንግድ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በክልሎች መሰጠት እንዲጀምርና ፈቃዱን ማስተዳደር እንዳለባቸው ውክልና መስጠቱን እና የተሰጡ ፈቃዶችና የብቃት ማረጋገጫዎች በግልባጭ እንደሚያሳውቃቸው ከመጋቢት 08 እስከ ሚያዚያ/2006 ዓ.ም. በደብዳቤ ለኦሮሚያ፣ ለትግራይ፣ ለአማራና ለደቡብ ክልል ማዕድን ቢሮዎች ያሳወቀ ቢሆንም ውክልና ሰጥቶ ፋይላቸውን ለክልሎች በወቅቱ ባለመላኩ እስከ 04/02/2007 ዓ.ም የክትትል ስራው በክልሎች ያልተጀመረ መሆኑ እንዲሁም እነዚህ ባለፈቃዶች ከ2004-2006 ዓ.ም ለስራ የሚያስፈልጋቸውን ጥሬ ወርቅና ብር ከብሄራዊ ባንክ ማዕድን ቢሮዎች መግዛታቸውን የሚያሳይ ተመዝግቦ የተቀመጠ ምንም ዓይነት ሪፖርት ወይም ማስረጃ በሚ/ር መ/ቤቱ ያልተገኘ መሆኑ፤ ከዚህም በተጨማሪ ለጋምቤላ የሰጠው ውክልና እና ለጋምቤላና ለአማራ ደግሞ የእደጥበብ ፋይል ስለመላኩ ተጠይቆ በሚ/ር መ/ቤቱ የውክልናውም ሆነ የዕደጥበባቱ ማስረጃ ተጠይቆ አልተገኘም፡፡

108. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ይህን በተመለከተ በሚ/ር መ/ቤቱ የእደጥበብ ባለፈቃዶች ለስራ የሚያስፈልጋቸውን ጥሬ ወርቅና ብር ከብሄራዊ ባንክ ብቻ ስለመግዛታቸው ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት እንዳለው ይሄውም የወርቅ ጥያቄ ከባለፈቃዶች ስመጣ ድጋፍ እንደሚሰጡ፣ ባለፈቃዶቹ ለፈቃድ ዕድሳት ሲመጡም ወርቅ ከብሄራዊ ባንክ ስለመግዛታቸው እንደሚያረጋግጡ እንዲሁም የኢንቨንተሪ ቆጠራ እንደሚያደርጉ ሆኖም ግን አዋጅ ቁጥር 678/2002 እና አዋጅ ቁጥር 651/2001 እርስ በርስ ስለሚጣረስ አዋጁ ላይም ክፍተት መኖሩን ይህ ደግሞ ባለፈቃዶቹ ከባንክ ውጭ እንዲገዙ መንገድ መክፈቱን፡፡ ችግሩን ለመፍታት ጥናት ተጠንቶ እንደነበረ ነገር ግን የችግሩ መፍትሔ አለመገኘቱን በዚሁ ምክንያት አብዛኛዎቹ የእደጥበብ ባለፈቃዶች ከባንክ ወርቅ የመግዛት ፍላጐት እንደሌላቸው፣ ገዙ ለማለት ብቻ ትንሽ ወርቅ ገዝተው ሌላውን በዝቅተኛ ዋጋ ከባንክ ውጭ እንደሚገዙና ብሄራዊ ባንክም ወርቅ ስገዛ 5% በመጨመር ከአዘዋዋሪዎች ላይ ስለሚገዛ ሲሸጥም መክሰር የለብኝም ስለሚል በከፍተኛ ዋጋ እደሚሸጥ ገልፀዋል፡፡

እንዲሁንም ለወርቅ ግዥ ብሄራዊ ባንክን የሚጠይቁት ጥቂት እደጥበባት እንደሆኑ በዚህም ላይ ክፍተት መኖሩን አስረድተዋል፡፡

109. በተጨማሪም በክልል ደረጃ በእደጥበብ ባለፈቃዶች ዙሪያ ውክልና መስጠትን በተመለከተ ከ2006 ዓ.ም አጋማሽ በፊት ሚ/ር መ/ቤቱ ፈቃድ የመስጠትም ሆነ የማስተዳደር ስራ ሊሰራ የነበረ ቢሆንም አዋጁ ላይ ለክልል ማዕድን ቢሮዎች ውክልና መስጠት እንዳለበት በመገለፁ በዚሁ መሰረት በ2006ዓ.ም ውክልና ለትግራይ፣ ለአማራ እና ለደቡብ እንደሰጡና ለሌሎች ክልሎች መጥተው እንዲወስዱ ጥሪ ቢደረግም የመኪና እና የሰው ኃይል ችግር አለን በማለት እንዳልወሰዱ ገልፀዋል፡፡ ክትትልን በተመለከተ ደግሞ እነርሱ ካልጠየቁአቸው ክትትል እንደማያደርጉ ሆኖም ግን በክልል ላሉትም የክትትል ሲስተም ስላልተዘረጋ ክፍተት መኖሩን፣ በአጠቃላይ ይሄንን በሚመለከት በሚ/ር መ/ቤቱ እና በብሔራዊ ባንክ በጋራ ማጥናት እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

110. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ ላይ የክልል ማዕድን ቢሮዎች የዕደጥበባትን መረጃዎች ከሚ/ር መ/ቤቱ የወሰዱ ቢሆንም በስምምነቱ መሠረት በሚ/ር መ/ቤቱ በመገኘት የሰው ኃይል አደራጅተው ሥራ እንዲጀምሩ ሥልጠና ለማድረግ በዕቅድ የተያዘ መሆኑና ጥቂት ክልሎችም ሥራ የጀመሩ መሆናቸውን፣ እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ ባለፈቃዶች ወርቅ ከባንክ እንዲገዙ አሠራር በመዘርጋት እየሠራ ቢሆንም የባንኩ የወርቅ ዋጋ በተለያየ መንገድ የሚገኝ በመሆኑ ከፍተኛ ልዩነት ይኖረዋል በሚል በጣም ጥቂት ባለፈቃዶች ብቻ ከባንክ የሚገዙ በመሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ ከባንኩ ጋር በመሆን ግብይቱን ተመጣጣኝ ለማድረግ ቢፈልግም ባንክ የሚገዛው 5% ጨምሮ በመሆኑ ባለፈቃዶቹ ጨምረው መግዛት ባለመቻላቸው መግባባት አለመቻሉ፣ ነገር ግን በቀጣይ ብዙ ስራ ለመሥራት እንደሚሞክር ገልጸዋል፡፡

111. ይህም በመሆኑ በየወርቅ ቤቶች አከባቢ ህገ ወጥ ነጋዴዎች እንዲበራከቱ ማድረጉን እና በመስክ ኦዲት ወቅትም በናሙና በተመረጡት ክልሎች ሥራው እንዳልተጀመረ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ፈቃድ ሰጪ አካላት ምርት ላይ የተሰማሩ ባለፈቃዶች የሚፈለግባቸውን ልዩ ልዩ ገቢ በወቅቱ መሰብሰባቸው፣ መመርመራቸው እና እርምጃ መውሰዳቸውን በተመለከተ፣

112. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን ከማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የተመረተውን ማዕድን በንግድ ልውውጥ በተሸጠበት ዋጋ ላይ መከፈል የሚገባውን የሮያሊቲ እና የመሬት ኪራይና ሌሎች ክፍያዎች ሂሳብ በወቅቱ ሊሰበስብና ሊመረምር ይገባል፡፡

113. በማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀጽ 63/1 እና 3 መሠረት የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የተመረተውን ማዕድን በንግድ ልውውጥ ዋጋ ላይ ለከበሩ ማዕድናት

8%፣ በከፊል ለከበሩ ማዕድናት 6% ሮያሊቲና መከፈል የሚገባውን የሮያሊቲ መጠን ለመተመን በማይቻልበት ጊዜ ባለፈቃዱ ጊዜያዊ የሮያሊቲ ክፍያና ለባህላዊ ማዕድናት በክልሎች በሚወጣው ህግ መሰረት እንዲሁም የመሬት ኪራይና ሌሎች ክፍያዎች ሂሳብ በወቅቱ ሊሰበስብና ሊመረምር እንደሚገባ የሚደነግግ ቢሆንም፤

114. በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ፈቃድ ሰጪ አካላት ከማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የተመረተውን ማዕድን በንግድ ልውውጥ በተሸጠበት ዋጋ ላይ ለከበሩ ማዕድናት 8%፣ በከፊል ለከበሩ ማዕድናት 6% ሮያሊቲ፣ ተመን ላልወጣለት ማዕድን ጊዜያዊ የሮያሊቲ ክፍያ ተመን በማውጣትና ለባህላዊ ማዕድናት በክልሎች በወጣው ህግ መሰረት  እንዲሁም የመሬት ኪራይና ሌሎች (የመንግስት ነፃ ድርሻና ግብር) ክፍያዎች ሂሳብ በወቅቱ ተከታትለው እንደማይሰበስቡና እንደማይመረምሩ ታውቋል፡፡በተጨማሪ ሁሉም ክልሎች በተሟላ መልኩ ለባህላዊ ማዕድናት የሮያሊቲ የአከፋፈል ህግ ባለማውጣታቸው እና ህግ ያወጡትም በሥራ ላይ ባለማዋላቸው  እንዲሁም  የሮያሊቲ  መጠን  ባለመተመን  በኦዲቱ  ወቅት  የታዩት የኦሮሚያ፣ደቡብና ትግራይ  ክልሎች ውስጥ በሶስቱም ክልሎች የሚገኙ አምራቾች አብዛኞቹ ሮያሊቲ የማይከፈሉ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

115. ይህም በመሆኑ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የከበሩ ማዕድን አምራቾች የሮያሊቲ ክፍያን በወቅቱና በተጠቀሙት ምርት መጠን የማይከፍሉ፣ የመሬት ኪራይና ሌሎች የመንግስት ገቢዎችን (ግብር) ገቢ የማያደርጉ መሆኑን እንዲሁም ከመንግስት የሚወስዱትን ደረሰኞች በአግባቡ እንደማይጠቀሙ ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች ማህበራት ደግሞ የአዘዋዋሪና የአምራች ፈቃድ በአንድ ላይ በመውሰድ በሚከፍሉት የሮያሊቲ ክፊያ ላይ ክፍተት የፈጠረ መሆኑ፣ እንዲሁም   መክፈል የሚገባቸውን ክፍያ ለመንግሥት ገቢ አለማድረጋቸው እና ገቢ ባለማድረጋቸው የክልሉ ማዕድንና ኢነርጂም የወሰደው እርምጃ አለመኖሩ፤

116. በዚሁ ክልል በ2004 ዓ.ም ከ1,961,502.54 ግራም ከቀረበ ወርቅ ብር125,536,162.56 እና ከ157,476 ኪግ ታንታለም ብር1,446,653  በድምሩ ብር 126,982,815.56 ክልሉ ከሮያሊቲ ክፍያ መታጣቱን እንዲሁም በ2005 ዓ.ም  የማዕድን አምራቾች ሮያሊቲ ባለመክፈላቸው ብር 300,000,000 ክፍያ ማጣቱ  በአጠቃላይ ብር 426,982,815.56 በላይ ክልሉ ከሮያሊቲ ገቢ ያጣ መሆኑ፤

117. በተጨማሪ ከክልሉ በታየው በአዶ ሻክሶ ወረዳ  የሚገኙ ባለፈቃዶች ለባንክና ለወረዳው የሚያስገቡት የምርትና ሽያጭ ሪፖርት በከፍተኛ ደረጃ በመለያየቱ በ2004ዓ.ም ብቻ ለባንክ የገባው የወርቅ መጠን 117,093.90 ኪ.ግ(98.4%) ሲሆን ለወረዳው የቀረበው ሪፖርት ግን 1,837.80ኪ.ግ (1.6%) በመሆኑ ለዚህም የተከፈለው ሮያሊቲ ክፍያ 110,554.70 ብር ብቻ

ሲሆን፤ ለ115,256.1 ኪ.ግ (የ98.40%ቱ) ሮያሊቲ ሳይከፈል ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ባለፈቃዶች ጋ መቅረቱን ከማስረጃው ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ክልል በናሙና በተወሰደ አንድ ወረዳ ላይ ብቻ ከ65 የማዕድን አምራች ባለፈቃዶች ውስጥ ሮያልቲ ከፍለው የማያውቁ 28 (43%) የተገኙ ሲሆን በወቅቱ የማይከፍሉ ደግሞ 25(38.5%) ባለፈቃዶች የተገኙ መሆኑን፣

118. ከዚህም ሌላ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከጉጂ ዞን እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከ80 - 85% የሚሆነው የወርቅና የታንታለም ማዕድን አቅርቦታቸው ሮያሊቲ ሳይከፈልበት በአዋጁ ከተቀመጡ አግባብ ውጪ ከሕገወጥ አምራቾችና ሮያሊቲ ካልከፈሉ ማህበራት ተገዝተው የሚቀርቡ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም ምክንያት ህጋዊ የማዕድን አምራቾችን ከሥራ ውጪ ማድረጉን፣

119. በሁሉም ክልል በተሟላ መልኩ ለባህላዊ ማዕድናት የሮያሊቲ አከፋፈልን በተመለከተ ህግ ባለማውጣቱ በደቡብ ክልል ወጥ በሆነ መንገድ የሮያሊቲ ክፊያ የማይሰበሰብ መሆኑ ማለትም ሮያሊቲ ሳይከፍሉ ምርታቸውን የሚሸጡ ባለፈቃዶች መኖራቸው፣ በክልሉ እስከ ጥቅምት 2007ዓ.ም ካሉት 8 የከበሩ ማዕድናት አምራቾች ውስጥ 1 ባለፈቃድ ሮያሊቲ በወቅቱ ያልከፈለ፣ 4 ባለፈቃዶች ሮያሊቲ ከፍለው የማያውቁ እንዲሁም 3 ባለፈቃዶች ደግሞ ማስረጃቸውም ሆነ መረጃቸው በክልሉ ያልተገኘ መሆኑ ከክልሉ ከተገኘ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

120. በዚሁ ክልል ወረዳ ላይ በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሆነው /አማዞናይትና ኳርትዝ/ ሮያሊቲ ለማስከፈል የክልሉን ማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ የሮያሊቲውን ተመን እንዲሰጠው ጥያቄ ቢያቀርቡለትም ከክልሉ በላይ ስለሆነ ክልሉ ለሚ/ር መ/ቤቱ ጥያቄ አቅርቦ በዓለም ደረጃ ያለውን የመሸጫ ዋጋ ማስረጃ ተንተርሰው ዋጋውን በማስላት እንዲያስከፍሉ መልስ ቢሰጣቸውም በደንብም ሆነ በመመሪያ ላይ የዋጋው ተመን ባለመኖሩ በግምት ቢያስከፍሉምመከፈል የሚገባው ክፍያ ለክልሉ ሙሉ በሙሉ እንዳልገባ የክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

121. ሁለት ማህበሮች ከማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ የወሰዱ ቢሆንም ማስረጃቸው ለክልሉ በወቅቱ ተሟልቶ ባለመተላለፉ ተገቢውን የመሬት ኪራይ ያልከፈሉ መሆኑን እና ባለመክፈላቸውም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ እንዲሁም በትግራይ ክልል ማንኛውም የባህላዊና የአነስተኛ ደረጃ የወርቅ ማዕድን አምራች ባለፈቃድ ለሚያመርተው የወርቅ ምርት 3% ሮያሊቲ እንዲከፍሉ በክልሉ ተወስኖ ማህበራት/ባለፈቃዶቹ/ እንዲከፍሉ የማዕድን ሥራውን ለሚያስተዳድሩት ወረዳዎች በቃል ቢተላለፍላቸውም የማዕድን አምራች ባለፈቃዶች

ግን የማይከፍሉ መሆኑ፣ እንዲሁም በዚሁ ክልል ከማዕድን ሚ/ር ፈቃድ ተሰጥቶአቸው በተለያዩ ቦታዎች የማዕድን ሥራዎች የሚሠሩ ባለፈቃዶች ቢኖሩም ለክልሉ በ2005 እና 2006 በጀት ዓመት የመሬት ኪራይ አለመክፈላቸው በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

122. ይህንን በተመለከተ ባለፈቃዶቹ ወደ ወረዳው የሚሄዱት ከባህላዊ ወርቅ ማምረት ወደ ኢንተርኘራይዝ ለመሸጋገር ሲፈልጉ ብቻ በመሆኑ ስለማያገኙዋቸው እንዲከፍሉ ለማድረግና እርምጃም ለመውሰድ የሚቸገሩ መሆናቸውን፣ ባለመክፈላቸውም ከሮያሊቲ መገኘት የሚገባውን ገቢ ማግኘት አለመቻሉ እንዲሁም የመሬት ኪራይን በተመለከተ በክልሉ የተወሰነ ነገር እንደሌለ ነገር ግን በ1996 ዓ.ም በወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን፣ ለባህላዊ ማዕድናት የምርት ቦታ ግን ለአምስት ሺህ ካሬ ሜትር በዓመት 50 ብር እንደሚከፍሉ የክልሉ ሁለት ወረዳዎች የማዕድን የውሃና ኢነርጂ ኤጀንሲ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

123. የሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃላ/የተ/ የግ/ማህበር በከፍተኛ ደረጃ የማዕድን የማምረት ስራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኝ ቢሆንም የሚከፍለው የሮያልቲ መጠን ግን በቀድሞው ጊዜ ማለትም በ1986ዓ.ም ለማዕድን ሥራዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 182/1986 እና በመጀመሪያው በተዋዋለው ውል መሠረት መሆኑን ከድርጅቱ በተገኘ ማስረጃና ለሥራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ የማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 አንቀፅ 81 ንዑስ አንቀፅ 1 ይህ አዋጅ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠ ፈቃድ ወይም የተደረገ የማዕድን ስምምነት ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረነ ድረስ ፀንቶ ለሚቆይበት ቀሪ ዘመን ተፈፃሚነቱ ይቀጥላል ቢልም እንዲሁም በንዑስ አንቀፅ 2 ደግሞ ይሄ ድንጋጌ ቢኖርም አንደኛው ወገን አግባብ ባለው ስምምነት በሚያካሂደው ስራ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ጉዳት የደረሰበት ወገን ሲጠይቅ ሁለቱም ወገኖች በቅን ልቦና ተወያይተው አስፈላጊውን ማስተካከያ ለማድረግ ሊስማሙ እንደሚችሉ ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ለአዋጅ ቁጥር 53/1985 በወጣው አዋጅ ደንብ ቁጥር182/1986 እና 678/2002 በሮያልቲእና በመንግስት ነፃ ድርሻ አከፋፈል አንቀፅ 63 እና 70 ላይ ሲታይ ግን ድርጅቱ በሚከፍለው ክፍያ በከፍተኛ ሁኔታ የሚቃረን በመሆኑ እንዲሁም የሀገር ጥቅም ከግምት ውስጥ ሳይገባ በአንድ ድርጅት አቤቱታ ብቻ ሚ/ር መ/ቤቱ ስምምነት በመፈፀም እስከ ታህሳስ/2005 ዓ.ም በ5% መክፈል ሲገባው በ2% በመክፈሉ ከመንግስት ነፃ ድርሻ ብቻ ብር 108,714,304.425 እንዲሁም እስከ መጋቢት/ 2006 ደግሞ 67,466,917.44 በድምሩ ከመንግስት ነፃ ድርሻ ገቢ ብር 176,181,221.87 ሀገርቷ ያጣች መሆኑ ታውቋል፡፡

124. እንዲሁም ከከበሩና በከፊል ከከበሩ የሮያልቲ አከፋፈልን በተመለከተ የቀድሞ አዋጅ ላይ ለከበሩ 5% እና በከፊል ለከበሩ ያልተገለፀ ሲሆን፣ በአዋጅ ቁጥር 678/2002 ደግሞ 8%ና 6%

ቢልም ከሚድሮክ ጎልድ ከከበሩና በከፊል ከከበሩ ማዕድናት ላይ ሮያሊቲ በ5% ብቻ በመሰብሰቡ ከ2004-2006 በጀት ዓመት ከወርቅ በ3% ማለትም ብር 252,961,236.45 እንዲሁም ከብር በ1% ማለትም ብር 413,394.46 በድምሩ 253,374,630.91 የሮያሊቲ ገቢ አገሪቷ ያጣች መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

125. በተጨማሪም ሚድሮክ ጎልድ ምርት በ2000 ዓ.ም የጀመረ ቢሆንም ሚ/ር መ/ቤቱ በየወቅቱ ተከታትሎ ሂሳባቸውን እንደማይመረምር ታውቋል፡፡ይህም በመሆኑ በሮያሊቲ ስሌት ጊዜ የሚመጡ ልዩነቶች ቶሎ ለመንግስት ገቢ ለማድረግ እንደማያስችል ለመረዳት ተችሏል፡፡

126. በዚህ ዙሪያ የብሄራዊ ባንክ የከረንሲ ማነጅሜንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለሮያሊቲ መከፈልና አለመከፈል ማረጋገጥ የብሄራዊ ባንክ የስራ ድርሻ እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡

127. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በባህላዊ መንገድ ከሚመረቱት ታንታለምና ጀሚስቶንን በተመለከተ የሮያሊቲ ክፊያ እየተሰበሰበ እንደሚገኝ፣ በተጨማሪም ባለፈቃዶች ወደ ውጭ ከከበሩና በከፊል ከከበሩ ማዕድናትን መላክ ሲፈልጉ ሚ/ር መ/ቤቱ ሮያሊቲ ስለመክፈላቸው ማስረጃ እንደሚጠይቅና ካልከፈሉ የክልል ማዕድን ቢሮዎች እንዲያስከፍል በስልክ እንደሚያገኛቸው ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ወርቅን በተመለከተ በሁሉም ክልሎች በተሟላ መልኩ ሮያሊቲ እንደማይሰበሰብ አስረድተዋል፡፡ ይሄንን ለማስከፈል ህግ ያወጡ ክልልሎች ቢኖሩም እንኳ ወርቅ አምራቾች ወርቅን በደረሰኝ ስለማይሸጡ ለመሰብሰብ እንዳልተቻለ ተገልጿል፡፡ ሆኖም ግን በአዋጅ ላይም የክልል ማዕድን ቢሮዎች ሮያሊቲ እንዲሰበስቡ፣ የሮያሊቲ ሂሳብ እንዲመረምሩና ባለፈቃዶች የመንግስት ገቢ ስለመክፈላቸው ክትትል እንዲያደርጉ ኃላፊነት የተሰጠው ለክልሎች በመሆኑ ክልሎችም ባለመወጣታቸው ይሄ ችግር ከሚ/ር መ/ቤቱም አቅም በላይ እየሆነ መሆኑን፣ በከፍተኛና በዝቅተኛ ደረጃ የሚሰጡ ፈቃዶችን ሮያሊቲ አሰባሰብን በተመለከተ በተመለከተ በዝቅተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ /small scale/ የክልል ማዕድን ቢሮዎች ሮያሊቲ የሚሰበስቡና የመሬት ኪራይስለመክፈሉ እንደሚከታተሉ ኃላፊነት እንደተሠጣቸው፤ ሆኖም ግን ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ስራ ፈቃድን በተመለከተ ፈቃዱ ከሚ/ር መ/ቤቱ ስለሚሰጥ ሮያሊቲ የሚሰበሰበው በሚ/ር መ/ቤቱ መሆኑን ግብርና የመንግስት ነፃ ድርሻ ግን በሌላ አካላት እንደሚሰበሰብ፡፡ በተጨማሪም የሚድሮክ ወርቅን በተመለከተ ግን የሮያሊቲና የመንግስትነፃ ድርሻ ክፊያዎች ብቻ ሳይሆን ከግብር ነፃ ዕቃ ማስገባትንም በተመለከተ እስካሁን ግብር ሳይከፍል በድሮ አዋጅ የሚያስገቡ መሆኑ ይህ የሆነው ግን ድርጅቱ በቀድሞ ደንብ ቁጥር 182/1989 ስምምነት ስለፈጸመ አዲስ አዋጅ ቢወጣም ከበላይ ኃላፊዎች ጋር በመወያትና ስምምነት በመፈፀም በዛው እንዲቀጥል መደረጉን ገልፀዋል፡፡

128. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ ላይ ክልሎች ከአዋጅ 678/2002 ተነስተው ሮያሊቲ ህግ የማውጣት ኃላፊነት የተሰጣቸው በመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 678/2002 በአንቀጽ 23/3 የተቀመጠ መሆኑን፣ በተጨማሪም ፈቃድ ሰጪው በሰጠው ፈቃድ ሮያሊቲ እና ግብር ማስከፈል ኃላፊነት እንዳለው፣ በክልሎች የሚታየው ክፍተቶች ተቀናጅቶ ካለመሥራትና ከአደረጃጀትና ከሰው ኃይል አለመኖር ሲሆን ሌሎች ችግሮችም ተያያዥ መሆናቸውን፣ እንዲሁም የገቢ ግብር የመሰብሰብ ስልጣኑ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ካፓኒዮችን አገልግሎት ሲጠየቁ ክፍያ የፈፀሙበትን ማስረጃ መጠየቃቸው፣ በተጨማሪም አዘዋዋሪዎች ከሕጋዊ ወደ ሕገ ወጥ ሥራ መዞር፣ ወርቅ ባንክ አለማስገባት፣ ግብር ላለመክፈል ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል በስውር ማሻገርና በሌሎች ግሮች ምክንያት ወርቅ ብሔራዊ ባንክ ያልገባበትን ማነቆ በመለየት ለማስተካከል ከክልሎች ጋር በጋራ በመሆን የማስተካከል እምርጃ እየተወሰደ መሆኑን፣ከዚህም በተጨማሪ የክልል ማዕድን ቢሮዎች እና ሚ/ር መ/ቤቱ ሮያሊቲ ማስከፈልን በተመለከተ በኦሮሚያ የቀረበው በዚህ ዓይነት ችግር ተያያዥ ያለውና ክልሎች ሀብቱን ባለመቆጣጠራቸው አንደኛው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በክልሎች ያለው ሮያሊቲ ያለማስከፈል ችግር ብቻ ሳይሆን ለማዕድናቱ ተመጣጣኝ ዋጋ በማድረግ ተመጣጣኝ ሮያሊቲ አለማስከፈል ችግር መሆኑ፣ ፈቃድ ሲታደስ ሮያሊቲ በየዓመቱ ማስገባት ግዴታ መሆኑን እና ከአጎራባች ክልሎች በአዘዋዋሪ የገባውን ወርቅ በማስላት ገቢ ማጣት ብቻ ሳይሆን ክልሎች ማዕድኑ ሲመረት መዝግቦ የማስከፈል ኃላፊነት እንዳላቸው ሆኖም ግን ክልሎችም የተደራጀ አሠራር ባለመዘርጋታቸውና የክትትልና ቁጥጥር ክፍተቶች በመኖራቸው ሚ/ር መ/ቤቱ ይህ ተግባራዊ እንዲደረግ በተለያየ ጊዜ ጥረት እያደረገ መገኘቱን ገልጸዋል፡፡

129. እንዲሁም የኢትኖ ማይኒግ እና የአኮቦ ማይኒግ ፈቃዶች መደራረብ ሁኔታን በተመለከተ ጉዳዩ በፍርድ ሂደት ላይ በመሆኑ አስተያየት መስጠት እንደሚያስቸግር የገለፁ ሲሆን በክልሉ ማህበራት /ባለፈቃዶች/ በወርቅ ምርት 3% ሮያሊቲ እንዲከፍሉ የተወሰነ ከሆነ አለማስከፈል የክልሉ ችግር መሆኑን ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ችግሮች በመለየትና አሠራሮችን በማስተካከል ከ2002-2005 ዓ.ም. ግብር በማስከፈል ላይ መሆናቸውን፣ በ2005 እና 2006 በጀት ዓመት የመሬት ኪራይ ያልተከፈለባቸውን በተመለከተ ባለፈቃዶች መኖቸው በመረጃ የተደገፈ ከክልል ማዕድን ቢሮዎች ከቀረበ በቀጣይ ማስተካከያ የሚያደር ጉበት መሆኑን፣ በተጨማሪም የሚድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት የሚገኝ ሲሆን አዋጅ 678/2002 ከመውጣቱ በፊት በነበረው ስምምነት በከፍተኛ ደረጃ ውይይት ተደርጐበት በተወሰነው መሠረት ግብር/ሮያሊቲ/ በመክፍል ላይ መሆኑን እንዲሁም በሌላ በኩል ከመንግሥት ነፃ ድርሻ አለማስከፈልን በሚመለከት በሁሉም ድርጅቶች ባለጀመሩ ሚ/ር

መ/ቤቱ አሠራሮች ለማስተካከል አዋጅና ደንብ በማውጣት ላይ እንደሚገኝ እንዲሁም ፈቃድ ላላሳደሰ ግለሰብ ወይም ድርጅት አገለግሎት እንደማይሰጥ እንዲሁም ስለሮያሊቲ መከፈልና አለመከፈል ማረጋገጥ የክልል ኃላፊነት እንደሆነና ከኦሮሚያ ክልል ወደ 20 የሚሆኑ የወርቅ አዘዋዋሪዎች ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ የግዥ ጣቢያዎች ወርቅ ከሚያቀርቡ አዘዋዋሪዎች መኖራቸው ከክልሉና ከብሔሪዊ ባንክ ለማጣራት ሚ/ር መ/ቤቱ መረጃውን ከኦዲት ቡድኑ ቢያገኝ ለመከታተል ሙከራ እንደሚያደርግ ገልፀዋል፡፡

130. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች በአዋጁ ላይ በተሰጣቸው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት የሮያሊቲ ፣ የመሬት ኪራይ እና ሌሎች ክፍያዎች ሂሳብ በወቅቱ እንዲሰበሰቡና ሂሳባቸው እንዲመረመር ባለማድረጋቸው ከዘርፉ ሊገኝ የሚገባውን ከፍተኛ ገቢ እንዳይገኝ ማድረጉን ለመረዳት ተችሏል፡፡

<u>**ሮያሊቲ በወቅቱ ባልከፈሉ፣ ሮያሊቲ ያልተከፈለበት ማዕድን በገዙ ግለሰቦች ላይ እርምጃ መውሰድን በተመለከተ፣**</u>

131. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውም ባለፈቃድ ሮያሊቲ በወቅቱ ካልከፈለ፣ ሮያሊቲ ያልተከፈለበት ማዕድን ከገዛ፣ በማዕድን አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ መሰረት መቅረብ ካለባቸው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትክክል ያልሆነ ወይም የሚያሳስት መረጃ አቅርቦ ከተገኘ እንዲቀጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

132. በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 መሠረት ማንኛውም ባለፈቃድ ሮያሊቲ በወቅቱ ካልከፈለ፣ ሮያሊቲ ያልተከፈለበት ማዕድን ከገዛ፣ በማዕድን አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ መሰረት መቅረብ ካለባቸው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትክክል ያልሆነ ወይም የሚያሳስት መረጃ አቅርቦ ከተገኘ እስከ ብር 200,000 የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ 5 ዓመት በሚደርስ እስራት ወይም በሁለቱም እንዲቀጡ ቢደነግግም በሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ በክልል ማዕድን ቢሮዎች ተፈፃሚ እየሆነ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

133. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ሶስቱም ክልሎች በደቡብ ፣በኦሮሚያ እና በትግራይ ክልሎች የሮያሊቲ አሰባሰብን በተመለከ የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ /ግብር/ ክፍያ ሙሉ በሙሉ ያልከፈሉ፣ ሮያሊቲ ያልተከፈለበት ማዕድን የሚገዙ እና በማዕድን ስራዎች አዋጅ መሰረት ከተሰጣቸው የምርት ቦታ ውጭ የሚሰሩ ባለፈቃዶች ቢገኙም እስካሁን ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ክልሎች ምንም ዓይነት እርምጃ አለመውሰዳቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

134. ይህም በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከደቡብ ክልል በሲዳማ ዞን ከታዩት አራት የወርቅ አምራችና አዘዋዋሪ ባለፈቃዶች ውስጥ ከ 1996ዓ.ም ጀምሮ የማምረት ፈቃድ ያገኙ ቢሆንም

3 የወርቅአምራቾች ከ2004-2006 ዓ.ም ላመረቱት የወርቅ ማዕድን ሮያሊቲ ከፍለው የማያውቁ እንዲሁም ሮያሊቲ ያልተከፈለበትን ማዕድን ከሌላ የወርቅ አምራች ማህበር ገዝቶ ለብሄራዊ ባንክ የሚያቀርቡ መሆኑ እንዲሁም ከግንዛቤ ችግር በቤሮ ወረዳ ላይ አምራቹም አዘዋዋሪውም ሮያሊቲ የሚከፍሉ መሆኑ፣

135. በኦሮሚያ ክልል በጉጂ ዞን በኦዳ ሻክሶ ወረዳ በመሬት ኪራይ ክፍያ ዙሪያ በፊት ህገ ወጥ ግለሰቦቹ ሲከፍሉበት እንደነበረ በማስመሰል ህገ-ወጥ ደረሰኝ ተዘጋጅቶ (ተመሳሳይ የደረሰኝ ቁጥር ያላቸው ለምሳሌ 42608፣ 42638ና 42645) በአንድ ጊዜ በተለያዩ ባለስልጣናት የተፈረመ እና ከመንግስት ግብርም አንፃር ከፍተኛ ስህተት የሚያስከትል ማስረጃ/ደረሰኝ/ መገኘቱ፤ እንዲሁም የትግራይ ክልል አምራቾች ለአመረቱት የወርቅ ምርት ሮያሊቲ እንዲከፍሉ ህግ ቢያወጣም በህጉ መሠረት አምራቾች እንደማይከፍሉ፣ እና አዘዋዋሪዎችም ሮያሊቲ ያልተከፈለበትን ወርቅ ከህገወጥ አምራች ገዝተው ወደ ባንክ እንደሚያቀርቡ ለማወቅ ተችሏል፡፡

136. በዚህም ዙሪያ በአቅም ውስንነትና በፀጥታ ችግር ምክንያት ምንም እርምጃ አለመወሰዱን የደቡብና የትግራይ የማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

137. ስለጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ችግር እንዳለና የባህላዊ ማዕድናትን በተመለከተ እርምጃ መውሰድ የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊነት እንዳልሆነና የክልል ማዕድን ቢሮዎች ድርሻ መሆኑን ነገር ግን ሚ/ር መ/ቤቱ በህጋዊ መንገድ ያልተደራጁትን በህጋዊ መንገድ እንድደራጁ ተሸከረካሪ እና የመሳሰሉ ድጋፎችን ለክልል ቢሮዎች እንደሚሰጥ፣ እንዲሁም በከፍተኛና በመካከለኛ ደረጃ የሚመረቱትን በተመለከተ ግን የተጠበቀው ምርት ባለመኖሩ የሚጠበቀው ያህል ሮያሊቲ ላይሰበሰብ እንደሚችል፡፡ ሆኖም ግን የመሬት ኪራይን በተመለከተ የሚ/ር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊነት /ማንደት/ ባይሆንም እንኳ ክልል የመንግስት አካል በመሆኑ ባለፈቃዶቹ ከሚ/ር መ/ቤቱ ድጋፍ ሲፈልጉ ስለመክፈላቸው እንደሚጠይቁ ባለሞያዎችም ወደ ክልል ለመስክ ስራ ሲሄዱ እንደሚከታተሉ፣ ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ ግን እየተፈፀመ ነው ለማለት እንደማያስችላቸው፣ የኢትዮ ማይኒግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ስቴላ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል/ማ ከሚ/ር መ/ቤቱ ወደ ክልል የተሟላ ማስረጃ በኮፒ እንደተላለፈ በተጨማሪም ፈቃዱ ከሚ/ር መ/ቤቱ ተላልፎ ወይም ፈቃዱ ተሰርዞ የተሟላ ማስረጃው ለክልል ማዕድን ቢሮዎች ያልተላለፈ አለመኖሩን፡፡ እንዲሁም ክልሉም ማስከፈል ከፈለገ መጠየቅ እንደሚችል፡፡ ነገር ግን በሁለት ክልሎች ድንበር ያለው ፈቃድ ቦታ ለአንድ ባለፈቃድ ሲሰጥ እንደ ሀገር በስራ ላይም ችግር እያመጣባቸው እንደሆነ ይህንን በተመለከተም የሚመለከታቸው አካላትን አነጋግረው ተገቢውን ምላሽ እንዳላገኙ ገልፀዋል፡፡

138. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ /ግብር/ ክፍያ ሙሉ በሙሉ ባለመከፈሉ ችግሮች ቢኖሩም ሮያሊትን በተመለከተ አምራቾች ሮያሊቲ እንዲከፍሉ በህግ ላይ የወጣና ክልሎች አሰራሮችን ዘርግተው ያለመስራት ችግር እንዳለ፤ ሆኖም ግን ይህንን ለማቃለል ክልሎችና ሚ/ር መ/ቤቱ በጋራ በመስራት ለክልሎች አደረጃጀት፣ የሰው ኃይልና የማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ የማስተካከል ሥራ ሚ/ር መ/ቤቱ መስራት እንዳለበት ነገር ግን ክልሎች የማስከፈል ኃላፊነት ያላቸው ቢሆንም ክፍተት ካለም መረጃዎችን በመያዝ እንዲያስተካክሉ ጥረት እንደሚደረግ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ያሉትን ህገ ወጥ አምራቾችንና ህገወጥ ደረሰኞችን በተመለከተ የክልሉ ድርሻ ቢሆንም ለወደፊት ለማጣራት እንደሚሞክሩ ገልፀዋል፡፡

139. ይሁን እንጂ በሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ በክልል ማዕድን ቢሮዎች/ዞኖችና ወረዳዎች/ ከማዕድኑ የሚገኙ ገቢ ላይ በቂ ትኩረት እንዳልተሰጠው ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ሐ.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

<u>የከበሩ ማዕድናትግብይትን ለማካሄድ አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ስለማግኘት እና ፈቃዱን ማሳደስ የሚችለው በየአንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ መሆኑን በተመለከተ፤</u>

140. ማንኛውም ሰው የከበሩ ማዕድናት(ወርቅ) ግብይትን ለማካሄድ የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣው በ651/2001 አዋጅ መሰረት አግባብ ባለው ፈቃድ ሰጪ አካል ቀርቦ በንግድ መዝገብ በመመዝገብ የተሰጠ የጸና ፈቃድ ወይም የታደሰ የከበሩ ማዕድናት (ወርቅ) ንግድ ሥራ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡

141. የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁ. 651/2001 ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው መ/ቤት ቀርቦ በንግድ መዝገብ ሳይመዘገብ እና የጸና ፈቃድ ሳይኖረው የከበሩ ማዕድናት ግብይት ማካሄድ አይችልም ቢልም፤በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎች እና ፋይላቸው ከሚ/ር መ/ቤቱ ቀርቦ በተከለሱ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በትግራይ፣ በአማራ እና በጋምቤላ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ አግባብ ባለው መሥሪያ ቤት ቀርበው በንግድ መዝገብ ሳይመዘገቡና የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣው በአዋጅ 651/2001 መሰረት የተሰጠ የጸና ፈቃድ ሳይኖራቸው የከበሩ ማዕድናትን ግብይት እያካሄዱ የሚገኙ ህገ ወጥ ግለሰቦች መኖራቸው ታውቋል፡፡

142. በዚህ ዙሪያ  የክልል የማዕድን ኢነርጂ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የክልል የማዕድን ቢሮ የመቅጫ ህግ ባለማውጣቱ  ፈቃድ ሳይዙ የተጭበረበረ ሚዛን ይዘው ወደ ገበያ የሚገቡ አዘዋዋሪዎች እንዲሁም በህገወጥ መንገድ ወርቅና የወርቅ መጠቆሚያ መሳሪያ የሚያዘዋውሩ ግለሰቦች መኖራቸውና ከገበያ እንዲወጡ ጥረት ቢደረግም ችግሩ ሊፈታ እንዳልቻለና ዝርዝራቸውም በውል  እንደማይታወቅ እንዲሁም ምንም እርምጃ እንዳልተወሰደባቸውና እርምጃ ለመውሰድም እንደማይችሉ ገልጸዋል፡፡

143. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በማዕድን ሥራ ከፍተኛ ኮንትሮባንድ ያለበት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን መንግሥትና የሚመለከታቸው መ/ቤቶች ለማስተካከል በጋራ ለመስራት በሂደት ላይ መሆናቸውን እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ቢሮዎች፣ ክልሎች፣ የፀጥታ ኃይሎች በመተባበር የመሥራትና ግንዛቤ የመስጠት እና  ሁሉም ቢሮዎች ክትትል እንዲያደርጉ የማስተባበር ድጋፍ የማድረግ ሥራ በመሥራት ላይ እንደሚገኝ በተጨማሪም መ/ቤቱ ጥቆማ ሲደርሰው በአዋጁ መሠረት ማስፈረድና ለህገወጦችም ትምህርት እንዲሆን በተሰጠው ኃላፊነት እየተወጣ መገኘቱንና ችግሮቹ ቀጣይ በመሆናቸው አሰራሮችን በመዘርጋት በጋራ መሥራት አስፈላጊ መሆኑ፣

144. እንዲሁም ለባንኩ የሚያቀርቡት ወርቅ አቅራቢዎች በህጋዊ የሚሰሩ ሲሆን፤ ፈቃድ ማሳደስንና አለማሳደስ ደግሞ የክልሎች በመሆኑ ባንኩ ከክልሎችና ከማዕድን ሚኒስቴር የተፈቀደላቸውን የአዘዋዋሪዎች ወርቅ መቀበልና ወደ ውጭ መላክ በቂ ሥራ ሲሆን ፈቃድ የሰጡ ክልሎች ፈቃዱ ሰርዘው ለባንኩ ቢልኩ ባለፈቃዶቹ ማስገባት እንደማይችሉ በመሆኑም በባንኩ የተሰጠው አስተያየት ለወደፊቱ መ/ቤቱ ለማየትና ለማስተካከል የሚሞክር መሆኑን፣ በደቡብ፣ በትግራይና በኦሮሚየ ክልልሎች የተነሱት የፈቃድ አለማሳደስ የመንግሥት አካል ፈቃድ ሳያገኙ ህገ ወጥ አምራች፣ ህጋዊ ፈቃድ የሌላቸው መሥራት፣ በህገወጥ መንገድ ወርቅ ሲያዘዋውሩና ሌሎች ችግር የክልሎች ክትትል ክፍተት መሆኑና ሚ/ር መ/ቤቱ ችግሮች እንዲስተካከሉ ድጋፍና ማስተባበር ግዴታ በመኖሩ ከክልሎች ጋር ሥራዎችን ለመሥራትና በጋራ ለመንቀሳቀስ ዕቅድ መያዙን እንዲሁም  ህገወጦችን ለመቆጣጠር መረጃ በመያዝ በቀጣይ ማጣራት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

145. ይሁን እንጂ ለወደፊት ህገ-ወጦች የማዕድን ገበያውን በመቆጣጠር በግብይቱ ላይ ተፅዕኖ እንደሚፈጥሩ እና በክልል ማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲዎች/ ቢሮዎች ላይም ስጋት ማሳደሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡

**ፈቃድ ሰጪ አካላት በማዕድን ህጎች መሰረት የማዕድን ፈቃድ ስለማደሳቸው እና ግዴታቸውን ባልተወጡ ባለፈቃዶች ላይ እርምጃ መውሰዳቸውን በተመለከተ፣**

146. ሚ/ር መ/ቤቱ እና የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋት በወጣው አዋጅ እና በማዕድን ስራዎች አዋጅ፣ በደንብና በመመሪያ መሰረት የማዕድን ፈቃድ ሊያድስ ፣ ባለፈቃዶቹ በአዋጁ መሰረት ግዴታቸውን ካልተወጡ ፈቃዱን ሊያግድና ሊሰርዝ እንዲሁም በፈቃድ ወይም በፈቃድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ከተመለከተው ውጭ ከተሰማሩ፣ ከግለሰብ የሚሰበስባቸውን የወርቅና ብር መጠን ሪፖርት ካላደረጉ እና ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሳይኖራቸው የከበሩ ማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ ከተሰማሩ በተቀመጠው ህግ መሰረት እርምጃ ሊወስዱ ይገባል ፡፡

147. በአዋጅ ቁጥር 651/2005 አንቀጽ 17/2 መሠረት የከበሩ ማዕድናት የንግድ ብቃት ማረጋገጫ ባለፈቃዶች ሰርተፊኬታቸውን(ፈቃዳቸውን) በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ማሳደስ እንዳለባቸው እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ እና የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት በማዕድን ስራዎች አዋጅ፣ በደንብ እና በመመሪያ መሰረት የማዕድን ፈቃድ ሊያድሱ እንደሚገባ ቢገልፅም በሚ/ር መ/ቤቱ እና በናሙና በታዩት በደቡብ፣በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች ውስጥ በሶስቱም ክልሎች ፈቃድ ወይም የፈቃድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው የማዕድን ባለፈቃዶች በየአንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ ፈቃዳቸውን እንደማያሳድሱ ታውቋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ከ2004-2006 በጀት ዓመት በትግራይ 119 ባለፈቃዶች፣ በኦሮሚያ 53 ባለፈቃዶች እንዲሁም በደቡብ ክልል 8 የአዘዋዋሪ ባለፈቃዶች ፈቃዳቸውን በእያንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ ሳያሳድሱ ግብይት በማከናወንና ለባንኮችም ወርቅ በማቅረብ ላይ መሆናቸው ታውቋል፡፡

148. ሚ/ር መ/ቤቱ እና የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋት በወጣው አዋጅ እና በማዕድን ስራዎች አዋጅ፣ በደንብና በመመሪያ መሰረት የማዕድን ፈቃድ ሊያድስ ፣ ባለፈቃዶቹ በአዋጁ መሰረት ግዴታቸውን ካልተወጡ ፈቃዱን ሊያግድና ሊሰርዝ እንዲሁም በፈቃድ ወይም በፈቃድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ከተመለከተው ውጭ ከተሰማሩ፣ ከግለሰብ የሚሰበስባቸውን የወርቅና ብር መጠን ሪፖርት ካላደረጉ እና ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሳይኖራቸው የከበሩ ማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ ከተሰማሩ በተቀመጠው ህግ መሰረት እርምጃ ሊወስዱ ይገባል ፡፡

149. በአዋጅ ቁጥር 651/2005 አንቀጽ 17/2 መሠረት የከበሩ ማዕድናት የንግድ ብቃት ማረጋገጫ ባለፈቃዶች ሰርተፊኬታቸውን(ፈቃዳቸውን) በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ማሳደስ እንዳለባቸው እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ እና የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት በማዕድን ስራዎች አዋጅ፣ በደንብ እና በመመሪያ መሰረት የማዕድን ፈቃድ ሊያድሱ እንደሚገባ ቢገልፅም በሚ/ር

መ/ቤቱ እና በናሙና በታዩት በደቡብ፣በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች ውስጥ በሶስቱም ክልሎች ፈቃድ ወይም የፈቃድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው የማዕድን ባለፈቃዶች በየአንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ ፈቃዳቸውን እንደማያሳድሱ ታውቋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ከ2004-2006 በጀት ዓመት በትግራይ 119 ባለፈቃዶች፣ በኦሮሚያ 53 ባለፈቃዶች እንዲሁም በደቡብ ክልል 8 የአዘዋዋሪ ባለፈቃዶች ፈቃዳቸውን በእያንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ ሳያሳድሱ ግብይት በማከናወንና ለባንኮችም ወርቅ በማቅረብ ላይ መሆናቸው ታውቋል፡፡

150. እንዲሁም በማዕድን ስራዎች አዋጅ እና በደንብ መሰረት በሚ/ር መ/ቤቱ በከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ መሠረት ከ2002 ዓ.ም ጀምረው በባሕላዊ ምርትና ግብይት ማስተባበሪያ ፈቃድ የወሰዱ ባለፈቃዶች ቢኖሩም ፈቃድ የማደስ ሥራ በዕቅድ መሠረት አለመሠራቱና በባህላዊ መንገድ ፈቃድ ሰጥቶ ከሚያስተዳድራቸው ዘጠኝ ዓይነት የማዕድን ፈቃዶች ውስጥ በስድስት የፈቃድ ዓይነቶች ላይ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ በመስራት ላይ ያሉ ባለፈቃዶች መኖራቸው፣ ፈቃዳቸውን ያሳደሱትም ከዕድሳት ጊዜው ከ4-7 ወራት በመዘግየት መሆኑን፣

151. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከፍተኛ ደረጃ በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ምርትና ምርመራ ላይ ከ1986 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2002 ዓ.ም ፈቃድ ካገኙት ውስጥ 90ዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሠጣቸውን የቆይታ ጊዜ ጨርሰው በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ ከ1 እስከ 15 ዓመታት ፈቃዱን ይዞ በመቆየት በመሥራት ላይ መሆናቸው እንዲሁም 14ቱ ደግሞ በአዋጅ 678/2002 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀስ 1 ላይ በተጠቀሰው መሠረት የመጀመሪያ የፈቃድ እድሳት ከ1 እስከ 5 ዓመት በመዘግየት ያሣደሱ መሆኑ እንዲሁም ሌሎች ሶስት ባለፈቃዶች ደግሞ የፈቃድ ዘመናቸው ከተቃጠለ ከ3-6 ዓመታት ያስቆጠሩ ቢሆንም ፈቃዱ ያልተሰረዘ ወይም ያልታገደ መሆኑ፤

152. ከዚህም ሌላ በኦሮሚያ ክልል በጉጂ ዞን በአዶ ሻክሶ ወረዳ ከተገኘው የ65 ባለፈቃዶች ዝርዝር ውስጥ የማዕድን ፈቃዳቸውን አሳድሰው የማያውቁ 39 (60%) ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ፈቃድ የወሰዱ ባለፈቃዶች እንዳሉ ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

153. በደቡብ ክልል ፈቃድ ከተሰጣቸው 97 የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ባለፈቃዶች ውስጥ 81ዱ (84%ቱ) ባለፈቃዶች ፈቃዳቸው ስለመሰረዙ እና ስላለመሰረዙ ምንም ዓይነት ማስረጃ በክልሉ አለመገኘቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

154. በአዋጅ ቁጥር 678/2002 መሰረት ሚ/ር መ/ቤቱ እና የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት በማዕድን ስራዎች አዋጅ፣ በደንብ እና በመመሪያ መሰረት የማዕድን ፈቃድ ባላሳደሱ እንዲሁም

ባለፈቃዶቹ በአዋጁ መሰረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ፈቃዳቸውን አለመሰረዛቸው ወይም አለማገዳቸው ታውቋል፡፡

155. በዚህ ዙሪያ በክልል የሚገኙ ባለፈቃዶች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሳያሳድሱ ወርቅ ባንክ አቅርበው እንደሚሸጡና ከፈቃዱ ዘመን በላይ እንደሚጠቀሙ ለዚህም የጠየቃቸው አካል እንደሌለ ባለፈቃዶቹ ገልጸዋል፡፡

156. እንዲሁም ከክልል ማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ በሚሰሩትና ፈቃዳቸው ከተሰረዘ በኃላ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ምርት የሚያመርቱ ባለፈቃዶች ላይ በማዕድን ስራዎች ደንብ ቁጥር 182/1986 መሰረት ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ መቀጮ በመጣል ማስከፈል እንደጀመሩ ቢገልፁም ስለተግባራዊነቱ በክልሉ ማስረጃ አለመገኘቱ ታውቋል ፡፡

157. ይህንን በተመለከተ የክልል ማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ፈቃድ የተሰጣቸው ባለፈቃዶች ሆነው በየአንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ ፈቃዳቸውን ያላሳደሱ ወይም አሳድሰው የማያውቁ መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡በማዕድን ስራዎች አዋጅ ግዴታቸውን ያልተወጡ ባለፈቃዶችም ያሉ ቢሆንም በተጨማሪም በህገወጥ መንገድ ከህገወጦች ላይ የወርቅ ግዥ የሚፈጽሙ አዘዋዋሪዎች መኖራቸውና ወርቁን ግን ለብሔራዊ ባንክ ቅርንጫፍ እንደሚያቀርቡ ቢታወቅም የትግራይ ክልልን በተመለከተ ያላሳደሱትን ለመቅጣት ስለማይችሉ የማደሻ ጊዜውም ቢያልፍ ያለቅጣት እንደሚያድሱላቸው ገልፀዋል፡፡እንዲሁም በደቡብ ክልል ደግሞ ባለማሳደሳቸውም ክልሉ ፈቃዳቸውን ለመሰረዝ ጉዳዩ የፀጥታ ችግር እንደሚፈጥርና እርምጃ ለመውሰድ እንደተቸገሩ የገለፁ ሲሆን፤ ይህም በመሆኑ ፈቃዳቸውን ባለማሳደሳቸው ምክንያት አዘዋዋሪዎችም ወርቅ ከየት እንደሚገዙ አጣርቶ የሚፈለግባቸውን ክፍያዎች ለማስከፈል አለመቻላቸውን ገልፀዋል፡፡

158. ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የከረንሲ ማኔጅመንት ዳይሮክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው ወርቅ አቅራቢዎች የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣው በአዋጅ 651/2001 መሰረት የተሰጠ የጸና ፈቃድ እንዳላቸው መጠይቅን በተመለከተ በብሄራዊ ባንክ መመሪያ /know your customer directive/ መሠረትና ደንበኛው ፈቃድ እንዳለውና እንደሌለው የመግባቢያ ሰነድ /memorandum of association/ ባለፈቃዱስ ማነው የመሳሰሉት ከተረጋገጠ በኃላ የደንበኝነት ምዝገባ አግኝቶ እንደሚመዘገብ እና ማስረጃውም ለኦዲት እንደሚቀርብ እንዲሁም ፈቃድ ላላሳደሰ ግለሰብ ወይም ድርጅት አገልግሎት እንደማይሰጥ የገለፁ ቢሆንም ማስረጃው አለመቅረቡ፤ ከዚህም በተጨማሪ ለኢትዮጵ ብሔራዊ ባንክ አዋሣና ሽሬ የወርቅ ግዥ ጣቢያ የስራ ኃላፊዎች የወርቅ

አዘዋዋሪዎች ወርቅ ወደ ባንኩ ለመሸጥ ሲመጡ አዲስ ደንበኛ ካልሆነ በስተቀር በባንኩ ውል መሠረት የመጣውን ወርቅ ፈቃዱ ታደሰም አልታደሰም እንደሚረከቡ ገልፀው ፈቃድ ስለማሟደሟቸውና የማይጠይቁበትም ምክንያት ከብሔራዊ ባንክ በየጊዜው እንድጠይቁ መመሪያ ስላላስተላለፈላቸው እንደሆነና ኃላፊዎቹ ግን በራሟቸው መጠየቅ እንደሚየስፈልግ ተነጋግረው በአንዳንድ አቅራቢዎች ላይ ማየት መጀመራቸውን የገለፁ ቢሆንም፤ በኦዲቱ ወቅት 20 ባለፈቃዶች ፈቃድ ሳያድሱ ለአዋሳ የወርቅ ግዥ ጣቢያ ወርቅ የሚያቀርቡ መሆኑን ከባንኩ ከተከለሱ ፋይሎች ውስጥ ተገኝተዋል፡፡

159. ስለጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከክልል ማዕድን ቢሮዎች ፈቃድ የወሰዱትን በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤቱን እንደማይመለከት ገልፀው እንዲሁም በባህላዊ ማስተባበሪያ የተሰጠውን የፈቃድ እድሳትን በተመለከተ ፈቃድ አግኝቶ በእያንዳንዱ ፍቃድ ዘመን መጨረሻ ያላሳደሱ አክቲቭ የሆኑ ቢኖሩም በሰው ሀይል እጥረት ምክንያት ፈቃዳቸውን ለመሰረዝ እንዳልተቻለና በአሁኑ ወቅትም ዳይሬክቶሬቱ በአዲስ መልክ ተዋቅሮ የሰው ሀይል በመቅጠር እና ጥረት በማድረግ የማስተዳደር ስራ ውስጥ እየገባ መሆኑንና ለወደፊት የሚያስተካክሉ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ እንደዚሁም በፈቃድ አስተዳደር የተሰጡ ፈቃዶችን በተመለከተ አንድ ባለፍቃድ አክቲቭ ካልሆነ አዋጁ ተጨማሪ እውቅና ሳይሰጠው ባለፈቃዱ እንደተሠረዘ ይቆጠራል ቢልም ከበላይ ኃላፊዎች ጋር ተነጋግረው ለመሰረዝ ውሳኔ በመጠበቅ ላይ እንደሆኑና የተሠረዙትም ፈቃዶች በአዋጁ መሰረት የባለፈቃዱ ምክንያት መታወቅ ስላለበት ባለፈቃዶቹ ምክንያት እንዲያቀርቡ ኖቲፊኬሽን/notification/ በማዘጋጀት ላይ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በአዋጁ ላይ ፈቃድ መሰረዝ እንዳለበት እንጂ በምን መንገድ መሰረዝ እንዳለበት ግልጽ አለመሆኑን ሆኖም ግን ይህንን ጉዳይ ለማስተካከል ከሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ከክልል ማዕድን ቢሮዎች ተጨማሪ ስራ እንደሚፈልግ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም ክትትል ሊያደርግበት እንደሚገባና ለወደፊት ትኩረት ሰጥተው እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

160. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በአዋጅ ቁጥር 651/2001 መሠረት ባለፈቃዶች ፈቃዳቸውን ወይም ሰርተፊኬታቸውን በየአንደንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ የማያሳድሱ አልፎ አልፎ ቢኖሩም ችግሮቹን ለማስተካከል ከ2005 ዓ.ም. ጀምሮ እንዲያሳድሱ በማድረግ ላይ መሆናቸውን እንዲሁም የከበሩ ማዕድናት የንግድ ብቃት ማረጋገጫ 651/2001 አንቀጽ 17/2 በክልል ማዕድን ቢሮዎች የሚሰጡ ፈቃዶች አለመሆኑንና ከህግ ውጭ የሚሰሩ ባለፈቃዶች ቢኖሩም ዝርዝራቸው በተሟላ መልኩ በክልል ማዕድን ቢሮዎች አልተገኙም ለሚለው ህገ ወጥ ከሆኑ መረጃ ማግኘት የማይታሰብ መሆኑንና ከግለሰብ የሚሰበስቧቸውን ወርቅ መጠን ለፈቃድ ሰጪው የማያሳውቁ ባለፈቃዶችም ካሉ ክልሎች

መከታተልና እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት እንዳለባቸው በተጨማሪም በክልሎች ያሉ ባለፈቃዶች ተገቢውን ፈቃድ ወይም የፈቃድ ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ሳይኖራቸው የከበሩ ማዕድናት ግብይት ስራ ላይ በመሰማራት የከበሩ ማዕድናት የሚያዛውሩ ግለሰቦችን የመቆጣጠርና እርምጃ የመውሰድ ስራ የክልሎች መሆኑን ሆኖም ግን ሚ/ር መ/ቤቱ አሰራሮችን ለማስተካከልና ሁሉም ክልሎች አንድ ወጥ አሰራር እንዲዘረጉ ለማድረግ እንቅስቃሴ የጀመረ በመሆኑ የክልሎች የሰው ኃይል አደረጃጀት ከተስተካከለና ከአመራር ጀምሮ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት ከተቻለ ማስተካከል እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

161. ከዚህም በተጨማሪ በአዋጅ 678/2002 ባለው አሰራር ጥቅት ድርጅቶች በተለያዩ ምክንያቶች ባለፉት ዓመታት ፈቃድ ባለማሳደሳቸው ሚ/ር መ/ቤቱ ተከታታይ ጥናት በማድረግ አሰራሩን በማስተካከል ላይ እንደሚገኝና በሚ/ር መ/ቤቱ አሰራርም ፈቃዶች በየጊዜው ካልታደሱ እንደተሰረዙ ቢቆጠርም አሁን ባላደሱና ግዴታቸውን ባልተወጡ ድርጅቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ገልፀው፤ በሚ/ር መ/ቤቱ በባህላዊ ምርትና ግብይት ማስተባበሪያ ክፍል ፈቃድ የወሰዱ ባለፈቃዶች አለመኖራቸውን ሆኖም ግን በክልሎች ያሉ ያልተሰረዙትን ፈቃዶች በተመለከተ መረጃዎቹን የሰጡት የክልል ማዕድን ቢሮዎች በመሆናቸው ለማጣራት ቢያስቸግርም ከክልሎች መልስ የሚሹ ጉዳዮች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

162. ይሁን እንጂ የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት በሚ/ር መ/ቤቱ እንደሚሰጥ ቢታወቅም በእኛ አስተያየት አዋጅ ቁጥር 651/2001 አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 2 ማንኛውም ባለፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት የተሰጠው ሰው ፈቃዱን ወይም ሰርትፊኬቱን በእያንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ ማሳደስ እንዳለበት የሚገልፅ መሆኑን ለመረዳት የተቻለ ሲሆን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ አንፃር በዚህ መልኩ የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ሥርዓትና ዘላቂነት ባለው መንገድ መልማቱን በተሟላ ሁኔታ ለማረጋገጥ እንደማያስችል ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

<u>ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የወጪ ንግድና የጌጣጌጥ ማዕድናት በኮንትሮ ባንድ ንግድ እንዳይወጡ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣</u>

163. ሚ/ር መ/ቤቱ በባህላዊ አምራቾች የሚመረቱ የወጪ ንግድ ማዕድናት ወይም ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የጌጣጌጥ ማዕድናት በኮንትሮ ባንድ ንግድ ከሀገር ውጭ እንዳይወጡ የሚያደርግ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

164. ሚ/ር መ/ቤቱ በባህላዊ አምራቾች የሚመረቱ የወጪ ንግድ ማዕድናት ወይም ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የጌጣጌጥ ማዕድናት በኮንትሮ ባንድ ንግድ ከሀገር ውጭ እንዳይወጡ የሚያደርግ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት አልዘረጋም፡፡

165. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎች ውስጥ የማዕድን ህገ ወጥ ዝውውርና ግብይት አለመወገዱ፣ ህገ ወጥ የወርቅ አዘዋዋሪዎች እየተስፋፉ መምጣታቸው፣ ለህጋዊ ግብይቶች ህጋዊ ከለላ ከመስጠትና ኮንትሮባንድን ከመከላከል አኳያ የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑ፣ ክትትል አለመደረጉና በህገ ወጥ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ወርቆችን ለመቆጣጠር የፍተሻ ኬላና ዘመናዊ የፍተሻ መሳሪያ አለመኖሩ፣ ከዚህም በተጨማሪ  በኬላዎች ላይ የተጠናከረ ድንገተኛና መደበኛ ፍተሻ  አለመደረጉ እንዲሁም ሕገወጦች ላይ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ባለመሰራቱ የማዕድናት ምርትና ግብይት እንቅስቃሴ ከምርቱ ጀምሮ እስከ ግብይቱ ድረስነ ስርዓትን ያልተከተለ እንዲሆን ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

166. ጉዳዩን አስመልክቶ  የዕደ ጥበብ ባለፈቃዶች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ህገወጥ የወርቅ ነጋዴዎች በመሸጫ አከባቢያቸው ድረስ እንደሚሄዱ ይህንንም በተመለከተ ለማዕድን ሚ/ርና ለፖሊስ በተደጋጋሚ በደብዳቤ ቢያሳውቁም እንዲሁም በተጨማሪም ማዕድን ሚ/ር፣ ገቢዎችና ጉምሩክ እና ፖሊስ ባሉበት ስለጉዳዩ ቢወያዩም መፍትሔ እንዳላገኙና የማስተካከያ እርምጃ እንዳልተወሰደ ገልፀዋል፡፡

167. በዚህ ዙሪያ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አዲስ አበባ ኤርፖርቶች ቅርንጫፍ ፅ/ቤት የካርጎና የመንገደኞች ጓዝ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ  በአምራቾች የሚመረቱ የወጪ ንግድ ማዕድናት ወይም ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የጌጣጌጥ ማዕድናት በኮንትሮ ባንድ ንግድ ከሀገር ውጭ እንዳይወጡ የሚያደርግ ከማዕድን ሚ/ር ጋር በጋራ የተዘረጋ የቁጥጥርና የክትትል ስርዓት አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡ይሁንእንጂ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በራሱ አሰራር ወደ ሀገር የሚገቡና የሚወጡትን ማዕድናት ላይ ቁጥጥር ቢያደርግም በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ አለመሆኑን አስረድተዋል፡፡

168. በተጨማሪም ቅንጅታዊ ስራው  በጋራ ስምምነት ሰነድ ላይ አለመቀመጡ ፣ ሚ/ር መ/ቤቱ በቦሌ ኤርፖርት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በመንገደኞች ጓዝ በ2005 ዓ.ም እና በ2006ዓ.ም  በዝውውር ወቅት የተገኙት ማዕድንና ማዕድን መሰል ነገሮች ቢያዙም ሚ/ር መ/ቤቱ አብሮ እንደማይሰራ እና እንደማይከታተል ገልፀዋል፡፡ይሄ ጉዳይ ከሰራተኞቹ ዕውቀት

በላይ መሆኑን ከዚህም የተነሳ ማዕድኑም በሚያዝበት ወቅት ለረዥም ጊዜ የሚቆይ መሆኑና ሚ/ር መ/ቤቱም በባለቤትነት እየተከታተለ የመምራት ችግር እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

169. ይህንን በተመለከተ የክልል ማዕድን ቢሮ የስራ ኃላፊዎች በባህላዊ አምራቾች የሚመረቱ የውጪ ንግድ ማዕድናት ወይም ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የጌጣጌጥ ማዕድናት በክልሎች ቢመረቱም በኮንትሮባንድ ንግድ ከሀገር ውጭ እንዳይወጡ በክልሎች የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት አለመዘርጋቱን ገልፀዋል፡፡ ሥርዓቱም ባለመዘርጋቱ ወርቅ ወደ ሌላ ጎረቤት ሀገራት በእቃ በመለዋወጥ በሕገወጥ መንገድ እየወጣ መሆኑና ሀገሪቷ ማግኘት የሚገባትን ገቢና የውጭ ምንዛሪ እያገኘች አለመሆኑን እንዲሁም ማዕድኑ በህገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ሀገር እንዳይወጣ ከአዘዋዋሪዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳይኖራቸው ያደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

170. ስለጉዳዩ ሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው የተጀመረ ነገር መኖሩንና ከገቢዎችና ጉምሩክ ጋር አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ ምክክር እንደሚደረግ በተጨማሪም ከንግድ የኤክስፖርት አስተባበሪ ጋር በየጊዜው ከኮንትሮባንድ ጋር የተያያዙ ነገሮች ላይ ስብሰባ እንደሚያደርጉ እንዲሁም ከፖሊስ ጋር አብረው የሚሰሩ መሆኑን ነገር ግን ታች ወርደው እንዳልሰሩና በህገወጥ መንገድ ከሀገር ውጪ የሚወጣ መኖሩን ገልፀዋል፡፡ ይህንን ለመከታተል በየክልሉ የፍተሻ ኬላ ማስቀመጥ እንደሚከብዳቸው ነገር ግን የመፈተሻ መሳሪያ ለመግዛት የአቅም ችግር እንዳለባቸው በተጨማሪም የህግ ክፍተት እንዳለባቸው ለወደፊት ግን በተጠናከረ መልኩ የክትትል አሰራር ስርአት ዘርግተው እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

171. ስለጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የከበሩ ማዕድናት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው፣ በቀላሉ ግለሰቦች ሊያዘዋውሯቸው የሚችሉና በዓለም ደረጃ በትልቅና በተደራጀ መልኩ የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው የመፈተሻ ኬላ መፍትሄ አለመሆኑንና የክትትሉና የቁጥጥር ስርዓቱ ከምርት ጀምሮ መሰራት ያለበት ሲሆን ክልሎች የሰጧቸውን የምርት ፈቃዶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ በጋራ መሰራት ያለበት ጉዳይ በመሆኑንና ሚ/ር መ/ቤቱም ህገወጥ የማዕድን ስራ የሚሰማሩትን ለመቀነስ የሚያስችል አሰራሮች በጋራ ለመስራት በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ እንዲሁም ክልሎችም ህገወጦችን መከላከል እንዲችሉ አሰራሮችን በመዘርጋት የሚመለከታቸውን በማስተባበር የመቀነስ ስራ መሰራት እንዳለበት የገለፁ ሲሆን፣ በቦሌ ኤርፖርት በ2006 ዓ.ም ተያዙ የተባሉትን ማዕድናትን በተመለከተ ሚ/ር መ/ቤቱ ድጋፍ በመስጠት በተለያ መልኩ የማገዝ ስራ የሰራ ቢሆንም ተያዙ ተባሉትን ማዕድናት የማጣራት ስራ ለመጀመር እንደሚሞከር በተጨማሪም በድንበር በኩል የሚደረጉ ህገወጥ

ስራዎችም ሚ/ር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በመስራት ህገወጥ አሰራሮችን መከላከልና እርምጃዎች መውሰድ በቀጣይ የሚሰሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

172. ይሁንእንጂ የውጭ ንግድ ማዕድናት ወይም ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የጌጣጌጥ ማዕድናት በኤክስፖርት እና በድንበሮች በኩል በህገወጥ መንገድ በኮንትሮ ባንድ የሚወጡ መሆኑና ምርቱ በሚመረትባቸው ክልሎች ላይም ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና የተፈጥሮ አከባቢ ችግሮችን ያስከተለ መሆኑን እንዲሁም አምራቾቹም ሆኑ ከማዕድን ሴክተሩ ሊገኝ የሚገባውን ጥቅም እንዳያገኝ ማድረጉን ለመረዳት ተችሏል፡፡

**መ. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሀብት አስተዳደር፣ ግብይት ክትትል እና ቁጥጥርን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ከክልሎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር፣ ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ እና ባለፈቃዶችን ለመደገፍ የሚያስችል ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርአት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣**

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመወያያ መድረክ ያለው ስለመሆኑ፤**

173. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት አምራቾችና ነጋዴዎች (አዘዋዋሪዎች) ያለባቸውን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረክ ሊኖረው ይገባል፡፡

174. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በደቡብ፣ በኦሮሚያ በትግራይና በአማራ ክልል ለሚገኙት የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት አምራቾችና ነጋዴዎች (አዘዋዋሪዎች) ያለባቸውን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል መደበኛ በሆነ መልኩ የመወያያ መድረኮችን ያላዘጋጀ እና ለሌሎች ክልሎች ደግሞ ለመወያየትም ጥሪ አድርጎላቸው እንደማያውቅ ታውቋል፡፡

175. በኦዲቱ ወቅት ከታዩት ሶስት አምራቾችና 10 አዘዋዋሪዎች በድምሩ ከ14ቱ ባለፈቃዶች ውስጥ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2004-2006ዓ.ም ለ5ቱ (36%) አምራችና አዘዋዋሪዎች የመወያያ መድረኮችን ፈጥሮላቸው የማያውቅ ሲሆን ለ 9ኙ (64%) የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት አምራቾች፣ አዘዋዋሪዎች እና ለጌጣጌጥ ላኪዎች ደግሞ የመወያያ መድረኮችን ቢፈጥርላቸውም ያለባቸውን ችግሮች በተዘጋጁት መድረኮች አማካኝነት ሊፈታላቸው እንዳልቻለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

176. መደበኛ በሆነ መልክ ውይይት ባለመደረጉም አዲስ የማዕድን አዋጅ ቁጥር 678/2002 ለማሻሻል በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ ለመወያየት በተዘጋጀው የመወያያ መድረክ ላይ የባለድርሻ አካል ተሳትፎ እንዲያደርጉ ዕድል ያልተሰጣቸው መሆኑንና ባለመሳተፋቸው በስራ

ላይ ችግር እንዳስከተለባቸው ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ጉዳዩን አስመልክቶ የሜድሮክ ጎልድ በተደጋጋሚ በደብዳቤ በመፃፍ ሚ/ር መ/ቤቱን ቢጠይቅም ምላሽ አለማግኘቱን ገልጿል፡፡

177. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከክልሎች ጋር በዓመት 4 ጊዜ ስብሰባ እንደሚያደርጉ ሆኖም ግን ከባለፈቃዶች ጋር ቋሚ ውይይት ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑንና ከክልል ኤጀንሲ ቢሮዎችና እዚህ አዲስ አበባ ካሉት አካላት እንጂ ወደ ወረዳ በመውረድ ከአዘዋዋሪዎች ወይም ከአምራቾች ጋር እንደማይገናኙ ገልፀዋል፡፡

178. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እንደገለፁት ሚ/ር መ/ቤቱ ለአዘዋዋሪዎችና ለአምራቾች በአመት አንድ ጊዜ የምክክር መድረክ እንደሚያዘጋጅና ምክክር እንደሚያካሂድ ከዚህም በተጨማሪ ለክልሎች በየ 3 ወሩ መድረክ እንደሚዘጋጅ እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ በራሱ ፈቃድ ለሰጣቸው የጋራ መድረክ በየ 3ወሩ በማዘጋጀትና የተለያዩ ኮሚቴዎችን በማቋቋም እየሰራ እንደሚገኝ፤ ሆኖም ግን አዘዋዋሪዎችና አምራቾችን በተመለከተ ድጋፍና መደበኛ የሆነ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት ያለባቸው ክልሎች በመሆናቸው ለወደፊት ክፍተት ካለ ግን ለማጠናከር እንደሚሞከር ገልፀዋል፡፡

179. ይሁን እንጂ ከላይ የተጠቀሠው ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ያልቀረበ ሲሆን ፤እንዲሁም ከተላከው ነባራዊ ሁኔታ ጋርም ተያይዞ አልቀረበም፡፡

180. ይህም በመሆኑ ባለፈቃዶች ያለባቸውን ችግሮች ለመቅረፍ እንዳላስቻላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ሚ/ር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ፤**

181. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ዙሪያ የማዕድን ምርቱን ፈቃድ ለማስተዳደር እና የግብይት አሠራርን ለማጠናከር እንዲያስችል በመቀናጀት ሊሰራ ይገባል፡፡

182. በኦዲቱ ከታዩት 10 ባለድርሻ አካላት ውስጥ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ8ቱ (80%) ጋር በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ዙሪያ የማዕድን ምርቱን ፈቃድ ለማስተዳደር እና የግብይት አሠራርን ለማጠናከር እንዲያስችል በመቀናጀት እንደማይሰራ እንዲሁም ከደቡብ ክልል ማዕድን ኤጀንሲ ጋር ደግሞ የተጠናከረ የቅንጅት አሰራር እንደሌለው የታወቀ ሲሆን፡ከዚህም በተጨማሪ በየደረጃው የሚገኙ የክልል ማዕድን ቢሮዎች ፣ የዞንና የወረዳ ማዕድን ፅ/ቤቶች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትጋር ያላቸው የስራ ግንኙነት የላላ በመሆኑ በመናበብና በመቀናጀት እንደማይሰሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

183. በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ላይም ወርቅ ከሚመረምሩ ባለሙያዎች ጋር በየጊዜው በሚፈጠረው አለመግባባት ምክንያት ከስራ ሰዓት ውጭ የሚመጡትን የወርቅ ነጋዴዎች ለማስተናገድ ችግር እንደፈጠረባቸውና ከዚህም የተነሣ በስራ ላይ ጫናና መጓተት በመፍጠሩ ምክንያት በጊዜ መግባት የነበረበት ወርቅ ሳይገባ ወይም ሳይረጋገጥ የሚቀር መሆኑን እንዲሁም በአዋሳ የብሄራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ ጣቢያ የወርቅ ጥራት በሚታይበት ጊዜ የወርቁን ጥራት የሚያሳይ ውሃ (Distiled water)እንደሚያልቅባቸውና እንዲመጣላቸውም ሲጠይቁ ክልሉና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተነጋግረው በአፋጣኝ ምላሽ ባለመስጠታቸው በሥራ ላይ ችግር እየፈጠረባቸው መሆኑ፣ በሽሬ የብሄራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ ጣቢያም ከአዘዋዋሪዎች የሚነሱትን ቅሬታዎች በአግባቡ እንዳይመልሱ ማድረጉን የስራ ኃላፊዎቹ ገልፀዋል፡፡

184. አዋጁ በሚፈቅደው መሰረት በአንድ የፈቃድ ክልል ውስጥ ያለ የማዕድን ቦታ የክልልና የዞን ማዕድንና የግብርና ቢሮዎች በባህላዊ ዘዴ ወርቅ ለሚያመርቱ ባለፈቃዶች በእርሻ ስራ ለተሰማሩት ግለሰቦች በተደራቢነት የሰጡ መሆኑና ከዚህም የተነሳ ከአከባቢው ማህበረሰብ እና ከባህላዊ ባለፈቃዶች ጋር አለመስማማት እንደፈጠረባቸው መሆኑና በዚህም ዙሪያ ለሚ/ር መ/ቤቱ ቢያሳውቁም መፍትሄ እንዳላገኙ የሜድሮክ ወርቅ የስራ ኃላፊዎች የገለፁ መሆኑ

185. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ቅንጅት ስራው ላይ ትኩረት እንዳልተሰጠበት እንዲሁም ከክልሎችና ከብሄራዊ ባንክ ጋር በዓመት አንድ ጊዜ ጠቅላላ ስብሰባ እንዳላቸው በዛ ላይ የሚገናኙ ቢሆንም ግን የአሠራር ችግር እየተፈጠረ ያለው ግንኙነት ላይ ሳይሆን ሥራዬ ነው ብሎ ትኩረት የመስጠቱ ችግር ላይ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

186. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እንደገለፁት ክልሎች ወርቅ፣ከኄጣኄጥና ታንታለምን ወደ ውጭ ሀገር እንዲላኩ ፣ማህበራት እንዲደራጁ አሰራሮች እንዲዘረጉ በማዕድን ሚ/ር የማቀናጀትና የማጠናከር ጥረት መደረጉን እንዲሁም ክልሎችን በተፈለገው ደረጃ ለመደገፍና ለማጠናከር ጥረት የተደረገ መሆኑን ሆኖም ግን ክልሎችን በተፈለገው ደረጃ ለመደገፍና ለመከታተል የሰው ዓይል አደረጃጀት ችግሮች ያሉት በመሆኑ ለማስተካከል ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ በተጨማሪም አዳዲስ አዋጆች ሲወጡና ሲረቁ ክልሎች ሃሳብ እንደሚሰጡበት እንዲሁም በብሄራዊ ባንክ በአዘዋዋሪዎችና በጂኦሎጅካል ሰርቨይ ላይ የሚነሱ ችግሮች አልፎ አልፎ ቢኖሩም ችግሮቹ ሲታወቁ ወይም ሲፈጠሩ በሶስትዮሽ ስምምነት በኮሚቴ እንዲፈቱ እንደሚደረግና ባንኩ ያለውን ችግሮች ለመፍታትና በጋራ ተጠናክሮ ለመሥራት ሚ/ር መ/ቤቱ ከበላይ ኃላፊዎች ጋር በየጊዜው ስብሰባ የማድረግ ስራ መጀመሩን ገልፀዋል፡፡

187. ይሁን እንጂ በክልል ማዕድን ቢሮዎች፣ዞኖችና ወረዳዎች ላይ በአዋጅ አፈፃፀምና በህግ አተሮጓጎም ዙሪያ ክፍተት የፈጠረባቸው መሆኑና ተቀናጅተው እንዳይሰሩ ማድረጉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

## <u>ሚ/ር መ/ቤቱ ባለፈቃዶችን ለመከታተል የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ዘዴ ያለው ስለመሆኑ፣</u>

188. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከባንኮች ጋር የከበረና በከፊል የከበረ ማዕድናት ምርትና ሽያጭ ዙሪያ የሪፖርት አቀራረብ ስርዓትን በተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ ሊኖረው እና የባለፈቃዶችን ወቅታዊ ሁኔታ /ሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ፣ የፈቃድ ዕድሳት ጊዜ፣ የክፍያ መፈፀሚያ ጊዜ… ወዘተ/ ለመከታተል የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ዘዴ ሊኖረው ይገባል፡፡

189. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከባንኮች ጋር በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ምርትና ሽያጭ ዙሪያ የሪፖርት አቀራረብ ስርዓትን በተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ እንደሌለው ታውቋል ፡፡

190. ከዚህ ጋር በተያያዘ የኦሮሚያ ክልል ውሃ ማዕድንና እነርጂ ቢሮ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርትና ማዕድን አምራቾች ዙሪያ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር የሪፖርት አላላክ ልምድ እንዳይኖር ማድረጉ ከዚህም የተነሣ ለስብሰባ ሲጠሩ እንጂ ወጥ በሆነ መልኩ ለሚ/ር መ/ቤቱ ሪፖርት እንደማያቀርቡ፣ ብሔራዊ ባንክ እና ማዕድን ሚኒስቴር የሚያቀርቧቸው ሪፖርቶች ባለመናበባቸው የተለያዩ ሪፖርቶች ማቅረባቸው /ለምሳሌ የጥቅምት ወር የባንክ ሪፖርት 675.6 ኪ.ግ. ሲሆን የሚኒስቴር መ/ቤቱ 651 ኪ.ግ./ ፣ ሊሆን መቻሉን የክልል የማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

191. በተጨማሪም ከዞን እስከ ክልል ማዕድን ቢሮዎች እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱን ጨምሮ ወጥ የሆነ የምርትና የሽያጭ የሪፖርት አደራረግ ስርዓት የሌለ መሆኑን በዚሁ ምክንያት ከዞኑ የእያንዳንዱ የወርቅ አዘዋዋሪ ከሀምሌ1/2004እስከ ጥር30/2005ዓ.ም ወደ ብሄራዊ ባንክ የገባው የወርቅ መጠን ሪፖርት ሲደረግ የተሸጠው እንጂ የተመረተውና በእያንዳንዱ ባለፈቃድ ስቶክ ላይ የቀረው የወርቅ መጠን ባለመገለፁ ሽያጩ ላይ ክፍተት ሊያስከትል እንደሚችል በኦዲቱ ወቅት ከታዮት ማስረጃዎች ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡

192. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከብሔራዊ ባንክ ጋር የሶስትዮሽ ስምምነት ያላቸው ቢሆንም አሰራሩ ግልፅ እንዳልሆነ ሆኖም ግን የመግባቢያ ሰነድ የሌላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የክልል ማዕድን

ቢሮዎች በትክክል ባለማስተዳደራቸው የምርት ሪፖርት እንደሌላቸው እና ከባንክም የሚያገኙት የሽያጭ እንጂ የምርት ሪፖርት አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህም በመሆኑ ትክክለኛ መረጃ እንዳያገኙ እንዳደረጋቸው በመግለፅ የብሔሪዊ ባንክ ዳታ ቤዝ ሲስተሙ ትራንስፖረንሲ ቢሆን ጥሩ እንደሚሆን/ማለትም ዲጂታል ሲስተም ቢኖር ጥሩ ነው/ የሚል አስተያት ሰጥተዋል፡፡

193. ስለ ጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ በላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እንደገለፁት በወርቅ ዙሪያ ከፍተኛ ችግር በተለያ ጊዜ በመኖሩ ክልሎችም መረጃ ለማግኘት በመቸገራቸው ውይይት ተደርጎና አሰራር ተዘርግቶ ከሚ/ር መ/ቤቱና ከባንኮች መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ስራ በመሰራት ላይ እንደሚገኝ እንዲሁም በሽያጭ ዙሪያ የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው ጋር ዕቅድ ተይዞ ለብሄራዊ ባንክ አሰራር የመዘርጋት ስራ መጀመሩንና ለክልል ማዕድን ቢሮዎች፣ለሚ/ር መ/ቤቱና ለገቢዎች የሚሰጠው መረጃ በተደራጀ መልኩ አለመሆኑንና አሰራሮችን ለማስተካከል ግዴታ በመሆኑ ለብሄራዊ ባንክ በደብዳቤ ከመጠየቅ ይልቅ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ መግባባት መቻሉን በተጨማሪም የመረጃ ክፍተቱ የተፈጠረው በስልክ ከግዥ ማዕከላት ጋር የሚሰራ በመሆኑ ሲሆን ይህንን ለማስተካከል እርምጃ ተወስዶ የመረጃዎች ፍሰት እየተስተካከሉ እንደሚገኙ  እንዲሁም ባንክ የገባው የወርቅ መጠን ሪፖርት ሲደረግ የተሸጠው እንጂ የተመረተውና በእያንዳንዱ ባለፈቃድ ስቶክ ላይ የቀረው የወርቅ መጠን ባለመገለፁ ሌላ አሰራርን መዘርጋት ወደፊት የሚሰራ መሆኑን እና የሶስትዮሽ ስምምነቱም ላይ የተገለጸው ወርቅ ባንክ ማስገባት እንጂ ስቶክ ላይ የቀረውን የወርቅ መጠን አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

194. ከዚህም በተጨማሪ ሚ/ር መ/ቤቱ የባለፈቃዶችን ወቅታዊ ሁኔታ /ሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ፣ የፈቃድ ዕድሳት ጊዜ፣ የክፍያ መፈፀሚያ ጊዜ… ወዘተ/ ለመከታተል የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ  የታገዘ መረጃ አያያዝ ዘዴ ካዳስተር ሲስተም እንዳለው ቢገልጽም ከክልሎች ጋር የመረጃ ልውውጥ ባለመኖሩ  የተደራረቡ የፈቃድ ቦታዎች እንዳሉ ታውቋል፡፡

195. በዚህ ዙሪያ የካዳስተር ሲስተሙን በተመለከተ   በክልል ማዕድን ቢሮዎች እንደማይሰራ እና በክልል ላሉት ባለፈቃዶች ከአነስተኛ ደረጃ ወደ መካከለኛ እንዲሁም ከባህላዊ ወደ ልዩ አነስተኛ ለመሸጋር ጥያቄ ሲያቀርቡ ቦታው በሌላ ባለፈቃድ አለመያዙን ለማረጋገጥ የተቸገሩ መሆኑን እንዲሁም ከሚ/ር መ/ቤቱ ጋር መረጃ መለዋወጥ ባለመቻላቸውና የሚለዋወጡትም መረጃ የተጠናከረ ባለመሆኑ የክፊያ መፈፀሚያ ጊዜና የፈቃድ ዕድሳት ጊዜ ለመከታተል እንዳላስቻላቸው  የክልል ማዕድን ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

196. ስለጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ መረጃ ለመለዋወጥ በፊት የነበረው የፍለክሲ ካዳስተር ሲስተም ለፈቃድ መስጠት ብቻ እንደሆነና ቼክ አድርገው መረጃውን ወደ ክልል ይልኩ እንደነበረ በተጨማሪም ጋዜጣ ላይም እንደሚያወጡ፡፡ ሆኖም ግን አሁን ባለው አሠራር ደግሞ ካዳስተር ፕሮጀክት ተቋቁሞ ከየክልሉ ሁለት ሁለት ሰዎች በመሰልጠን ካዳሰተሩ ሥራ ላይ መሆኑን ይሁን እንጂ ፍሌክሲ ካዳስተር ስሲተሙም የሰው ኃይል እጥረት በመኖሩና በኔት ወርክ ችግር ምክንያት አፈጻጸም ላይ ችግር እንዳለባቸው እንዲሁም የኢትኖ ማይኒንግ መረጃ ለክልሎች አለማስተላለፍን በተመለከተ ኢትኖ ፈቃድ በወሰደበት ጊዜ የፀጥታ ችግር ስለነበር መረጃ ለመለዋወጥ እንዳልተቻለ፡፡ በአጠቃላይ ክልሎችም የማዕድን መረጃ ሲስተም እንደሌላቸውና በዚሁ ምክንያት የመንግስት ገቢ እየገባ እንዳልሆነ ይህም በመሆኑ ምን ያህል እንደተመረተ እና እንደተሸጠ መረጃ ለማግኘት እንዳላስቻላቸው ለወደፊት ግን ልሰሩ እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡

197. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ በላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እንደገለፁት የካዳስተር ሲስተሙን በተመለከተ የተሰጠው አስተያየት ሁሉንም ክልሎች እንደማይወክል ሆኖም ግን ማዕድን ሚ/ርም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች መብራት ወይም ኢንተርኔት ሲቋረጥ የካዳስተር ሲስተሙ እንደማይሰራ የሚታወቅ መሆኑ ሌላው ችግር ደግሞ በአንዳንድ ክልሎች ያሉ በካዳስተር ሲስተሙ የሰለጠኑ ባለሙያዎች በሙሉ በመልቀቃቸው የተፈጠረ ችግር ቢኖርም በየክልላቸው በመሄድ ወይም ወደ ማዕድን ሚ/ር እንዲመጡ በማድረግና በማሰልጠን ችግሩ እየተቀረፈ መሆኑን በተጨማሪም ለሁሉም ክልሎች ጀማሪ እና አድቫንስድ ለሆኑት ስልጠናዎችን ለመስጠት ዝግጅት መደረጉን ገልፀዋል፡፡

198. ይህም በመሆኑ የክልል ማዕድን ቢሮዎች ከባንክ በየጊዜው የሚፈልጉትን ሪፖርት እንዳያገኙ ማድረጉና በየክልላቸው የተመረተውን የወርቅ መጠን ለማወቅ እንዳላስቻላቸው እንዲሁም መረጃውን ለሚፈልጉ አካላትም ማስተላለፍ እንዳልቻሉ እና ወርቅ አዘዋዋሪዎች ለብሄራዊ ባንክ ምን ያህል ወርቅ እንዳስገቡ እንዳያውቁና ስራቸው በተፈለገ መንገድ እንዳይሰራ ማድረጉን እንዲሁም የባለፈቃዶችን ወቅታዊ ሁኔታንም ለመከታተል እንዳላስቻላቸው ገልፀዋል፡፡

199. ይሁን እንጂ በሚ/ር መ/ቤቱ ፣በክልል ማዕድን ቢሮዎች እንዲሁም በባለድርሻ አካላት መካከል የመረጃ ክፍተት እንዲፈጠር ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## ወደ ውጭ አገር ለመሸጡ የማዕድናት ተመን ስለማውጣቱ እና ለባህላዊ ማዕድናት አምራቾች የቴክኒክ ድጋፎች መስጠቱን በተመለከተ

200. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ለመሸጥ ተመን በማውጣት ለግብይቱ ህጋዊ ድጋፍ እንዲሁም በክልሎች ለሚገኙ ለባህላዊ ማዕድናት አምራቾች (የወርቅ፣) የቴክኒክ ድጋፎችን (የተሸሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ድጋፎች) ሊሰጥ ይገባል፡፡

201. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ለመሸጥ ተመን በማውጣት ለግብይቱ በተሟላ መልኩ ህጋዊ ድጋፍ አላደረገም፡፡

202. ሚኒስቴር መ/ቤቱ እስከ 2006 ዓ.ም ወደ 280 የሚሆኑ የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ለመሸጥ ፈቃድ የወሰዱ ባለፈቃዶች ቢኖሩም ለ2005ዓ.ምና ለ2006ዓ.ም የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ለሚሸጡ ባለፈቃዶች የማዕድናቱን ተመን ከኢንተርኔት መረጃውን በመውሰድ ሁለት ጊዜ ብቻ በባህላዊ ደረጃ ለሚያመርቱት የዋጋ ተመን የተሰጣቸው ቢሆንም መጀመሪያ የወጣውም ተመን በጥናት ላይ ተመስርቶ ማጽደቁን የተመኑ ጥናት በሚ/ር መ/ቤቱ ተጠይቆ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም በ2004ዓ.ም የዋጋ ተመንም ሆነ የተሻሻለበት ማስረጃም ከሚ/ር መ/ቤቱ ተጠይቆ አልተገኘም፡፡

203. ከሀገሪቱ እሴት ሳይጨመርባቸው ወደ ውጭ ሀገር የሚወጡ (ለምሳሌ ኦፓል፣ አማዞናይት፣ ኮረንደም ሳፋየርና ሩቢ ኤመራልድ እና ግራን ቶርማን እንዲሁም የመሳሰሉ ማዕድናት) እንዳሉ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ወደ ውጭ አገር ለሚሸጡ ባለፈቃዶች ለማዕድናቱ የሚያወጣውን የማዕድንተመን (ጥሬና እሴት የተጨመረባቸው) በአገር አቀፍ እና በአለም አቀፍ ያለውን ተጨባጭ የገበያ ሁኔታን መሰረት ያላደረገና በጥናት /Market Assessment/ ላይ ያልተመሰረተ ዋጋ በመስራት ላይ የሚገኝ መሆኑ፤ እንዲሁም የሚጠቀምበትንም ዋጋ ተመን በየጊዜውና በየወቅቱ ተመኑን የማያሻሽል እና የማያፀድቅ በመሆኑ የጌጣጌጥ ማዕድናት የላኪነት ፈቃድ ያላቸው ባለፈቃዶች በአዋጅ 651/2001 ከተመለከተው ውጭ በክምችት ከ74 እስከ 21,001 ኪሎ ግራም በከፊል የከበሩ ማዕድናት ይዘው እንደሚቆዩ፣

204. በተጨማሪም በ2004ዓ.ም የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ለመላክ ለባለፈቃዶች ተመን በማውጣትና በየጊዜው በማሻሻል ለግብይቱ ህጋዊ ድጋፍ እንደማይሰጥ እና ለዝቅተኛ ደረጃ በተለምዶ አዋራ በመባል የሚታወቀውን ኦፓል ቀርጾ እና አስውቦ ወደ ውጪ ለመላክ ዋጋ እንዲወጣላቸው እንዲሁም ያልተቀረፀ ኦፓል ወደ ውጭ አገር የመሸጫ ዋጋ በገበያው መሠረት እንዲስተካከልላቸው በቃልና በጽሑፍ በተደጋጋሚ ሚ/ር መ/ቤቱን ቢጠይቁም ምላሽ

ያላገኙ መሆኑን እንዲሁም የማዕድን ሚ/ር መ/ቤት ከክልሎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በ2005 በተደረገው ቢጋራ ምክክር ላይ ችግሩ ቢጠቀስም መፍትሔ እንዳልሰጣቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

205. ስለጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው አንዳንድ ማዕድናት ከፍተኛ ኪሎ ሲመዝኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ዝቅተኛ እንደሚመዝኑ ሆኖም ግን አምራቾች ጊዜና ገገር እስከሚያገኙ ድረስ ይዘው እንደሚቆዩ፣ በሚ/ር መ/ቤቱም በአለም አቀፍ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታን መሰረት ያደረገ የገበያ ጥናትም /Market Assessment/ የሌለ መሆኑንና ለአምራቾች የዋጋ ተመን ቢያስፈልጋቸውም ሚ/ር መ/ቤቱ የምርቱን መጠን እንደሌላቸው ምክንያቱም ክልሎች ይህን ያህል ምርት አምርተናልና ዋጋ ተምኑ ብለው ትክክለኛውን የምርት መጠን እንደማይሰጥዋቸው፡፡ በአጠቃላይ ክልል ምን ያህል እንደተመረተ የምርቱን መጠን ባለማወቃቸውና የኢንፎርሜሽን ክፍተት በመኖሩ የተጠና ለከበሩና በከፊል ለከበሩ ማዕድናት የዋጋ ተመን የገበያ ጥናት ሙሉ በሙሉ እንዳልተሰራ እንዲሁም ኦፓልን በተመለከተ ግን ጥናት እንዳለና ለኦዲት ቡድኑ እንደሚያቀርቡ፣ድጋፍንም በተመለከተ ከማሸግ ጀምሮ ኤርፖርት እስከሚደርስ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ሚ/ር መ/ቤቱ በድጋፍ ላይ ችግር እንደሌለበት ሆኖም ግን በድጋፍ አሰጣጡ ላይ የመጓተት ችግር እንዳለ በተጨማሪም በክልል የተሰጡ ፈቃዶች ላይ በአመራረት ዙሪያ ችግር/ክፍተት/ መኖሩን እያንዳንዱ አምራቾች ያመረቱትን ለሚ/ር መ/ቤቱ ሪፖርት አለማድረጋቸው፡፡ ለወደፊት ግን እንደሚስተካከል ገልጸዋል፡፡

206. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እንደገለፁት ኦፓል፣አማዞናይት፣ኮረንደም ሳፋየርና ሩቢ ኤመራልድ እና ግራን ቶርማን በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ያለውን ተጨባጭ የገበያ ሁኔታን ተለዋዋጭ በመሆኑና ማዕድናቶቹ ስለሚለያዩ አንድ ዋጋ ማውጣት ስለማይቻልና ሌሎች ችግሮች በጥናት/Market Assessment/ በማድረግ በወቅቱ የሚከለስ ዋጋ ተመን እየተሰራ እንደሚገኝ፣ እንዲሁም ከፍተኛ ክምችት ያላቸው በከፊል የከበሩ ማዕድናት ያለው ዋጋ ትመና ከፍተኛ መሆኑ በተለያዩ መድረኮች በመነሳታቸው መ/ቤቱ አዲስ ዋጋ ትመና በማድረግ ለውጥ ለማምጣት መሞከሩንና የዋጋ ተመን ስራ ከላኪዎች በተወጣጡ ኮሚቴ በየጊዜውና በየወቅቱ ተመኑን የሚያሻሽልና የሚያፀድቅ በመሆኑ እንዲሁም ያልተቀረፀ ኦፓል /ለዝቅተኛ ደረጃ በተለምዶ አኘራ በመባል የሚታወቅ/ ከውጭ አገር የገበያ መሸጫ ዋጋ መሰረት እንዲስተካከል በማድረግ ከ2005ዓ.ም ጀምሮ ዋጋ ወጥቶለት በመሰራት ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

207. ሚ/ር መ/ቤቱ የባህላዊ ማዕድናት ምርትና ግብይት አሰራርን ለማጠናከር እና አምራቾችን ተጠቃሚ ለማድረግ የቴክኒክ ድጋፎችን (ምርትን የሚያሳድጉ የተሸሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ድጋፎች) እንደሚሰጥ በመሰረታዊ የስራ ሂደቱ አጥንቶ ለመስራት በእስትራቴጅክ ዕቅዱ ያቀደ ቢሆንም ሚ/ር መ/ቤቱ ለባለፈቃዶች ከ2004-2006ዓ.ም የቴክኒክ ድጋፎችን (የተሸሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ድጋፎች) እንደማይሰጥ ታውቋል፡፡

208. በኦዲቱ ወቅት በደቡብ፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልል በናሙና ከታዩ ከታዩ 3 የማዕድን ቢሮዎችና 13 ባለፈቃዶች ውስጥ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለ1 የማዕድን ቢሮና ለ11ዱ (85%) ባለፈቃዶች ከ2004-2006ዓ.ም በክልሎቹ ለሚገኙ ለባህላዊ ማዕድናት አምራቾች የቴክኒክ ድጋፎችን (የተሸሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ድጋፎች) ያልሰጠ መሆኑ እንዲሁም ለሁለት ክልሎችና ለ2 (15%) ባለፈቃዶች ደግሞ በተሟላ መልኩ የተሻሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ድጋፎች እንዳልሰጣቸው ታውቋል፡፡

209. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የቴክኒክ ድጋፍን በተመለከተ ብዙ እንዳልተኬደበት፣ እንደሁም የተሸሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች ላይ ግን ችግር እንዳለ ይሁን እንጂ የሰርቶ ማሳያ ስልጠናን በተመለከተ ገና ለመስራት እየታሰበ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

210. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እንደገለፁት ከ2004ዓ.ም ጀምሮ የተሰጡት የቴክኒክ ድጋፎች (የተሸሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ድጋፎች) በመጠን አነስተኛ ቢሆኑም በ2005ና 2006ዓ.ም ተከታታይ ጥናት በማድረግ በተደረገው የጃፓን ልማት መጠነኛ ድጋፍ መሰጠቱን እንዲሁም ብዛት ያላቸው አምራቾች የወርቅ መጠቆሚያ መሳሪያ እንዲያስገቡ ድጋፍ በማድረግ በሁሉም ክልሎች ብዛት ያላቸው አምራቾች መሳሪያ በማስገባት ስራ መጀመራቸውን ሆኖም ግን ቴክኖሎጂን የማስገባት ስራ ከፍተኛ ስራና ወጪን የሚፈልግ በመሆኑ ከአምራች ፍላጎት እንዲኖር ግንዛቤ እንዲወሰድ በማድረግ በቂ ዝግጅት የሚያስፈልገው ቢሆንም ዝግጅት ተደርጎ አምራች ማህበራት ማሽን እንዲያስገቡ ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

211. ይህም በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ለመሸጥ ተመን የወጣበት ወይም የገበያ ጥናት የሚመለከተው ክፍል በተደጋጋሚ ተጠይቆ ያልቀረበ ሲሆን ተመን ባለማውጣት በአምራቾችና በባንኩ መካከል ያለው የወርቅ ዋጋ ተመን ፍትሃዊ የገበያ ውድድርን የሚያፋልስ መሆኑን እንዲሁም የተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎች ድጋፍ ባለመደረጉ ማህበራቱ ማምረት የሚገባቸውን ያህል እያመረቱ አለመሆኑና የወርቅ መጠቆሚየ መሣሪያ

ባለመኖሩ ብዙ ጊዜ ብዙ ጉድጓዶችን ቆፍረው ወርቁን ሲያጡ ትተውት የሚሄዱ መሆኑንና ምርቱ የት ቦታ እንዳለ ለመለየት ችግር እየፈጠረባቸውና ማህበሮቹንም ለተጨማሪ ወጪ እንደዳረጋቸው፤ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የባህላዊ ማዕድናት አምራቾችን ምርት ለማሳደግና ምርትን የሚያሳድጉ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ የተሻሻሉ የማምረቻ መሳሪያ አጠቃቀምም ሆነ የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ባለመሰጠቱና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋዋቅ ሥራ አለመሠራቱ ባለፈቃዶች መሣሪያውን እንኳን መግዛት ቢችሉ በመሣሪያው ላይ የአጠቃቀም ችግር ሊያስከትልባቸው እንደሚችል እና የመሳሪያ ድጋፍ ለተሠጣቸውም ስልጠና ባለመሰጠቱ መሣሪያዎቹን ለመጠቀም ክፍተት መፈጠሩን ከዚህም የተነሣ ባለፈቃዶቹ በወቅቱ ማግኘት ያለባቸውን ትርፍ ማግኘት አለመቻላቸውን የክልል የማዕድን ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

212. በመሆኑም ሚ/ር መ/ቤቱ ለማዕድናቱ በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ያለውን ተጨባጭ የገበያ ሁኔታን መሰረት ያደረገ ጥናት በማጥናት/Market Assessment/ ተመን በማውጣት ለግብይቱ በቂ ድጋፍ ያላደረገ መሆኑና በክልሎች ለሚገኙ ለባህላዊ ማዕድናት አምራቾች (የወርቅ፣) የቴክኒክ ድጋፎችን (የተሸሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ድጋፎች) በተሟላ መልኩ ያልተሰጠ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

<u>***ሚ/ር መ/ቤቱ ባለፈቃዶች ያመረቱትን (የሸጡትን) የማዕድን ዓይነትና መጠን ለፈቃድሰጪው አካል የሚያሳውቁበት ስርዓት ዘርግቶ ስለመከታተሉ እና የእደ-ጥበብ ባለፈቃዶች ሪፖርት ስለማድረጋቸው***</u>

213. ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርትና ግብይት ባለፈቃዶች ያመረቱትን ወይም የሸጡትን የማዕድን ዓይነትና መጠን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚያሳውቁበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊነቱን ሊከታተል፣የምርት ባለፈቃድ ያመረቱትን ወይም የሸጡትን የምርት ዓይነትና መጠን እንዲሁም የእደ-ጥበብ ባለፈቃድ ከግለሰብ የሚሰበስባቸውን የወርቅና ብር መጠን በወቅቱ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

214. የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርትና ግብይት ባለፈቃዶች ያመረቱትን ወይም የሸጡትን የማዕድን ዓይነትና መጠን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚያሳውቁበት ስርዓት ቢዘረጋም በኦዲቱ ወቅት ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት ተግባራዊነቱን እንደማይከታተሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

215. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በኦሮሚያ፣ በደቡብና በትግራይ ክልሎች የታዩት የከበሩ ማዕድናት ምርትና ግብይት ባለፈቃዶች ያመረቱትንና የሸጡትን የማዕድን መጠን ለፍቃድ ሰጪው እንዳያሳውቁ እና የምርት ሪፖርት ወቅቱን ጠብቀው በየጊዜው እንዳያቀርቡ ማድረጉ፣ እንዲሁም በደቡብ ክልል አምራችና አዘዋዋሪዎችን በተመለከተ ሪፖርት በዓመት አንድ ጊዜ

እንደሚደርሳቸው እና ሪፖርት በማያደርጉትም በየጊዜው ማስጠንቀቂያ የሚፃፍባቸው መሆኑን ሆኖም ግን ያመረቱትን እና በእጃቸው ያለውን ለይተው ሪፖርት እንደማያደርጉ ከዚህም የተነሳ የማዕድን ህግ ከሚከለክለው ውጭ ከ400-800 ኪ.ግ ወርቅ በእጃቸው ይዘው የሚገኙ ባለፈቃዶች መኖራቸው ከዚህም ሌላ የኦሮሚያ ክልል ውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ወርቅ አዘዋዋሪዎች ብሔራዊ ባንክ ወርቅ ሲያቀርቡ ያለ ማዕድን ቢሮው ድጋፍ ስለሚያቀርቡ ሪፖርት የሚያደርጉበት ምክንያት እንደሌለ እንዲሁም በኦሮሚያ ማንኛውም ባለፈቃድ በየዓመቱ የበጀት ዘመን በተጠናቀቀ 30 ቀናት ውስጥ ያካሄዱትን ግብይት በግልፅ ሪፖርት እንደማያደርጉ፣ እንዲሁም የወርቅ፣ የታንታለምና ጀምስቶን ምርት ሽያጭና የተገኘው የውጭ ምንዛሪ መረጃ በክልሉ አለመገኘቱና ለስራ አስቸጋሪ መሆኑ፣ በተጨማሪም በትግራይ ክልል ደግሞ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርትና ግብይት ባለፈቃዶች ያመረቱትን ወይም የሸጡትን የማዕድን ዓይነትና መጠን ለክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ የሚያሳውቁበት ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ሪፖርት እንደማያደርጉ እና ባለማድረጋቸውም የተወሰደባቸው እርምጃ አለመኖሩን ታውቋል፡፡

216. በክልሎች የሚገኙ (ሃዋሳ እና ትግራይ) የብሔራዊ ባንክ ቅርንጫፎች ለዋናው መ/ቤት ሪፖርት ማቅረብ የሚችልሉበት እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ ከዋናው መ/ቤት ሪፖርት ጋር መናበብ እንዲችል የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ተዘርግቶ በየክልል የሚገኙ ባንኮች በየሳምንቱ ለብሄራዊ ባንክ እንዲሁም ብሄራዊ ባንክ ደግሞ በየወሩ ለሚ/ር መ/ቤቱ ሪፖርት ቢያደርግም ሪፖርቱ የነጋዴውን ስም፣ የወርቁን መጠን እና ክብደቱን እንጂ ከየት ክልል እንደሆነ ሪፖርቱ ላይ እንደማይጠቃለል ለብሔራዊ ባንክ በቀረበው ቃለ-መጠይቅ ታውቋል፡፡

217. በዚህ ዙሪያ የሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጠ ፈቃድን የሚያስተዳድረው ሚ/ር መ/ቤቱ ሲሆን በክልል የተሰጡትን ፈቃዶች ደግሞ የክልል ማዕድን ቢሮዎች ናቸው፡፡ በክልሎች ላይ ችግር እንዳለ ቢታወቅም ሚ/ር መ/ቤቱ በክልል ፈቃድ በተሰጠው ላይ ስለተግባራዊነቱ መከታተል እንደማይችል ሆኖም ግን መደረግ ያለበት በክልል አዋጁ እንዲሠራ ማድረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

218. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ በላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እንደገለፁት በክልሎች የምርት ሪፖርት የማያቀርቡትን በተመለከተ በናሙና የታዩትን ባለፈቃዶች ባለማወቃቸው ምላሽ መስጠት እንደማይችሉ እንዲሁም ከ400-800 ወርቅ ይዘው ሚገኙ ባለፈቃዶች መኖራቸውን የሚለውንም በተመለከተ ስለትክክለኛነቱ ለማረጋገጥ እንደሚያስቸግራቸውና ብዛት ያላቸው አቅራቢዎች ዋጋ ሲቀንስባቸው ዋጋ እስከሚጨምር ወይም የገዙት ዋጋ ተመጣጣኝ እስከሚሆን መያዙ ጉዳቱ አነስተኛ መሆኑን፣ እንዲሁም

ከትግራይ ክልል የተገኙት መረጃዎች የግዥ ጣቢያና ብሄራዊ ባንክ የመቀበል አሰራር የዘረጋ መሆኑን ግን ወረዳዎች መረጃዎቹን እንዲያገኙ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ በተጨማሪም ከባንኩ የሚሰጠው መረጃ ለተባለው ለክልሎችም ሆነ ለሚ/ር መ/ቤቱ በቂ የሆነ መረጃ ባለመሆኑ መረጃዎቹ በግዥ ጣቢያው ካለውና አቅራቢዎች የሚሞሉትን ፎርም ባለማካተቱና ባንኩ የሚልከው ትክክል ባለመሆኑ ትክክል ያልሆነበትንም ለማስረዳትና በአጭር ጊዜ ለማስተካከል ከባንክ ጋር ውይይት ተደርጎ አሰራሮችን በመዘርጋት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

219. በአዋጅ ቁጥር 651/2001ና 816/2006 በተቀመጠው ጊዜ መሰረት ባለፈቃዶች የምርት፣የግብይትም ሆነ ከግለሰብ የሚሰበስባቸውን የወርቅና ብር መጠን ለሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ ለክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት በወቅቱ ሪፖርት የማያቀርቡ ቢሆንም ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች እርምጃ አለመውሰዳቸውና በተሟላ መልኩ ክትትልም እንደማያደርጉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

220. ከዚህ ጋር በተያያዘ ከ ማዕድን ሚ/ር ፈቃድ የተሰጣቸው የእደ ጥበብ ባለፈቃዶች ያካሄዱትን ግብይት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቢያሳውቁም ከ4-7 ወራት በመዘግየት ሪፖርት የሚያደርጉ መኖራቸውን እንዲሁም ባለፈቃዶቹ በራሳቸው ጊዜ ሪፖርት ከሚልኩት ውጭ ሚ/ር መ/ቤቱ በአካልም ሆነ በፁሑፍ የሚከታተልበት መንገድ የሌለውና ከባለፈቃዶቹ ለሚላከውም ሪፖርት ግብረ መልስ እንደማይላክላቸው ለባለፈቃዶቹ በኦዲት ቡድኑ በተደረገው ቃለ መጠይቅና ከሚ/ር መ/ቤቱና ከክልሎች በተከለሰው ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በኦዲቱም ወቅት ሚ/ር መ/ቤቱ የተከታተለበት ማስረጃ ተጠይቆ አልተገኘም፡፡

221. ይህንን በተመለከተ የክልል ማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲየስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የእደ ጥበብ ባለፈቃዶችን በተመለከተ ከዚህ ቀደም በክልሎች እንደማይሰራ ፈቃድ የተሰጣቸው ከፌዴራል እንደሆነ፣ይህንንም ለመከታተል ውክልና የተሰጣቸው በመጋቢት / 2006 ዓ.ም ስለሆነ በዚህ ዘርፍ ስራ አለመጀመራቸውን ገልጸዋል፡፡

222. ስለ ጉዳዩ የሚ/ር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በባህላዊ ደረጃ ጄምስቶንን በተመለከተ የተወሰኑ ባለፍቃዶች ሪፖርት እንደሚልኩላቸው ሆኖም ግን ከክልል እስከ ሚ/ር መ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያሳውቁ ለወደፊት ሰንሰለቱ እየተጠናከረ እንደሚሄድ፣ ወርቅን በተመለከት ግን ሁሉም ባለፍቃዶች ወቅታቸውን ጠብቀው ሪፖርት እንደማያደርጉ፣ ክትትሉም ሆነ ግብረመልስ መላኩ በሚ/ር መ/ቤቱ ሙሉ በሙሉ አለመጀመሩን፡፡ ለወደፊት ግን እንደሚያደርጉ እንዲሁም በፍቃድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬትም ወቅቱን ጠብቀው ሪፖርት የማይልኩ ባለፍቃዶች ቢኖሩም እንደሚከታተሉና፡፡ ግብረመልስም ለባለፈቃዶቹ እንደሚልኩ

ከዚህም በተጨማሪ ሪፖርት እና የመንግስት ገቢን በተመለከተ በወቅቱ እንዲያሳውቁ ለባለፍቃዶቹ እንደሚያሳውቁ እና ማስረጃዎቹን በሙሉ ለኦዲት ቡድኑ እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል፡፡

223. ስለሁኔታው የሚ/ር መ/ቤቱ በላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እንደገለፁት በማዕድን አዋጅ ያለፈቃድ ወርቅና ብር መያዝ ክልክል እንደሆነና ባህላዊ አምራቾች/አዘዋዋሪዎች/ ከሆኑ በተመሳሳይ መቆጣጠር ያለባቸው ክልሎች መሆናቸውን የክልል ማዕድን ቢሮዎችም እርምጃ አለመውሰዳቸው አዋጁ ላይ ባለመገለፁ ሳይሆን በተቀናጀ መልኩ ባለመሰራቱ መሆኑንና ይህንንም ለማስተካከል ሚ/ር መ/ቤቱ ተከታታይ ስራዎችን በመስራት ላይ እንደሚገኝ እንዲሁም አምራቾች፣አዘዋዋሪዎችና ሌሎች ፈቃዶች በአዋጁ መሰረት ሪፖርት የመቆጣጠር፣ፈቃዱን የመሰረዝ ኃላፊነት የክልሎች መሆኑን፣በሚ/ር መ/ቤቱ የሚሰጡ ፈቃዶችንም /የእደ-ጥበብና ሌሎች/ በተመለከተ በተመሳሳይ ሁኔታ ሚ/ር መ/ቤቱእንደሚቆጣጠር በአዋጁ ላይ መገለጹንና እስካሁንም በየዓመቱ የገቡትን ውል ያልፈጸሙ የመሰረዝ ስራ ሲሰራ መቆየቱን ሆኖም ግን በክልሎች ፈቃድ የሚያስተዳድርና የሚቆጣጠር ባለሙያ ባለመኖሩ ብዙ ያልተሰሩ ስራዎች መኖራቸው ከግምት ገብቶ አዳዲስ አደረጃጀትና ባለሙያ በመቅጠር ከ2007ዓ.ም ጀምሮ የማጣራት ስራ እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

224. እንዲሁም የእደጥበብ ባለፈቃዶች ያካሂዱትን ግብይት ማሳወቅ የሚገባቸው በ3ወር ውስጥ ሲሆን አልፎ አልፎ መዘግየቶች እንደሚታዩ ይህንንም ለማስተካከል አሁን ሁኔታዎች እየተመቻቹ መሆናቸውን በተጨማሪም በአዋጅ 651/2001 በክልሎች ባሉት አዋጆችና ደንቦች ወርቅ አቅራቢዎች የበጀት ዘመኑ በተጠናቀቀ በ30 ቀናት ውስጥ ያካሄዱትን ግብይት በግልፅ ሪፖርት እንደሚያደርጉ እንደሚጠቅስ ነገር ግን ይህንን መከታተል ያለባቸው ክልሎች ሲሆኑ አደረጃጀቱን ለማስተከከል ግን ሚ/ር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በጋራ በመሆን ስራዎችን በመስራት ላይ እንደሚገኝ ከዚህም ሌላ የእደጥበብ ባለፈቃዶችን ፈቃድ ለክልሎች እንዲተላለፍ የተደረገው በ2006 ዓ.ም ከክልሎች ጋር በነበረው ስምምነት የተሰጣቸው ሲሆን ክልሎች ግን በሰው ኃይል አደረጃጀት መስራት ባይችሉም ሚ/ር መ/ቤቱ ግን የጀመረውን ስራ ለመስራት ይቸግራል ተብሎ እንደማይገመት ገልፀዋል፡፡

225. ይህም በመሆኑ ባለፈቃዶች ያመረቱትን እና የሸጡትን እንዲደብቁ ማድረጉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ሀብትን ለማስተዳደር እና ግብይትን ለማስፋፋት እንዲሁም ባለፈቃዶችን ለመደገፍ በሚኒስቴር መ/ቤቱና በፈቃድ ሰጪ አካላት በርካታ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህም አንፃር የክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በመንግስት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ ተፈፃሚና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ ሲሆን፣ ከዚህ ዓላማ አንፃር ፈቃድ አስተዳደር፣ ምርትና ግብይት ቁጥጥር አፈፃፀም እና ውጤታማነት በተመለከተ በተካሄደው የክዋኔ ኦዲት በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለ አዋጅ ቁጥር 651/2001 እና ለአዋጅ ቁጥር 678/2002 የማስፈፀሚያ ደንብ በሚመለከተው አካል አለማፀደቁ፣
- ሚ/ር መ/ቤቱ በየበጀት አመቱ በሚያዘጋጀው የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ለሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶች ተገቢውን የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት እርምጃ አለመውሰዱ እና ለስራ አመራር /የማኔጅመንት/የውይይት ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በቃለ ጉበኤ በማስደገፍ ማስረጃውን አለመያዙ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱን የሚያማክር የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት አለመቋቋሙ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ5ቱ የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች ውስጥ ለ3ቱ(60%) ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ይሁንታ ያገኙበት ማስረጃ አለመገኘቱ እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ባለፈቃዶች የሚያካሂዱቸው የማዕድን ስራዎች የአከባቢ ጥበቃን ያገናዘቡና ለማኅበረሰቡ የአከባቢ ለልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን በተሟላ መልኩ የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ሚ/ር መ/ቤቱ በከበሩ ማዕድናት የአዘዋዋሪነት እና የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው ግለሰቦች/ሰዎች ወደ ውጭ የሚልኳቸውንና የሚያዘዋውሯቸውን ጥሬ የከበሩ ማዕድናት የተገኘበትን ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እንዲያሳውቁ ስርዓት በመዘርጋት አለመከታተሉና ከማዕድን ስራዎች ህግ ውጪ ለ ሁለት የዕደ ጥበብ ባለፈቃዶች ድጋፍ ሰጥቶ ከቀረጥ ነፃ መሳሪያዎችን እንዲያስገቡ ማድረጉ እንዲሁም በትግራይ/ብ/ክ/መ/ በተለያዩ ቦታዎች የማዕድን ምርመራ ሥራዎች የሚሠሩትን ባለፈቃዶችለማዕድን ሥራ ከውጭ ሀገር ከቀረጥ ነፃ ያስገቧቸውን መሣሪያዎች በየፕሮጀክቱ ማግኘት አለመቻሉ፣

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች ውስጥ በደቡብ ፈቃድ ከወሰዱት 16 ባለፈቃዶች ውስጥ 15ቱ፣ በኦሮሚያ ከ65 ባለፈቃዶች ውስጥ 56ቱና በትግራይ ክልል 78 ባለፈቃዶች በአዋጁ መሠረት በባህላዊ የማምረት የፈቃድ ዘመናቸውን ጨርሰው ፈቃድ ያልመለሱ እንዲሁም የፈቃድ ዘመናቸው ከተጠናቀቀ በኃላ ከ9ወራት እስከ 11ዓመታት በማስቆጠር በፈቃዱ የሚጠቀሙ መሆናቸው፣
- በኦሮሚያ፣በደቡብ እና በትግራይ ክልል ማዕድን ቢሮዎች በአነስተኛ የማዕድን ማምረት ወይም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ተሰጥቷቸው የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች በማክበር ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ የምርት ስራ ያልጀመሩ መሆናቸው፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ የማዕድን ስራዎች መካሄዳቸውን በማዕድን ደንቦች ፣ አዋጆች፣ መመሪያዎች እንዲሁም አግባብ ባላቸው ስምምነቶች(በማዕድን ውል)መሰረት መሠረት አለመቆጣጠሩ፣
- ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች ወደ ማናቸውም ክልል በመግባት በፈቃድ ክልላቸው ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የማዕድን ስራ እንቅስቃሴ ወጥ በሆነና በተሟላ መልኩ በሁሉም ክልሎች ላይ የማይከታተሉና የማይቆጣጠሩ መሆኑ፣ እንዲሁም ለክትትል ለተኬደባቸው አከባቢዎችም ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ ከክልል እስከ ወረዳ ያሉት የማዕድን ቢሮዎች/ፅ/ቤቶች መፍትሄም ሆነ የግብረመልስ ሪፖርት ለባለፈቃዶቹ እንደማይልኩላቸው፣
- ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በስምምነት የሚወሰነውን ወርቅና ብር ማዕድናት መጠን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲያቀርቡ ሁሉም ፈቃድ ሰጪ አካላት ስለመቆጣጠራቸው ወጥ በሆነ መልኩ ከ2004-2006 ዓ.ም በመደበኛነት ክትትል እንደማያደርግ እና ክትትል በተደረገባቸው ክልሎችም ወርቁ ሊቀንስ የቻለበትን ምክንያቶች በመለየት ለችግሮቹ አፋጣኝ መፍትሔ ሊያስወስድ የሚችል የግብረ መልስ ሪፖርት አለመላኩ እንዲሁም በደቡብ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና በጋምቤላ ክልሎች ከ2004-2006ዓ.ም ለብሄራዊ ባንክ የሚቀርበው የወርቅ ዕቅድ አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ መሆኑ ፣
- የማዕድን ሚኒስቴር ወርቅ አቅራቢዎች በአዋሣ፣ በጅማ፣ በመቀሌና በአሶሳ ለሚገኙ ለአራት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ ጣቢያዎች ወርቅ ሲያቀርቡ በወቅቱና ሥርዓትን በተላበሰ መንገድ የሚስተናገዱ ስለመሆኑ የሚከታተልበት ሥርዓት የሌለው መሆኑ እና የከበሩ ማዕድናት እደጥበብ ባለፈቃድ ለስራ የሚያስፈልገውን ጥሬ ወርቅና ብር ከብሄራዊ ባንክ ብቻ እንዲገዙ ስርዓት ቢዘረጋም አለመከታተሉ፣
- በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ፈቃድ ሰጪ አካላት ከማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የተመረተውን ማዕድን በንግድ ልውውጥ በተሸጠበት ዋጋ ላይ ለከበሩ ማዕድናት 8%፣ በከፊል ለከበሩ ማዕድናት 6% ሮያሊቲ፣ ተመን ላልወጣለት ማዕድን ጊዜያዊ የሮያሊቲ ክፍያ ተመን

በማውጣትና ለባህላዊ ማዕድናት በክልሎች በወጣው ህግ መሰረት እንዲሁም የመሬት ኪራይና ሌሎች (የመንግስት ነፃ ድርሻና ግብር) ክፍያዎች ሂሳብ በወቅቱ ተከታትለው የማይሰበስቡና የማይመረምሩ መሆኑ፣

- በ2005 ዓ.ም ኦሮሚያ ክልል ከብር 426,982,815.56 በላይ ከሮያሊቲ ገቢ ያጣ መሆኑ፤
- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከጉጂ ዞን እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከ80 - 85% የሚሆነው የወርቅና የታንታለም ማዕድን ከሕገወጥ አምራቾችና ሮያሊቲ ካልከፈሉ ማህበራት ተገዝተው የሚቀርቡ መሆኑን፣
- በአዋጅ ቁጥር 678/2002 መሰረት ሜድሮክ ወርቅ ክፊያዎችን ባለመፈፀሙ ከመንግስት ነፃ ድርሻ ብር 176,181,221.87 እና ከሮያሊቲ ብር 253,374,630.91 ገቢ አገሪቷ ያጣች መሆኑ፣
- ሮያሊቲ በወቅቱ ለማይከፈሉ፣ ሮያሊቲ ያልተከፈለበት ማዕድን ለሚገዙ በማዕድን አዋጅ ደንብ መመሪያ መሠረት መቅረብ ካለባቸው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትክክል ያልሆነ ወይም የሚያሳስት መረጃ አቅርበው ለተገኙ የማዕድን ባለፈቃዶች በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል ማዕድን ቢሮዎች በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ እየሆነ አለመሆኑ፡፡
- በሚ/ር መ/ቤቱና በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎች እንዲሁም ፋይላቸው ከሚ/ር መ/ቤቱ ቀርቦ የተከለሱት በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በትግራይ፣ በአማራ እና በጋምቤላ ክልሎች እና በአዲስ አበባ አግባብ ባለው መሥሪያ ቤት ቀርቦ በንግድ መዝገብ ሳይመዘገቡና የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣው በ 651/2001 አዋጅ መሰረት የተሰጠ የጸና ፈቃድ ሳይኖራቸው በህገ ወጥ የሚሰሩ እንዲሁም ከ2004-2006 በጀት ዓመት በትግራይ 119 ባለፈቃዶች፣ በኦሮሚያ 53 ባለፈቃዶች እና በደቡብ ክልል 8 ባለፈቃዶች ፈቃዳቸውን በእያንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ በወቅቱ ሳያሳድሱ ነገር ግን የማዕድን ግብይትና ሥራውን በማከናወን ላይ የሚገኙ ግለሰቦች መኖራቸው ፤
- ሚ/ር መ/ቤቱ በባህላዊ አምራቾች የሚመረቱ የወጪ ንግድ ማዕድናት ወይም ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የጌጣጌጥ ማዕድናት በኮንትሮ ባንድ ንግድ ከሀገር ውጭ እንዳይወጡ የሚያደርግ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑና የማዕድናት ምርትና ግብይት እንቅስቃሴ ከምርቱ ጀምሮ እስከ ግብይቱ ድረስ ስርዓትን ያልተከተለ መሆኑ፣
- በአዋጅ ቁጥር 678/2002 መሰረት ሚ/ር መ/ቤቱ እና የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት በማዕድን ስራዎች አዋጅ፣ በደንብ እና በመመሪያ መሰረት የማዕድን ፈቃድ ባላሳደሱ እንዲሁም ባለፈቃዶቹ በአዋጁ መሰረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ፈቃዳቸውን አለመሰረዛቸው ወይም አለማገዳቸው እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት በደቡብ ፣በትግራይ እና በኦሮሚያ ክልሎች ፈቃድ ካላቸው ባለፈቃዶች ውስጥ በፈቃዳቸው ወይም በፈቃድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬታቸው ከተመለከተው ውጭ የሚሰሩ ባለፈቃዶች እንዳሉና ዝርዝራቸው በተሟላ መልኩ በክልሉ ማዕድን ቢሮዎች አለመገኘቱ እንዲሁም ተገቢውን ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሳይኖራቸው የከበሩ ማዕድናት ግብይት

ሥራ ላይ በመሰማራት የከበሩ ማዕድናትን የሚያዘዋውሩ ግለሰቦች ቢኖሩም በክልል ቢሮዎችም ሆነ በሚ/ር መ/ቤቱ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ለአምራቾችና አዘዋዋሪዎች የመወያያ መድረኮችን ቢፈጥርላቸውም ያለባቸውን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረኮችን ያልፈጠረላቸው መሆኑ እና በኦዲቱ ከታዩት 10 ባለድርሻ አካላት ውስጥ ለ8ቱ (80%) ጋር ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ዙሪያ የማዕድን ምርቱን ፈቃድ ለማስተዳደር እና የግብይት አሠራርን ለማጠናከር እንዲያስችል በመቀናጀት የማይሰራ መሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከባንኮች ጋር የከበረና በከፊል የከበረ ማዕድናት ምርትና ሽያጭ ዙሪያ የ ሪፖርት አቀራረብ ስርዓትን በተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ እና የባለፈቃዶችን ወቅታዊ ሁኔታ /ሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ፣ የፈቃድ ዕድሳት ጊዜ፣ የክፍያ መፈፀሚያ ጊዜ... ወዘተ/ ለመከታተል የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ዘዴ የለሌው መሆኑ
- በሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ለመሸጥ እንዲያስችል በጥናት ላይ ተመስርቶ የወጣ ተመን ተጠይቆ ማስረጃ አለመገኘቱ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት በደቡብ፣በኦሮሚያና በትግራይ ክልል ከታዩ 3 የማዕድን ቢሮዎችና 9 ባለፈቃዶች ውስጥ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለ1 የማዕድን ቢሮና ለ7ቱ ባለፈቃዶች ከ2004-2006ዓ.ም በክልሎች ለሚገኙ ለባህላዊ ማዕድናት አምራቾች የቴክኒክ ድጋፎችን (የተሻሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ድጋፎች) አለመስጠቱ
- በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርትና ግብይት ባለፈቃዶች ያመረቱትን ወይም የሸጡትን የማዕድን ዓይነትና መጠን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚያሳውቁበት ስርዓት ቢዘረጋም ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት ተግባራዊነቱን የማይከታተሉ መሆኑ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 651/2001ና 816/2006 በተቀመጠው ጊዜ መሰረት ባለፈቃዶች የምርት፣የግብይትም ሆነ ከግለሰብ የሚሰበስባቸውን የወርቅና ብር መጠን ለሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ ለክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት በወቅቱ ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ፣

ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ግድፈቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይም ለማቃለል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለማዕድን ስራዎች እና የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር የወጡ አዋጆች በስራ ላይ የአፈፃፀም ችግር እንዳያስከትሉ እንዲሁም የሚፈጠሩትን ክፍተቶችን ለመቀነስና የበለጠ አሰሪ ለማድረግ እንዲረዳ የማስፈፀሚያ ደንብ በማውጣት እንዲፀድቅለት ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ እና ሊከታተል እንዲሁም ለከበሩና በከፊል ለከበሩ ማዕድናት ምርት እና ግብይት አስተዳደር የወጡ አዋጆች እና ደንቦችን የበለጠ ግልፅ የሚያደርግ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ ይገባል፡፡
- ሚ/ር መ/ቤቱ በየበጀት አመቱ በሚያዘጋጀው የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ለሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶች እርምጃ ሊወስድ እንዲሁም በመደበኛና በተከታታይ ለሚደረገው ለስራ አመራር /የማኔጅመንት/ ውይይት በውይይቱ ወቅት ለሚነሱት ሃሳቦች የማሻሻያ እርምጃዎችን ለመውሰድ እንዲያስችለው በማኔጅመንት የሚደረጉ ስብሰባዎችን በቃለ-ጉባኤ በመያዝ ተከታታይ ቁጥር ሰትቶ በተገቢው ቦታ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡
- በማዕድኑ ዘርፉ የሚፈጠሩትን ችግሮች ለመፍታት እንዲያስችል ሚኒስቴር መ/ቤቱን የሚያማክር የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት ሊቋቋም እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገርን ጥቅም ከማስከበር እና በአከባቢና በማህበረሰቡ ላይ የሚደርሱትን ጉዳት ከመከላከል አንፃር ለማዕድን ምርት ባለፍቃድ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሁንታ ሊጠይቅ እና የአከባቢን ደህንነት ለመጠበቅ፣ ለማልማትና የማዕድን ማምረት ሥራ ተከናውኖባቸው የተጐሳቆሉ አካባቢዎችን መልሶ የማቅናት ሥራ እንዲሰራባቸው ባለፈቃዶች የሚያካሂዱቸው የማዕድን ስራዎች የአከባቢ ጥበቃን ያገናዘቡና ለማኅበረሰቡ የአከባቢ ለልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ሚ/ር መ/ቤቱ ክልሎች ማግኘት የሚችሉትን ገቢ እንዲያገኙ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበርና ሁኔታዎችን በማመቻቸት የከበሩ ማዕድናትን የአዘዋዋሪነት እና የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጠው ሰው ወደ ውጭ የሚልካቸውንና የሚያዘዋውራቸውን ጥሬ የከበሩ ማዕድናት ጥራትና መጠን የሚያመለክት የላብራቶሪ ውጤት፣ ማዕድኑ የተገኘበትን ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውን እና የከበረውን ማዕድናት ኘሮሰስ ያደረገውን ስምና የፈቃድ ቁጥሩን እንዲያሳውቁ እንዲሁም የማዕድን

ባለፈቃዶች ለማዕድን ሥራ ከውጭ ሀገር ከቀረጽ ነፃ ያስገቧቸውን ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች በትክክል ለማዕድን ሥራው ማዋላቸውን የሚቆጣጠርበትና የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የከፍተኛ ደረጃ ፣ የአነስተኛ ደረጃና የባህላዊ ማዕድን የማዕድን ማምረትየፈቃድ ዘመን በማዕድን ስራዎች አዋጅ መሠረት ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ መብለጥ የለበትም፡፡ እንዲሁም የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ የምርት ስራውን ለመጀመር እና የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች እንዲያከብሩ ሚ/ር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርትና ግብይት እንቅስቃሴ ከምርቱ ጀምሮ እስከ ግብይቱ ድረስ ህጋዊ ስርዓትን እንዲከተል ለማድረግ እንዲያስችል ባለፈቃዶችን በማዕድን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች እና ውሎች ሊያስተዳድርና ሊቆጣጠር እና ፈቃድ ሰጪ አካላት በተያዘላቸው በጀትና ጊዜ መሠረት የሚፈለገው የሰው ኃይል በበቂ ሁኔታ በማሟላት ወደ ማናቸውም ክልል በመግባት በፈቃድ ክልላቸው ላይ ወይም ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የማዕድን ስራ እንቅስቃሴ በአግባቡ መሠራታቸውን ሊቆጣጠሩና ሊከታተሉ እንዲሁም የሀገሪቷን የኢኮኖሚ ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲረዳና ህገወጥ ነጋዴዎች እንዳይስፋፉ ለማድረግ እንዲያስችል የከበሩ ማዕድናት እደጥበብ ባለፈቃድ ለስራ የሚያስፈልገውን ጥሬ ወርቅና ብር ከብሄራዊ ባንክ ብቻ እንዲገዙ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስርዓት በመዘርጋት ሊከታተል ይገባል ፡፡
- የሚፈለገው የውጭ ምንዛሪ እንዲገኝ፣በአራቱም ክልሎች በተቋቋሙ የብሄራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ ጣቢያዎች እና በአዘዋዋሪዎች መካከል ያለውን ክፍተት በማጥበብ የወርቅ አዘዋዋሪ ባለፈቃዶች ሳይጉላሉ፣ በወቅቱና ሥርዓትን በተላበሰ መልኩ በእቅዳቸው መሠረት ለባንኩ ማቅረብ ያለባቸውን ወርቅ ለማቅረብ እንዲችሉ ሚ/ር መ/ቤቱ ወርቅ አቅራቢዎቹ የሚስተናገዱበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሠራር ስርዓት ሊዘረጋ እንዲሁም የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣ አዋጅ ቁጥር 651/2/001ና በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በስምምነት የሚወስነውን ወርቅና ብር ማዕድናት መጠን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአራቱም ክልል የወርቅ ግዥ ጣቢያዎች የሚያቀርቡ መሆኑን ፈቃድ ሰጪ አካላት ስለመቆጣጠራቸው ሊከታተል ይገባል፡፡
- ሀገሪቷ ከከበሩና በከፊል ከከበሩ ማዕድናት የሚገኘውን የሮያሊቲ ገቢ በአግባቡ ለሚፈለገው ዓላማ ለማዋል እንዲቻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን ከማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የሚገኘውን የሮያሊቲ፣የመሬትና ሌሎችክፍያን እንዲሁም ለባህላዊ ማዕድናት በክልሎች በሚወጣው ህግ መሰረት ወጥ በሆነ መልኩ ሊሰበስብና

ሂሳባቸውን ሊመረምሩ እንዲሁም የማዕድን ባለፈቃዶች ሮያሊቲ በወቅቱ ካልከፈሉ፣ ሮያሊቲ ያልተከፈለበት ማዕድን ከገዙ፣ በማዕድን አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ መሰረት መቅረብ ካለባቸው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትክክል ያልሆነ ወይም የሚያሳስት መረጃ አቅርበው ከተገኙ በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 መሰረት እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡

- የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርትና ግብይት እንቅስቃሴ ከምርቱ ጀምሮ እስከ ግብይቱ ድረስ ህጋዊ ስርዓትን የተከተለ እንዲሆን ህገወጥ ግብይት እንዳይስፋፋ በአዋጅ ቁጥር 678/2002ና 651/2002 መሰረት ማንኛውም ሰው ወርቅ ወደ ሚመረትበት አከባቢ ሄዶ ወርቅ ለማምረት እና የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማካሄድ አግባብ ባለው መሥሪያ ቤት ቀርቦ በንግድ መዝገብ በመመዝገብ የጸና ፈቃድ ሊያገኝ ወይም የታደሰ የከበሩ ማዕድናት ወርቅ ንግድ ሥራ ሊኖረው ፣ በየፈቃድ ዘመኑ መጨረሻ ወቅቱ ሣያበቃ የምርትና የግብይት ሥራ ፈቃዱን በየዓመቱ ሊያሣድስ ይገባል፡፡
- ሚ/ር መ/ቤቱ በባህላዊ አምራቾች የሚመረቱ የወጪ ንግድ ማዕድናት ወይም ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የጌጣጌጥ ማዕድናት በኮንትሮ ባንድ ንግድ ከሀገር ውጭ እንዳይወጡ ለማድረግ እንዲያስችልና ሀገሪቷም ከማዕድኑ የሚታገኘውን ገቢ እንዳታጣ እስከ ክልል የሚወርድ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ፈቃድ ሊያድስ እንዲሁም ባለፈቃዶቹ በአዋጁ መሰረት ግዴታቸውን ካልተወጡ ፈቃዱን ሊያግድና ሊሰርዝ እንዲሁም በፈቃዱ ወይም በፈቃድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ከተመለከተው ውጭ ከተሰማሩ፣ ከግለሰብ የሚሰበስባቸውን የወርቅና ብር መጠን ሪፖርት ካላደረገ በህጉ መሰረት ሊቀጣ ይገባል ፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸውን በማሰልጠንናግንዛቤ በመፍጠር እንዲሁም ከወረዳ እስከ ዋና ከተሞች የፍተሻ ኬላዎችን በማቋቋም የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ዙሪያ ክትትል በማድረግ ተገቢው ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሳይኖረው የከበሩ ማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ በተሰማሩት ግለሰቦች/ድርጅቶች ላይ በአዋጅ ቁ 651 መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ባለፈቃዶች የሚገጥማቸውን ችግሮች በማየትና በየጊዜው መደበኛ የሆነ መድረክ በመፍጠር የመፍትሔ አቅጣጫ በማስቀመጥ የሚፈጠሩትን ክፍተቶች ሊቀርፍ እንዲሁም በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ዙሪያ የማዕድን ህገወጥ ንግድን ከመቆጣጠርና ከማዕድን ምርት የሚገኘውን ገቢ ከማሳደግም በተጨማሪ የማዕድን ምርቱን ፈቃድ ለማስተዳደር እና የግብይት አሠራርን ለማጠናከር እንዲያስችል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ሊሰራ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከባንኮች ጋር የከበረና በከፊል የከበረ ማዕድናት ምርትና ሽያጭን በተመለከተ ወጥነት ያለው  የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ እና ማዕድንናት ያለውን የማዕድን ምርት እንቅስቃሴ ለማወቅ እንዲያስችልና በባለፈቃዶች ላይ የሚፈጠሩትንም ችግሮች ለይቶ ለማወቅና የመፍትሔ ሃሳብ ለመስጠት እንዲያስችል የማዕድን ባለፈቃዶች ሪፖርት የሚያቀርቡበት ፣ የፈቃድ እድሳትና የክፍያ መፈፀሚያ ጊዜን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ መረጃ አያያዝና ልውውጥ ዘዴ ተግባራዊ ሊያደርግ ሊኖረውይገባል፡፡
- የማዕድን ሚኒስቴር  የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ለመሸጥ በጥናት ላይ የተመሰረተ ተመን በማውጣት እና ወቅታዊ የገቢያ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ በየጊዜው በማሻሻል  ለባለፈቃዶቹ በመስጠት በግብይቱ ዙሪያ  ህጋዊ ድጋፍ ሊያደርግላቸው እንዲሁም የባህላዊ ማዕድናት አምራቾች ምርት ለማሳደግ እንዲረዳ እና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን(የቴክኒክ ድጋፎችን)  በማስተዋዋቅ የማዕድናት አምራቾችን የማምረት ክህሎት በማሳደግ ባለፈቃዶቹ እንዲበረታቱ በማድረግ የተሸሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎችንና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና  በመስጠት  በክልሎች ለሚገኙ ለባህላዊ ማዕድናት አምራቾች ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርትና ግብይት ባለፈቃዶች ያመረቱትን ወይም የሸጡትን የማዕድን ዓይነትና መጠን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚያሳውቁበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊነቱን ሊከታተል እና የምርት ባለፈቃድ ያመረተውን ወይም የሸጠውን የምርት ዓይነትና መጠን እንዲሁም የእደ-ጥበብ ባለፈቃድ ከግለሰብ የሚሰበስባቸውን የወርቅና ብር መጠን በህጉ በተቀመጠው ጊዜና በወቅቱ ለፈቃድ ሰጭው አካል ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተካሄደው የክዋኔ ኦዲት ወቅት ለተደረጉልን የስራ ትብብር እናመሰግናለን!!!